ዘራ (ልብ ወለድ)

አቤንኤዘር መርጃን 2012 ዓ.ም

የቅጂ መብት - © አቤንኤዘር መርጃን

©መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

©All rights reserved.

ይህንን መፅሀፍ ያለ ፀሀፊው ፍቃፍ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ስራ በሙሉ ወይም በከፊል አባዝቶ መጠቀም አይፈቀድም።

የመጀመሪያ እትም 2012 ዓ.ም

በመፅሀፉ ላይ አስተያየት ቢኖርዎት በቴሌግራም አድራሻ t.me/abenezer_merjan ብለው ፀሀፊውን ማግኘት ይችላሉ።

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

1.ያመለጠው እድል..... 4

2.ሆ ! በሉ ሆ !..... 8

3.ማየት ማመን ነው ወይስ ማመን ማየት ነው.....16

4. ከፈተናው አንዱ..... 23

5. እንቢ ለእውነት..... 29

6.ህልም እንጀራ ሲሆን 41

7. ዲፕሎማው 50

8. ደግነት 59

9. ጥቁሩ ካባ 74

10. ቃል 84

11. አድራሻው 100

12. ዞራ 120

ያመለጠው እድል

"እንዴት ?!" በማለት ከሚያሰማራቸው ከብቶች በክሳት ደረጃ ዝቅ ላለችው ከብት አምባረቀባት ፤ ላሚቷ ግን ነገሩን የለመደች ይመስል ስሜቱ እና ቁጣውን ችላ በማለት በላምኛ ገላምጣው አፏን ምታለፋበት ደረቅ ሳር ጋጠች።

ለነገሩ ላሚቷ ስሜቱ ቢገባትና ቃሉን ብትረዳ እንደ ሰው አፍ አውጥታ

"አይዞህ !" ብትለው ያሳለፋቸው ድፍን ሀያ አመታት ከሚያስባቸው ሀሳቦችና ከሚያልማቸው ህልሞች ላፍታም ዘወር አያደርጉትም። ምክንያቱም ለሱ የማፅናኛ ቃል እለት እለት እንደሚያሰማራቸው የቤተሰቡ ብቸኛ ሀብቶች ከእነዚያ ከሲታ ከብቶች ጋር ደባል ተደርጎ የሚሰጠው ይህ የማፅናኛ ቃል ነው "አይዞህ!"

ብሩክ ይባላል የቀይዳማ ረዥምና የተደላደለ ሰውነት ያለው ልጅ ነው ተወልዶ ያደገው ብሎም አሁን ከብቶቹን የሚያሰማራባት ሜዳ ባለቤት የሆነች አነስተኛ ከተማ ቀመስ ነገር ግን የከተማው ጣዕሙ የጠፋባት ከዚህም በተጨማሪ ተንፏቆ በማደግ ፈንታ እንደ ክረምት ወራጅ ውሀ ቁልቁል እየወረደች የመንደሩን ነዋሪዎች አማርራ ከተወለዱበት ከቅድመ አያቶቻቸው ሰፈር አፈናቅላ ለሰቆቃ የምትዳርገው የገጠር መንደር።

ይህች አነስተኛ መንደር እንደ ወጉ ወደ ከተማነት ምትንደረደርበት እድል ከውጭ ሀገር በመጡ ባለሀብቶች አግኝታ ነበር ግን የሰፈሩ ክፉ ልማድ መንደሪቷ ወደ ከተማነት እንዳትለወጥ ሰንክሳር የሆነ ነገር ነበር።

የመንደሩ ነዋሪዎች ለባለሀብቶቹ ጥለው መጥፋት የሚያምኑበት ጉዳይ አለ።

ጉዳዩም እንዲህ ነው ፦ ባለሀብቶቹ ፋብሪካቸውን የሚተክሉበትን ቦታ ለመምረጥ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ሰፋቱ እንደልባቸው የሆነ ፤ ደግሞም አንድ ፋብሪካ አይደለም አየር ማረፊያ ከሶስት የጋራ መኖሪያ ቤት መንደሮች ጋር የሚይዝ ፤የመሬቱ ለምነት ድንጋይ ቢዘራበት አለት

የሚያበቅል መስሎ የተሰማቸው አንድ መሬት ጋር ቀልባቸው ወደደው እንደተማከረ ሰው ባለሀብቶቹ ይህ ቦታ በአንድ ሀሳብ መረጡት።

ነፍሳቸው ይማረውና የብሩክ አባት አቶ ፈይሴ በተላላኪ በአስቸኳይ እንዲጠሩ ተደረገ።

ባለሀብቶቹም የእሳቸው መሬት እንደፈለጉትና በምትኩ የሚሰጡአቸው የገንዘብ መጠን ነገሩአቸው። አቶ ፈይሴም ሀገር የሚመግቡበት የቡና ማሳቸው አሁን ግን ማዳበሪያ በስርአት ካለመጠቀማቸው የተነሳ አሲዳማነት የወረረው ፤ የተንጣለለውና የተገራ የዱር ፈረስ ከአንዱ ጥግ እስከ አንዱ ጥግ ቢጋልብበት እስከ መሀሉ ብቻ ቢደርስ እንጂ እርሻቸውማ ሰፊ ነበር። ይህን አስበው ሳይጨርሱ ግን የተጠራው የገንዘብ መጠን አቶ ፈይሴ አንድ ነገር እንዲያስታውሱ ገፋፋቸው ፡ በአንድ ወቅት መንደራቸው የቢጫ ወባ ወረርሽኝ ተከስቶ በነበረ ጊዜ የመንደሩን ነዋሪን ያሳዘነ እስክስታ እያስመታ ወደ ሞት ብዙ የመንደሩ ሰዎችን የሸኘ ጊዜ ትዝ አላቸው። እርሳቸውም በዚሁ በሽታ ተጠቅተው እስክስታ አይሉት መንቀጥቀጥ ተንቀጥቅጠዋል።

አሁንም የሆነው ይህ ነው ከእግር ጥፍራቸው ጀምሮ እስከ ራስ ጠጉራቸው ተንዘፈዘፈ።

ባለሀብቶቹም የነገሩን መልስ በጉጉት እንደሚጠብቁና በቅርብ እንደሚመለሱ ለብሩክ አባት ለአቶ ፈይሴ ተናግረው ተሰናብተዋቸው ሄዱ።

በእነ ብሩክ መንደር አንድ ልማድ አለ በዚህ ልማድ መሰረት አንድ መልካም ወይንም ክፉ ነገር ሲገጥም የሚያማክሩት የሀገሬው አዋቂ አለ በልምዱ መሰረት ይህ አዋቂ ዘራ የሚባል መንፈስ እንደሚያድርበትና በሚመጡት

ጥቂት ቀናቶች ምን እንደሚፈጠር ይናገራል ተብሎ ይታመናል።

የመንደሩ ነዋሪዎች ለዞራ መንፈስ ከፍተኛ ቦታ እና ፍራቻ ስላላቸውና መንፈሱ የሚቃወሙትን ይገድላል ብለው ስለሚያምኑ አንዳች አይነት ጥርጣሬ በውስጣቸው አይፈጠርም።

በወቅቱም የሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን ቢባሉም ማንም ሰው ግን ደፍሮ አቶ መኮንን በማለት ሙሉ ስማቸውን አይጠራቸውም ይልቅ ጌታው ፣ አለቃው እና አዋቂ በማለት ይጠሯቸዋል።

እናም የብሩክ አባት እንደ መንደሩ ልማድ መሰረት ጉዳያቸውን ይዘው ወደ የሀገሬው አዋቂ ቤት ይሄዳሉ ።

ጉዳያቸውም በአጭሩ ለሀገሬው አዋቂ አሳወቁ።

የገንዘቡን መጠን የሰማው የሀገሬው አዋቂ አይኑን እስከ አራት የሚደርስ ጊዜ ካአጉረጠረጠ በኋላ "አቶ ፈይሴ የእርሶ ጉዳይ ከፍተኛ ነው በነጋው ተመልሳችሁ ይምጡ" በማለት የብሩክን አባት ይሸኙአቸዋል ።

የብሩክ አባት ከቤቱ ለጥ ብለው እጅ ነስተው በመውጣት በነጋታው መልስ አገኛለው ብለው ተስፋ ይዘው ወደ ሀገሬው አዋቂ ቤት ገሰገሱ የሀገሬው አዋቂ ግን "ይህ መልእክት ለአንተ ብቻ እንድነግር ዞራ አልፈቀደልኝምና የመንደር ሰው መሰብሰብ አለበት " ተባለ።

የመንደሩ ሰውም ከመንፈስ ዞራ መልእክት አለህ ና ውጣ ተብሎ ሲለፈፍ

በማጀት ለባለቤቷ እና ለልጆችዋ እንጀራ መጋገር ላይ የነበረች እመቤት ከነ ሊጧ ፤ በመደቡ ላይ ሆኖ በርጋታ የወፎችን ዝማሬ ሲሰማ የነበረው ኩታራ ከነ አገለደመው ጨርቅ ፤ የማለዳዋን ፀሀይ ለመሞቅ ጋቢያቸውን አጣፍተው ፊታቸው ለምስራቅ ጀርባቸውን ለምዕራብ ሰጥተው የተቀመጡት አባትም ከነጋቢያቸው እንዲሁም በኩራዝ ብርሀን ለሊቱን ሲያነብ አድሮ የእንቅልፍ አምሮት ያልወጣለት ብሩክን ጨምሮ የመንደሩ ሰዎች ወደ መሰብሰቢያው ዋርካ በቅፅበት ተሰበሰቡ።

ሆ ! በሉ ሆ

የዞራን መልእክት ለመታደም ሁሉም ከያሉበት ወደ ዋርካው ከመጡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ የሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን ሁለት ሎሌዎቻቸውን አስከትለው ከመሬቱ ጉብ ወዳለው ቦታ ልክ እንደ መልአክ በዝግታ እየተራመዱ ከፍ ከፍ አሉ ። የሀገሬው አዋቂ መልካቸው ጠቆር ብሎ ቁመታቸው አጠር ያለ ሲሆን የአፍንጫቸው ሰልካካነት እና ከግራ አይናቸው ጎን ያለችው ረጅም ቀጭን ጠባሳና ሙዳ ሰጋ የሚያክለው የከንፈራቸው ውፍረት የልዩ ፍጥረት መልክን ሰጥቷቸዋል ትኩር ብሎ ለተመለከታቸው የአይናቸው ቅላት ብርክ ያስይዛል የለበሱት ጠቆር ከሚል ቆዳ የተሰራው እንደ ጋቢ የለበሱት ልብስ ልዩ ግርማ ሰጥቷቸዋል።

አቶ መኮንንም ጉሮሮአቸው ሁሉት ጊዜ ከጠረጉ በኋላ እንዲህ ሲሉ ለመንደሩ ነዋሪዎች አሰሙ " የመንደሩ ነዋሪ የሆናችሁ ሆይ ስሙ ....እነሆ ታላቁ አባታችን ዞራ ማታ ተገልጦልኝ በመንደሩ ሊሆን ያለው ነገር በህልም

ቁልጭ አድርጎ አሳይቶኛል። "በማለት ለአፍታ እንደማዘን አንገታቸውን ደፉ ። አንገታቸው በደፉበት ወቅት በዚያ የሚያልፍ ሰው ቢያየው የሰቅላት ፍርድ ተፈርዶበት በገመድ የተንጠለጠለ ሰው ይመስለው ነበር።

ይህንን የተመለከቱት የዋሆቹ የመንደር ነዋሪዎች "ምናልባት መንፈሱ ዞራ አስፈሪ ነገር አሳይቶ ቢሆን ነው አዋቂው አንገቱን እንደዚህ የደፋው " በማለት በዝቅተኛ ድምፅ እርስ በእርሳቸው አጉተመተሙ።

የሀገሬው አለቃ ሎሌ ዝም እንዲሉ እጁን ወደ ላይ ገትሮ አቆመው በአንድ ጊዜ ሁሉም የመንደሩ ነዋሪዎች ፀጥ አሉ ምናልባት በፀጥታው መሀል አንዲት ትንሽዬ ጉንዳን ከተመናመነ ሳር ብትወድቅ ፀጥታውን ታደፈርሰው ነበር።

አሁንም የሀገሬው አለቃ ቀና በማለት ማውራቱን ቀጠለ "ማታ በህልሜ ለሰሚ የሚከብድ ለተናጋሪ የሚታክት ነገር ተመለከትሁ እነሆ እነኚህ ገጠራችሁን ከተማ ፈረሶቻችሁ ባለ ጎማ እናደርግላችኋለን ያሉት ባለሀብቶች ለዘመናት ሰናመልከው እና ስንገዛለት የነበረው የዞራ አምልኮ ቤት ሲያፈራርሱ ተመለከትኩ ። ከዚያም በመቀጠል ዞራ ወደ አቶ ፈይሴ መሬት እየጠቆመኝ ' ይህ መሬት ታስነኩትና ልጆቻችሁ የጅብ መጫወቻ ሚሰቶቻችሁ የጌታ ባርያ መሬቶቻችሁ የአውሬ መፈንጫ ይሆናል!' በማለት ነገረኝ።የመንደሬ ህዝብ ሆይ ስማ ልጆቻችሁ ሚሰቶቻችሁ እና መሬታችሁ የምትፈልጉአቸው ከሆነ ተከላከሉ የገቡትን እነዚህ ቁጣ አምጪዎችም አስወጡ አለበለዚያ ዞራ ያዝናል ይቀጣናል።" በማለት ለመንደሩ ህዝብ በከፍተኛ ቁጣ እየጮሁ እና ለማዘን እየሞከሩ ተናገሩ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የመንደሩ ነዋሪዎች ለባለሀብቶቹ ያላቸው አመለካከት ተቀይሮ ወደ ጥላቻ ሽግግር ያደረገው ባለሀብቶቹ ለመንደሩ ነዋሪዎች በበረከት ፈንታ እርግማን በደስታ ፈንታ ለቅሶን በእልልታ ፈንታ

ዋይታን በፋብሪካ ፈንታ የልቅሶ ድንኳን ይዘውላቸው እንደመጡ አመኑ።

በሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን ትዕዛዝ መሰረትም የመንደሩ ነዋሪዎች ባለሀብቶቹ ሀገር ሰላም ብለው ሲመጡ ጠብቀው ሰድበው አንቋሸውና ተፍተውባቸው የመጡበትን እንኳን ለመምታት ለመንካት የሚያሳሳው ውብ እና ውድ መኪኖቻቸውን ሰባብረው ከመንደሩ ላይመለሱ አባረሩአቸው።

****

ምንም እንኳን ይህንን ትዕይንት ከተፈጠረ አምስት አመት ቢያልፉትም ብሩክ ግን እስካሁን የባለሀብቶቹ መባረር ውስጡን ያሳምመዋል ።

ከመንደሩ ካሉት የእሱ እኩዮች በቀለም እውቀት ብሩክ የሚስተካከለው የለም የእድል እና የግጥምጥሞሽ ጉዳይ ሆነ እንጂ መማሩንማ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል በየቀኑ አስራ ሰባት ኪሎ ሜትር ሊሞላ አምስት መቶ ሜትር ሚቀረው መንገድን እያቆራረጠ ይህ ነው በማይባል ድካም ተምሯል። አባቱ ለቀለም ትምህርት ቦታ ሰላላቸው እንጂ በመንደሩ ነዋሪዎች ዘንድ ማንም ልጁን እንደ አቶ ፈይሴ ያስተማረ የለም።

ብሩክ ከሚጠብቃቸው ከሲታ ላሞች ዘወር ብሎ ፊቱን ወደ ትምህርት ቤት አቅጣጫ ሲያዞር ከሁለት አመት በፊት የሆነው የአስራ ሁለተኛ ክፍል ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተናው ትውስ አለው ። እንደማንኛውም ጎበዝ ተማሪ በቂ ዝግጅት አድርጎ የተማሪ መፈተኛ ቅፅ ሞልቶ ፈተናው እስኪመጣ በጉጉት እንጂ በፍርሀት አልጠበቀውም ነበር። የፈተና ሰሞን ሲቃረብም የብሩክ አባት አቶ ፈይሴ በጠና ይታመማሉ ቤተሰብ በሙሉ ትኩረቱን ከተማሪውና ከተስፈኛው ብሩክ አንስቶ ወደ አቶ ፈይሴ አደረገ

እርሱን ከሞት ለመታደግም ርብርብ ተጠናከረ ከባህል መድሀኒት እስከ ዞራ ቢዞሩ ምንም የረባ ነገር አላገኙም። ብሩክ ግን ለረባ ላልረባ ነገር ወደ ዞራ እና ወደ ሀገሬው አዋቂ መሄዳቸው አልጣመውም ነበር ይልቅ ወደ ከተማ ሄደው ዘመናዊ ህክምና እንዲያገኙ ሀሳብ ሲያነሳ የቤተሰቡ አካላት በሙሉ በከፍተኛ ሁኔታ ተቆጥተው ዝም እንዲል አስጠነቀቁት።

ለብሩክ ፈተና አንድ ሳምንት ሲቀረው አቶ ፈይሴ ፍፁም ጤና አገኙ። ወደ ለመዱት የቡና ተክል ማልማት ሰራም ተመለሱ አባትም እንደመሆናቸው ለብቸኛ ወንድ ልጃቸው የአባት ምክሩን በጓሮአቸው በሚገኝ የቡና ተክል ስር ተጠው ምክሩን ገሱት አቶ ፈይሴም እንዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ"ይኸውልህ አቡሽ "አቡሽ ማለት ቤተሰቡ እና የቅርብ ጓደኞቹ የሚጠሩበት የቤት ሰሙ ነው። "ይኸውልህ አቡሽ ይህች መንደር እንደ ሌሎች ሰፋፊ ከተሞች ማደግ የምትችል መሬቷ ለም የሆነ መልክአ ምድርዋ ለሁሉም የሚስማማ ነበር ግን ልጄ አልሆነም የመንደሩ ነዋሪዎችን ልማድ ታውቀዋለህ የልማዳቸው አስተሳሰብ አዕምሮአቸውን አደንዝዞታል እንደ ሰው ሳይሆን የሚያስቡት እንደ ሀገሬው አዋቂ እና እንደ ዞራ መንፈስ ተብዬው ሀሳብ ነው የሚኖሩት። ደግሞም አቡሽ የማህበረሰቡ ልማድ ራሱን ማህበረሰቡን የሚጎዳ ፤ ስልጣኔን የሚጠላ ፤ ህዝቡን ወደ ኋላ የሚጎትት ፤ አስተሳሰባቸውን የሚያሳውር ከሆነ አትቀበለው ተቃወመው።

ልጄ አስተሳሰብህ በዚህ እኩይ ልማድ እንዳይበረዝ በማለት ነው የሚታክተውን መንገድ ለብዙ አመታት እንድታቆራርጥ ብሎም የቀለም ትምህርት እንድትማር የገፋፋሁህ።

አንተም በርትተህልኝ ይኸው እስካሁን ቤቱ በአንተ የምስክር ወረቀትና ሜዳልያ ተሞልቷል።ልጄ እኔ መቼ ወደማይቀረው እንደምሄድ አላውቅምና

የቤቱን እና የሁለቱ መንትያ እህቶችህ ሀላፊነት ለአንተ እሰጥሀለው አደራ በቅርቡ ፈተናህን ስትፈተን ዞራ ያባረራቸውን ከተማ የሚጎሳቆሉት ጎረቤቶችህን እያሰብክ የእኔ እና የቤተሰቡ ድህነት እያሰብክ ይህችን መንደር እያሰብክ ነገህን በተስፋ እያየህ ተፈተን። ልጄ ይህች መንደር ምትለወጠው በአንተ እውቀት እና ብልሀት እንደሆነ ውስጤ ይነግረኛል። አይዞህ ፈፅሞ ከዞራ የሚመጡ ምክሮችን እንዳትሰማ የሱ ምክሮች ጠማማ ሀሳቡም ለእድገት ሳይሆን ለውድቀት የሚጋብዙ ናቸው። ልጄ አንተ ከበረታህና ከክፉው ልማድ ራስህን ካገለልክ መከራው ብዙ ቢሆንም ነገን በተስፋ እየጠበክ እንደምትለወጥ አስበህ ኑር። በፈተናው ጥሩ ውጤት ካመጣህ "

በማለት የተጣጠፈ ወረቀት በእጁ እያደረጉ "አዲስ አበባ የሚባል ቦታ ሄደህ ይህ ወረቀት የሚጠቁምህ ቤት ወረቀቱን አሳያቸው ዱሮ ለስራ እመላለስ በነበረ ጊዜ የተዋወኳቸው መልካም ሰዎች ናቸው። " ካለው በኋላ አቶ ፈይሴ ልጃቸው ብሩክን እቅፍ አድርገው አለቀሱ ። ብሩክ የሚሰማው ምን እንደሆነ ግራ ቢገባውም የአባቱን እንባ እሱንም አሸነፈው።

****

የፈተናው ቀን ደርሷል ብሩክም በለሊት ያችን አታካች መንገድ እያሳበረ ለመሄድ ቤት ያገኘውን ቀማምሶ ሲወጣ አባት ያለ ልማዳቸው ደጅ ድረስ በመውጣት እንባቸውን እያዘሩ አቅፈው ተሰናበቱት።

ብሩክ ትምህርት ቤት ከደረሰ በኋላ ወደ መፈተኛው አዳራሽ ገባ ትምህርት

ቤት ላይ የክፍል ጓደኞቹ እና ሁሉም የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ብሩክ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያመጣ ሙሉ እምነት ነበራቸው።

ፈተናው ተጀመረ በቅድሚያ የእንግሊዘኛ ቋንቋ እየተፈተኑ ብሩክ ቀና ብሎ ዉደ መስኮቱ ሲያስተውል የሀገሬው አለቃ አንደኛው ሎሌ ቆሞ ተመለከተ። የሀገሬው አለቃ ሎሌ በድንገት እዛ በመገኘቱ ብሩክ ውስጡ ተረበሸ ምክንያቱም ይህ ሎሌ ሰራው መንደር ለመንደር እየዞረ የሞቱ ሰዎች ካሉ የሚያረዳ ስለነበር ነው።

ብሩክ የቀሩትን አስር ገደማ ጥያቄዎች እንደ ነገሩ ሞልቶ በአንድ አይኑ ሰአቱን በአንድ አይኑ ሎሌውን እያየ በሀሳብ ነጎደ አንዳንድ ተማሪዎች ግን መልስ እንዲሰጣቸው ብሩክን ቢነዘንዙትም ከገባበት የሀሳብ ባህር መውጣት አልቻለምና ዝም አላቸው።

ብሩክም በሀሳቡ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ሲያወጣ እና ሲያወርድ "ሰአት አልቋል!!" የሚል ጎርናና የአስፈታኛቸው ድምፅ ከሀሳብ ባህር ጎትቶ አወጣው።

ብሩክም እየተቻኮለ ወደ ሎሌው ሄዶ ምን እንደተፈጠረ እንዲነግረው ነዘነዘው። ሎሌው ግን ከአቋሙ ፍንክች አላለም ፤ ሰፈር ይዤህ መሄድ አለብኝ እንዳለው ነው። ብሩክም በእሺታ አንገቱን ነቀነቀ።

ብሩክ ያንን ሁሉ መንገድ አሳብሮ መንደሩ ሲገባ ያየውን ለማመን አንገራገረ ቤታቸው ደጃፍ ህዝብ የሚሰበሰብ ድንኳን ተጥሏል። ብሩክ ሎሌውን በመተው በሩጫ ወደ ድንኳኑ አቅጣጫ በመሮጥ ወደ ውስጥ ገባ አጎቱ ፣ አክስቱ ፣ ሁለት ትናንሽ እህቶቹ በመራር ሀዘን ውስጥ ሲያለቅሱ አየ ብሩክ ራሱን መቆጣጠር አቃተው። "አ....ባ.....ዬ!!!!" በከፍተኛ ድምፅ ጮኸ አበደ ለያዥ ለገራዥ አስቸገረ። ለካስ ጠዋት የተሰናበተኝ

እስከወድያኛው ነው በማለት መሬቱን በእጆቹ እየቧጠጠ ደረቱን እየደቃ አሰቃቂ ለቅሶ አለቀሰ።

መረጋጋት አይቀርምና ተረጋጋ የዛሬው የሂሳብ ፈተና አምልጦታል። በህይወት እድል አንዴ የሚመጣው ይህ ፈተና እንዳያመልጠው ራሱን እያረጋጋ እና አባቱ የሰጠው አደራ እያሰበ እንደ እናት ለሚያያት አክስቱ ነገ ፈተናውን እንደሚቀጥል ነገራት አክስቱን ካንገራገረች በኋላ ፈቀደችለት።በነጋታው ብሩክ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ የአባቱ ማረፍ ሰምተው የነበሩ የክፍሉ ልጆች ከልባቸው አዘኑለት። ፈተናው ተጀመረ ብሩክ ግን አልቻለም። ጥቂት ጥያቄ እየሰራ ማንም ሳያየው እያቀረቀረ ያለቅሳል እንደዚህ እያለ ሁሉንም ፈተናዎች ተፈተነ።

በሰርአቱም የአባቱን ለቅሶ ተቀምጦ እንግዳ አስተናግዶ ለቅሶው ተነሳ ድንኳኑም ፈረሰ ነገር ግን የአባት ሀዘን ሆኖበት ልቡ ላይ ያለ ወራጅ እና ቋሚ የተገነባው የሀዘኑ ቤት ከልቡ ውስጥ አልፈረሰም።

የፈተና ውጤት እንደመጣ ተነግሮት ያቺን አታካች መንገድ አሳብሮ ትምህርት ቤት ደረሰ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተሩ ብሩክን ለብቻው ቀኝ እጁን እየጎተተ ቢሮ አስገባው ። የተለያዩ የማፅናኛ ቃል ሲነግሩት ብሩክ ውጤቱ ዝቅ እንዳለ ገባው ነገር ግን ዳይሬክተሩ የብሩክ ውጤትን የሚያሳየው ወረቀት ሲሰጡት ብሩክ ከሬሳ በላይ ደረቀ የውጤቱ ፊደላት እየተዘበራረቁ ሁለት ይሆናሉ መልሰው ወደ ወጡበት ፊደል ገብተው አንድ ይሆናሉ ፤ አንዴ ደግሞ ቁጥሮቹ እኛን ማየት አትችልም ብለው የተመካከሩ ይመስል ላይ ታች ይርመሰመሱበታል እነዚህን ታግሎ የፈተናውን ወረቀት አጥብቆ ይዞ ትኩር ብሎ ሲመለከት የመጀመሪያ ቀን ከተፈተነው ከእንግሊዘኛ በስተቀር ሁሉም ከሀያ በታች አገኘ በድምሩ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት አመጣ።

የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ውጤቱ ዝቅ ያለው በአባቱ ሞት ምክንያት እንደሆነ ገብቶታል ቢሆንም ብሩክ ከዚህ በላይ ተጨንቆ ራሱን እንዳይጎዳ በማሰብ ምክር ቢጤ ሊለግሱት ጉሮሮአቸውን ሲያፀዱ ብሩክ ከተቀመጠበት ወንበር ተነስቶ ቆሞ ለብቻው ማውራት ጀመረ

"መቶ ሰላሳሁለት ከአምስት መቶ ፤ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ከሰባት መቶ " በማለት ቁጥሮቹን እየደጋገመ እያወራ የፈተናው ውጤት የመጣበት ወረቀት የዳይሬክተሩ ቢሮ ትቶት በሁለት እጆቹ ጭንቅላቱን ይዞ ከትምህርት ቤቱ ወጣ ይህ ሲሆን የሚመለከቱትና የሚያዝኑለት እንዲሁም ከንፈራቸውን በመምጠጥ ሊያፅናኑት የሞከሩም አልጠፉም ነበር።

****

"ብሩክ.... ብሩክ ....ብሩክ ላሞችህ ወደ ወንዙ እየሄዱ ነው።" የሚል የመንደር አብሮ አደግ ጓደኛው ጥላሁን ድምፅ ነው ከሀሳብ አለም የጠራው።

ብሩክ ከዞረበት አቅጣጫ ላሞቹን ለማምጣት ወደ ከሱት ላሞች ገሰገሰ።

ጥላሁን እና ብሩክ የነፍስ ጓደኛሞች ናቸው በእድሜያቸውም አይበላለጡም ። ከብሩክ ጋር ከብት ይጠብቃሉ ችግሩ ከብቶቻቸው እለት በእለት ወደ መስክ ቢያወጡአቸውም የሰቡ እና የፋፉ አይደሉም እንደውም የጥላሁን ከብቶች በጣም የከሱ ከመሆናቸው የተነሳ ጥላሁን አንዳንዴ ላሞቹን ወደ ቤት የሚያስገባቸው ተሸክሞ ነው።

ጥላሁን የሚኖረው ከቤተሰቦቹ ጋር ነው ከሰፈሩ ሰዎች አንፃር ጥሩ

የሚባል ገቢ አላቸው። ምናልባት ኑሮአቸው ከሌላው የመንደሩ ነዋሪዎች የተሻለበት ምክንያት የመንደር አዋቂ ሎሌ የጥላሁን አጎት መሆኑ ሊሆን ይችላል። ጥላሁን ቀልደኛ ቢጤ ቢሆንም ቁምነገረኛነቱ እና መካሪነቱ ይበልጣል የሚሰጡት ሰራዎችንም በአግባቡ መወጣት መቻሉም ጥላሁን የተጎናፀፈው አንደኛው ሰብዕናው ነው ። በብሩክ አባት አቶ ፈይሴ ብዙ ጥረት ጥላሁን ትምህርት ቢጀምርም አስረኛ ክፍል ላይ በለስ አልቀናውም። ቢሆንም ጥላሁን አስተሳሰቡ እንደ መንደሩ ነዋሪዎች በዘራ እና በመንደሩ አዋቂ የሚመራ አይደለም ብዙ ጊዜም ከብሩክ ጋር የሚግባባበት መንገድም ይህ አስተሳሰቡ ሳይሆን አይቀርም።

ማየት ማመን ነው ወይስ ማመን ማየት ነው ?

የመንደሩ ሰዎች ከዘራ በተቀበሉት ምክር መሰረት አዋቂ የሚል ስም ያለው እና ፊደል የቆጠረ ሰው አይቀበሉም። ምክንያቱም ዘራ አዋቂ ይጠላል አዋቂ በበዛ ቁጥርም ሁሉም የየራሱን መንገድ ስለሚከተል ህብረት እና አንድነት አይኖርም በማለት ዘራ መንፈሱ በአቶ መኮንን አማካኝነት ለመንደሩ ነዋሪዎች አሳምኗቸዋል ለዚህ ነው አብዛኞቹ የመንደሩ ነዋሪዎች

ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ይልቅ ሴቶቹን በቤት ውስጥ ስራ እና ወንዶቻቸውን በከብት ጥበቃነት የሚያሰማሯቸው።

ብሩክና ጥላሁንም ሁሌም እንደሚያደርጉት አጠገብ ላጠገብ ቁጭ ብለው የማህበረሰቡ ልማድ ላይ እየተነጋገሩ ነው።

ጥላሁን ሁል ጊዜ ጥያቄ መጠየቅ ስለሚወድ ብሩክ የሆነ የሰባት አመት ህፃን በውስጡ ያለ ነው ሚመስለው። ለነገሩ ብሩክ መልስ የሌለው ጥያቄ የለም ፤ ችግሩ ከእኛ ከሰዎች አለማወቅ የተነሳ ሊሆን ይችላል እንጂ ምድር ላይ ሁሉም ጥያቄዎች መልስ አላቸው በማለት ያምናል።

"እኔ ምልህ ብሩክ ዞራ ሚባል መንፈስ እኛ መንደር አለ ብለህ ታምናለህ ?" በማለት ለመጠየቅ የማይታክተው ጥላሁን ጠየቀ።

ብሩክም ትንሽ ካሰበ በኋላ "እንዴት መሰለህ ጥሌ ትክክለኛ የሆነውን አስተሳሰብ ለመምረጥ በቅድሚያ ሁለቱ ተቃራኒ ሀሳቦች የሚሰጡን ማስረጃ መቀበልና ድምዳሜ ላይ መድረስ እንችላለን ግን የቀረቡት ማስረጃዎች ግምት ወይም መላ ምት ከሆኑ ተቀባይነት አይኖራቸውም" አለው።

ጥላሁንም "ጥላሁንም ምንድነው ያንተ ማስረጃ? " በማለት ሲጠይቀው ብሩክ በሩጫ ወደ ሌላ እርሻ እየሸሹ የነበሩትን ላሞች ለመመለስ ሄደ።

ከሄደበት ሲመለስ ጥላሁን ያንኑ ጥያቄ ጠየቀው።

ብሩክም "እሺ የእኔ ማስረጃ የሚወሰነው በማየው ነገር እንጂ በማምነው ነገር አይደለም። "አለው የሰባተኛ ክፍል ኬምስትሪ አስተማሪያቸው የመፅሀፉን ትምህርት በቃል ከተማሩ በኋላ የተማሩትን ለመተግበር ወደ ቤተ ሙከራ ተማሪዎችን ይዞ ሲሄድ የሚላቸውን ቃል በመጠቀም።

ብሩክም ይህ አስተማሪያቸው ጉረኛ እና አጉል ደፋር ስለሆነ በአንድ ወቅት በቤተ ሙከራ አስተማሪው የደረሰበት አስደንጋጭ እና ቆይቶም አስቂኝ ሁነት ትዝ ብሎት ብቻውን ከት ብሎ ሲስቅ ነገሩ ያልገባው ጥላሁን እያዋከበ ምን እንዳሳቀው ጠየቀው።

ብሩክም "ሰባተኛ ክፍል ቲቸር ገብረ መድህን "እንዳለው ጥላሁን ከብሩክ ብሶ መሬት ለመሬት እየተንፈራፈረ ሳቀ።

ነገሩ እንዲህ ነው ጥላሁንና ብሩክ ሰባተኛ ክፍል እየተማሩ አንድ ቀን ለተግባር ትምህርት የኬምስትሪ ቤተ ሙከራ ይገባሉ። እናም ከዚህ ቀደም የጥንቃቄ እርምጃ ሳይወስድ የቤተሙከራ እቃዎችን በድፍረት የሚነካካው መምህር ገብረ መድህን አሲድ በውሀ ነው ሚጨመረው ውሀ ግን በአሲድ አይጨመርም በማለት "ማየት ማመን ነው "የሚለው ዲስኩር ከደሰኮረ በኋላ መጨመር ጀመረ በመጀመሪያ አሲዱ ውሀ ውስጥ ሲጨምረው ምንም አልተፈጠረም። አጉል ድፍረት ያለው መምህር ገብረ መድህንም እየጎረረ ውሃው አሲዱ ውስጥ ሲጨምረው የጥንቃቄ እርምጃ ሳይወስድ ክፍት የነበረው እጁ በሰማያዊ እሳት ተያያዘ። ተማሪዎቹም ደንብረው ክፍሉን አይደለም ትምህርት ቤቱ ግቢ ለቀው ወጡ። ከብዙ ማስጠንቀቂያ በኋላ መምህር ገብረ መመድህን ትምህርቱን ቀጥሎ ዛሬ እነ ብሩክ ሆዳቸው እስኪያማቸው የሳቁበት ሁነት ተፈጠረ።

እንደተለመደው አቶ ገብረ መድህን " ማየት ማመን ነው " በማለት እየደሰኮሩ ተማሪውን ከኋላቸው አስከትለው ቤተ ሙከራ ገቡ ።

በወቅቱ የስነ-ሕይወት ቤተ ሙከራ ፅዳት ላይ ስለሆነ ተብሎ በአዋቂ ሰው ቁመትና ስፋት ልክ የተሰራ የሰው ልጅ ሙሉ አካል አፅም ወደ ኬምስትሪ ቤተ ሙከራ ገብቶ የነበረ ቢሆንም ማንም አፅሙን አላስተዋለውም ነበር።

በድፍረታቸው በትምህርት ቤቱ የሚታወቁት መምህር ገብረ መድህንም በጉራ ይህ ኬሚካል ፍሎሮአንቲሞኒክ አሲድ ይባላል የሰውነታችን ቅርፅ ወደ አፅምነት ይቀይረዋል በማለት በብልቃጥ ትንሽ ፈሳሽ ከፍ አድርገው ይዘው ለተማሪው ሲያሳዩ ድንገት እቃው ከእጃቸው ወድቆ ተሰበረ ሁሉም በግርግር እንደ አሲዱና ውሃው ጊዜ ተበታተኑ ።

በወቅቱ መምህር ገብረ መድህን ይወጣሉ ተብሎ ቢጠበቅ ..... ቢጠበቅ.... የሉም ከዛም ተማሪዎቹ ተሰብስበው ጥላሁን ቢሮ ሄዶ እንዲናገር ላኩት ጥላሁንም ቢሮ ሄዶ ለዳይሬክተሩ እየተንተባተበ " ቲቲቲቸር ... ገብረ መመድህን... ላብ ገብቶ እስካሁን አልወጣም "እያለ የተፈጠረውን ነገር ለዳይሬክተሩ እይየተርበተበተ ከተናገረ በኋላ የመሰናዶ ኬምስትሪ አስተማሪ ተጠርቶ በጥንቃቄ ወደ ቤተ ሙከራው እንዲገባ ተፈረደበት።

መምህሩ ወደ ቤተ ሙክራው ሲሄድ ገብረ መድህን ይዞት የነበረው ኬሚካል ከስነ- ህይወት ቤተ ሙከራ የመጣው አፅም ላይ ወድቆ አፅሙ እየጨሰ ነው የፕሪፓራቶሪ አስተማሪውም እየጮኸ ከቤተ ሙከራው ወጣ ተማሪዎቹ እና ሌሎች አስተማሪዎች ምን እንደተፈጠረ ሲጠይቁት የመሰናዶ መምህሩ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ "ገብረመድህን... አሲዱ ተደፍቶበት... አፅም ሆኗል ...አፅሙም እየጨሰ ነው። "በማለት ሲነግራቸው ያለቀሱ ብዙ ተማሪዎች ነበሩ ፤ ለካስ መምህር ገብረ መድህን በተፈጠረው ነገር ከተማሪ ይበልጥ ደንግጠው አስራ አንደኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ጋር ዘለው ገብተው ነበር ።

ከዛ ቀን ጀምሮ መምህር ገብረ መድህን ከስራ ተባረሩ ተማሪዎቹም በመምህር ገብረ መድህን ጊዜ አንዳች አይነት አደጋ ሳይደርስ ከቤተ ሙከራው የማይወጡ ስለነበር በመምህሩ መባረር ምክንያት የቤተ

መከራው ሰያሜ ወደ ቀድሞው ሰያሜው ቤተ ሙከራ እንዲመለስ ተደረገ።

አዲስ የተቀጠረላቸው መምህርም የአቶ ገብረመድህን ተቃራኒ ፈሪ ስለነበር የቃል በቃል ትምህርት አስተምሮአቸው "ማመን ማየት ነው ! "ይላቸውና ከክፍል ውልቅ ይል ነበር።

ይህ ሁኔታ ነው ብሩክና ጥላሁን ሆዳቸው እስኪያማቸው በሳቅ ያፈረሳቸው።

ብዙ ከሳቁ በኋላ ብሩክ በሳቅ ብዛት የፈሰሰውን እንባ እየጠረገ " እና ጥሌ የመንፈሱን ጉዳይ በአቶ ገብረ መድህን ዲስኩር ካየነው መንፈሱ የሰራቸው ነገሮች ልንዘረዝር ብሎም ድምዳሜ ላይ ለመድረስ እንገደዳለን። እንደ አዲሱ የኬምስትሪ አስተማሪያችን ማመን ማየት ነው ካልን ደግሞ እንደመንደሩ ሰው የዞራ መኖር በየዋህነት አምነን ልንደመድም ስለምንችል ለእኔ የአቶ ገብረ መድህን ዲስኩር ይሻለኛል ቢጠቅመኝም ቢጎዳኝም አይቼ እደመድማለው እንጂ አምጄ አልደመድምም።" አለው

ምላሹ ግራ ያጋባው ጥላሁንም አልፎ አልፎ ከሚመጣበት ሳቅ እየተናነቀ እዛው መሬት ላይ በጀርባው ተኝቶ "አቡሽ መንፈሱ እኮ ያወራል እንጂ ሚፈፅሙትማ የኛው የመንደሩ ነዋሪዎች ናቸው " በማለት ቀጠል አድርጎ

"ቆይ ግን ሰው ሁሉ የመንፈሱን ትዕዛዝ አልቀበልም ቢል ምን ሊፈጠር ይችላል ? " በማለት መጠየቅ የማይሰለቸው ጥላሁን ለብሩክ ጥያቄውን አነሳ።

ብሩክም "ያው መንፈሱም ትንቢቱም አስተሳሰብ ነው ብዬ ስለማምን አስተሳሰባቸው ይቀየራል አስተሳሰብ ከተቀየረ ደግሞ ኑሮን ይቀየራል። "

በማለት ነገረው።

ብዙ ከተጨዋወቱ በኋላ ቀኑ ተራውን ለሌሊት ሊለቅ ሲል ላሞቻቸውን በዱላቸው እያቃኑ ወደ መንደራቸው ለመመለሻ ተሰነባብተው ጉዞ ጀመሩ።

ብሩክ አሁንም ቢሆን መንደሩ ተለውጣ የሰዎቹን አስተሳሰብ ተቀይሮ ወደ በረሀነት ሊለወጥ ጥቂት ደረቅ ሳሮች ያሉት የተመናመነው የእርሻ መሬታቸው ለም ሆኖ የተለያዩ ሰብሎች ዘርቶ ከመንደሩ አልፎ በቅርብ ርቀት የምትገኘው ከተማን መግቦ ፤ ትምህርት ቤት ለመንደሯ ተሰርቶ አዲሱን ትውልድ ከድንቁርና መከላከል ፤ ሆስፒታል ተገንብቶ በህክምና መዳን ችለው በበሽታ የሚማቅቁት የመንደሩ ሰዎችን ማዳን እና ሌሎች የማያልቁ ተስፋዎች አሉት።

ግን ብሩክ ትክክለኛ ማንነቱ፣ ህልሙንና ተስፋውን የሚያውቁለት አባቱ ከሁለት አመት በፊት ወደማይቀረው ሄደዋል። እንደ እናቱ የሚያያቸውና እንደ እናቱ የሚንከባከቡት አክስቱም ብሩክን የሚያውቁት በጎበዝ ተማሪነቱ እና ታታሪ ሰራተኝነቱ እንጂ የመንደሩን ልማድ እንደሚቃወም ፈፅመው አያውቁም ።

በአንድ ወቅትም የብሩክ አባት ከሞቱ ባመቱ አክስቱ ለራሱ በማዘን " አባትህ በህይወት እያለ በቡና ማሳውም በእርሻውም ላይ ታች እያለ የእኛን ጉሮሮ ይደፍን ነበር አሁን ግን እርሻው በሽታ ወረረው የቡና ማሳውም እየደረቀ ነው እስቲ ለዞራ ምን ማድረግ እንዳለብህ ጠይቀው እጅ መንሻ ደሞ ይቺን ወይፈን" በማለት ከሁሉም የምትወፍረው ላም እያሳዩ "ይቺን ወይፈን ይዘህ ሂድ ። " በማለት ሲጠይቁት ብሩክ ነገሩን አረሳስቶ ልማዱን ለመከተል በግልፅ አሻፈረኝ ባይልም እንደማይሄድ ቅድመ ሁኔታ አስቀምጦ ነበር ። ያም ቢሆንም ብሩክ ላለመሄድ ያስቀመጣቸው ቅድመ

ሁኔታዎች ከአቅሙ በላይ ሆነው ወደ ሚፀየፈው ልማድ ለመሄድ ቢያስገድዱትም የተለያዩ ዘዴዎችን እየፈለገ ወደ ልማዱ እንዳይገባ ጥረት አድርጓል።

 በአንድ ወቅት በቤቱ ምንም የሚላስ የሚቀመስ እህል ጠፋ የሙት አባቱ አደራ የሆኑት ታናናሽ ውብ እህቶቹም "ራበን!! "እያሉ ብሩክን አስጨነቁት ከዛም በቅፅበት ወደ አዕምሮው የመጣው የአስረኛ ክፍልን በከፍተኛ ውጤት ሲያጠናቅቅ የተሸለመው ከስሩ ሰሙ የተቀረፀበት ውብ እና አብረቅራቂ ዋንጫ ነበር።

እሱን ዋንጫ ይዞ በፍጥነት ወደ ከተማ ገሰገሰ። ገዢ ሲያፈላልግ አንድ ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ በዝቅተኛ ዋጋ ገዙት ገዢዎቹ ግን የሰሙ መኖር ግድ አልሰጣቸውም ነበር ,ይልቁንም ዋንጫው እጅግ የሚያምር ስለነበር ተስገብግበው ነበር የገዙት።

ብሩክም ያቺን ከዋንጫው ትርጉም ጋር ስትወዳደር ጥቂት የሆነችው ገንዘብ ለምግብ ልብስ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እያብቃቃ ለትንሽ ጊዜ በቤተሰቡ ግፊት ወደ መንፈስ ተብዬው ዞራ እንዳይሄድ ሞከረ።

 ሌሎች የጉብዝናው እና የአቅሙ ውጤት መስካሪ የሆኑ ሜዳልያዎቹን ለጌጣጌጥ ሱቅ ከተማ ድረስ በመሄድ እየሸጠ አሁን ያለበት ድረስ ደርሷል። ግን "ነገስ ? " የሚለው ጥያቄ በብሩክ አዕምሮ አስጨናቂው ጥያቄ ነውን

ስለ ነገ በተስፋ እያዘበ የጥንት ከመሆኑ የተነሳ ቁንጫዎች እና ትኋኖች እንደልባቸው የሚንጎማለሉበት የሳር ፍራሹ ላይ ተኝቶ ስለ ነገ ማሰብ ጀመረ

"ነገ በሁሉም ሰው አዕምሮ የሚኖር ያልተጨበጠ ተስፋ ነው ልጆች ነገ

የሚባል ተስፋ ለጨዋታቸው ፤ ወላጆች ነገ የሚባል ተስፋ ለልጆቻቸው እና ለራሳቸው ፤ ነጋዴው ነገ የሚባል ተስፋ ለንግዱ ፤ ሀይማኖተኛው ነገ የሚባል ተስፋ ለእምነቱ ፤ ተማሪዎች ነገ የሚባል ተስፋ ለእውቀታቸው ብቻ ምን አለፋኝ በሁሉም ህይወት ባለው ሰው አዕምሮ ውስጥ ያለ ብቸኛ ተስፋ ነገ ብቻ ነው።" እያለ እንቅልፍ እያባበለ ወሰደው።

በነጋታው ብሩክ ቤት ውስጥ ሁሉም ነገር ሟሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ፤ መች እንደሚሞቱ የማይታወቁ ከሲታ ከብቶቹን ሊያሰማራ ፤ እንደለመደው ከአክስቱ እና ከአጎቱ የማፅናኛ ቃል ተቀብሎ፤ ለሚመጡት ቀናቶች ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ እንዳለበት ለራሱ እየነገረው ከእነ ጥላሁን ደጅ ላሞቹን እየነዳ እየተጣራ ወደ ሰፊው መስክ ሄደ።

ከፈተናው አንዱ

ብሩክ ወደ ደረቀው መስክ ከወጣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጥላሁን እስከ ጉልበቱ የምትደርስ የተቆረጠች ሱሪ ልብሶ የከሱት ላሞቹን እየነዳ ዱላውን እያሽከረከረና እያፏጨ ወደ ብሩክ ሄደ።

ብሩክ አሁንም " ነገስ ምን ሊፈጠር ይሆን ? " የሚለው ጥያቄ አሁንም እያብሰለሰለው ነው። ይህንን ለመረዳት ጊዜ ያልወሰደበት ጥላሁን "አቡሽ ሰላም አይደለህም እንዴ ? ፊትህ ልክ አይደለም ወይስ ቤት የተፈጠረ ችግር አለ ? " በማለት ጥያቄውን አከታተለበት።

ብሩክም ስሜቱን መደበቅ ስላቃተው ያሳሰበውን ነገር ሁሉ አንድ ሳያስቀር ዘረገፈለት።

"ጥሌ ታውቃለህ እኛ ቤት የእኔን እጅ እንደሚጠብቁ ፤ እኔ ደግሞ የቤተሰቡን ጉሮሮ የምደፍንበት ምንም ይህ ነው የሚባል የማገኘው ገንዘብ የለም። ገንዘቡን የማገኘው በደህና ጊዜ ያገኘኋቸው ጥቂት ሜዳልያዎችን እየሸጥኩ ነው። ቤተሰቡ ይተዳደርበት የነበረው የቡና ማሳም ይኸው ደረቅ እንጨት ብቻ ነው ማሳውን የሞላው ፤ ላሞቹም ቢሆኑ ቢሸጡ ይህ ነው የሚባል ገንዘብ አያወጡም ፤ ወተት ከነጠፈባቸውም ዘመናት ተቆጥረዋል እንጃ ጥሌ ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኛል፤ ለእኔስ ይሁን ይራበኝ ችግር የለውም የአባቴ አደራ የሆኑት ታናናሾቹ እህቶቼ ደሞም አክስቴ እና አጎቴስ ፤ አክስቴ እና አጎቴ በሰፈሩ ልማድ ተተብትበው እንኳን ስራ ሊሰሩ 'ዞራ ምንበላው ይሰጠናል በሚል አጉል እምነት' የሚሰራውንም ሰው እንዳይሰራ ጫና ይፈጥራሉ። ጥሌ እኔ ማስበው የቡና ማሳ ላይ ተገትረው የቆሙት እንጨቶችን እሸጥና ጥቂት ገንዘብ እጄ ላይ አለ እሱን ጨምሬበት እህቶቼን ይዤ ከተማ መግባት ነው ምፈልገው።" በማለት ብሩክ ብሶቱን ለጥላሁን ዘረገፈለት።

መላ የማያጣው ጥላሁንም የመፍትሄ የሚለውን ሀሳቡ ሰነዘረ።

"ብሩክ ያለህበት ሁኔታ ሁሉም ሰው ይረዳሀል። በተለይም እኔ። እና የአንተ ችግር ከሰፈሩ ሰው ችግር የሚለየው በዚህ እድሜህ እንደ አባወራ ቤተሰብ የማስተዳደር ሀላፊነት ላይ መውደቅህ ነው። ብሩክ አሁን ወቅቱ ወደ ክረምት እየተጠጋ ነው። በክረምት ወቅት ደግሞ ምናልባት መሬቱ እየተበላሸ ቢሆንም የሆነ ዘር ቢዘራበት ያበቅላል ብዬ አስባለው ። እና ብሩክ የኔ ሀሳብ ከተስማማህ ክረምት እስኪወጣ እዚሁ ቆይ አጎትህንና አክስትህንም ወደ ከተማ እንደምትሄድ እየቆየህ እየቆየህ ለማሳመን

ሞክር። እስከዛሬ ያለህን ገንዘብ እየቆጠብክ ተጠቀም ፤ የቡና ማሳው ላይ የደረቁት እንጨቶችም ለትንሽ ጊዜ ተዋቸው። ማን ያውቃል እስከዛም አንድ መፍትሄ እናገኛለን ። " በማለት ለብሩክ መለሰለት።

ብሩክም ጥቂት አቀርቅሮ ካሰበ በኋላ በእሺታ ፈገግ ብሎ ጥላሁንን ተመለከተው።

እንዲህ እንዲያ እያሉ ቀናት ገፉ የበጋው ወቅትም ጊዜውን ለክረምት አሳልፎ ሊሰጥ ተሰናዳ ፤ ነገር ግን የመንደሩ ሰዎች እንደጠበቁት የክረምቱ ዝናም በቶሎ ሊመጣላቸው አልቻለም። ክረምቱም ደግሞ ሰማዩን ጥቁር ደመና ያለብሰውና የመንደር ሰዎች "ዛሬስ ዝናም ሊዘንም ነው " በማለት ሲጠባበቁ መልሶ ደመናውን ወስዶ ጠራራ ፀሀይ ይለቅባቸዋል።

ብሩክ ይህንን ሁኔታ ሲያይ የ ሰነ-ምድር ትምህርቱ ላይ የተማረው ትዝ አለው። የመንደሩ ሰዎች የሚተዳደሩት የነበረው በነበራቸው ሰፊ ማሳ ላይ ያሉትን ዛፎች በመጨፍጨፍ እሱንም ለማገዶ ፣ ለቤት መስሪያነት ፣ ለጣውላ መስሪያነት በየፈርጁ እያደረጉ ለከተማ ገበያ በማቅረብ ነበር ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም መንደሯ ምትታወቀው ለከተማ እንጨት በማቅረብ ነበር።

ታድያ ይህ ያለ አግባብ ዛፍ መጨፍጨፋቸው ነው የአሁኑን ክረምት ሄድ መለስ የሚያደርገው እንዲሁም ጎርፍ የሚያስከትል ዝናብ በቅርብ ቀን ሊጥል ይችላል የሚል ጥርጣሬ ብሩክ ላይ አድሯል።

ብሩክ ይህንን ይወቅ እንጂ የመንደሩ ነዋሪዎች " ዞራ ተቆጥቷል ምክሩን መቀበል አለብን " በማለት ከአንዴም ሁለት ጊዜ በዝናብ ጉዳይ ዞራ ጋር ቢሄዱም ከሰማይ ምንም ጠብ ያለ ነገር የለም።

አንድ ቀን ብሩክ ከሰፈራቸው ራቅ ባለ ቦታ ላይ ወደሚገኝ ወንዝ ላሞቹን ውሀ ለማጠጣት ይዞ እየሄደ እንደተለመደው ሰማዩ በአስፈሪ እና ጥቁር ደመና ተሸፈነ። ብሩክ ግን ነገሩን እንደከዚህ ቀደም ነው ብሎ በማሰብ ጉዞውን ቀጠለ።

ወንዙም በሁለት አነስተኛ ከፍታ ባላቸው መልከዓ ምድሮች የታጀበ ነበር ብሩክም ከፍታው ላይ በመቆም ወደ ታች ሳይወርድ የሚያሰማራቸው ወደ ሰባት የሚጠጉ ከብቶቹን ከውሀው እንዲጠጡ ለቀቃቸው። ላሞቹን ከለቀቀ ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ሰማዩ ባልተለመደ መልኩ መብረቁን እና ንፋሱን አከታተለው ትንንሽ ጠብታ ዝናም ማንጠባጠብ ጀመረ። ብሩክም ነገሩ የከባድ ዝናም ምልክት መሆኑ ስለገባው ላሞቹን ለመመለስ ቁልቁለቱን በመውረድ ላይ እያለ የተቆረጠ ዛፍ ስር ጠልፎት እየተንከባለለ ወደ ወንዙ ገባ፤ ደግነቱ ወንዙ አልሞላም እንጂ ቢሞላ ኖሮ ሚፈጠረው ከዚህ የከፋ ነበር ።

ብሩክም ከገባበት ውሀ እየወጣ ሰውነቱን ሲያይ ቆዳው ተላልጦ እየደማ ጉልበቱ ላይም በድንጋይ ተመትቶ ከአዋቂ እጅ መዳፍ በጥቂት በሚያንስ መጠን ቆዳው ተገሸልጧል ሰማዩን ሲያይ አስፈሪነቱ እያየለ የደመናው ጥቁረት እየጨመረ ቢሆንም ብሩክ እያነከሰ ወደ ላሞች በፍጥነት ከሄደ በኋላ አንድ በአንድ ከወንዙ እተመላለሰ በማውጣት ላይ እያለ ሰባተኛዋን ላም ከወንዙ ለማውጣት ሲመለስ ጆሮን የሚበሳ ሀገር ምድሩን የሚደበላልቅ ከባድ የመብረቅ ድምፅ ላሞቹን አስደንብሮ በታተናቸው።

የደነበረ እንስሳ መመለስ ከምንም በላይ የሚያስቸግርና ትዕግስትን የሚፈታተን መሆኑ ብሩክ አላጣውም ያም ቢሆን ብሩክ በፍጥነት ወንዙ ጋር የነበረችው ላም ከቁልቁለቱ አውጥቶ እያነከሰ ወደ ተበታተኑት ላሞች ጋር ሲሄድ ዝናቡ ብሶት ይዞት የነበረ ይመስል ሁሉንም በአንድ ላይ

ዘረገፈው።

ብሩክ በዝናብ እየበሰበሰ ወደ መንደሩ አቅጣጫ የሚሄዱትን ትቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ የሚሄዱትን ላሞች ለማምጣት ሲሮጥ ያደረገው በረባሶ ጫማ ተበጥሶ ሁለት ጊዜ ወድቆ ወደ ላሞች ደረሰ። እነሱን በማምጣት ላይ እያለ ሰማዩ የዝናብ አልበቃ ብሎት ምን የሚያካክል በረዶ ማውረዱን ተያያዘው። ብሩክ ላሞቹን ትቶ የመሄድ ሀሳብ መጥቶለት ነበር ነገር ግን የቤተሰቡ ብቸኛ ሀብቶች መሆናቸውን እና የአባቱ አደራ አስቦ ምራቁን ዋጥ አድርጎ ወደ መንደሩ ላሞቹን እየገረፈ ገሰገሰ።

ሰውነቱ ላይ ጣል ያደረጋት ያረጀች ካናቴራ ገላውን የሙጥኝ ብላለች ያደረገው ቱታ መሰል ሱሪም ቅድም በወደቀበት ሰአት ተቀዳዷል ፤ ከዝናቡ ታላቅነት የተነሳ አይኑ የተሸፈነው ብሩክ የሚረግጠው ሁሉ እሾህና ድንጋይ ሆኖበት አንዴ ተደናቅፎ ወደፊት እየተንደረደረ አንዴ እሾህ የውስጥ እግሩን እየበሳ አዘልሎ እያስነክሰው ወደ መንደሩ በስቃይ መገስገስ ቀጠለ ፤ እየደማ ከነበረው የሰውነቱ ክፍል የሚወጣው ደም ልብሱን ቀለሙ እየለቀቀ ያለ ቀይ ልብስ አስመስሎታል ፤ በየመሀሉ ጭንቅላት የሚበሳው በረዶም ስቃዩን አብዝቶታል ብሩክ ግን እነዚህን ሁሉ ችሎ ወደ መንደሩ ሲደርስ በመግቢያው የነበረው የዞራ ዋርካ ስር ላሞቹን አስጠልሎ በዘመናዊ ሁኔታ የተሰራው የሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን በረንዳ ተዘርግፎ ወደቀ።

እየተንፏቀቀም ወደ ግድግዳው በመሄድ የድረሱልኝ ድምፅ አሰማ ነገር ግን ሰሚ ስላጣ ግድግዳውን ተደግፎ እግሮቹን ዘርግቶ ተቀመጠ።

"ለምን እንደዚህ አደረክ ?? " የሚል ቅድም ከሰማው መብረቅ ድምፅ የሚስተካከል ጎርናና ድምፅ ከገባበት ሰመመን ቀሰቀሰው።

ብሩክም ቀና በማለት አይኑን በጨፍጋጋው እየከፈተው ከዝናቡ እኩል የሚንጠባጠቡ ቃላቶቹን እያወጣ "ወን....ዝ...ሄ..ጄ....ዝና...ብ..... "ነገር ግን ያ ድምፅ ብሩክን አቋርጦት ከት ብሎ ሳቀ ብሩክ ነገሩ የሁለት ሰዎች ጭውውት መሆኑ የገባው ቆይቶ ነው። ዝናቡ ከባድ ቢሆንም የሰዎቹ ንግግር ለመደማመጥ እንዲያመቻቸው ከፍ አድርገውት ስለነበር ወሬው ወደ ብሩክ ጆሮ ሰተት ብሎ ይገባል ።

"እኔማ ሰዎቹ የዋህ ስለሆኑ ነዋ!"

"የዋህ ብቻ ?! ምስኪን እንጂ"

"ይኸው ዛሬ በለስ ቀንቶሀል በዝናሙ አመካኝተህ ለምን ሶስት ወይፈን አታስጥልም ?"

" ሶስት ወይፈን ትላለህ ብቻህን ልትበላ ነው ? ባይሆን ጨምረው ይዘው እንዲመጡ ማድረግ ነው"

"ቆይ ግን ዞራ ማን ነው ? ብለው ልጆችህ ቢጠይቁህ ማን ልትላቸው ነው ?"

" ሀሀሀ መንፈስ .... ትልቅዬ ጥቁር መንፈስ .... ሀሀሀሀ!""""

" ሀሀሀሀ"

ብሩክ ሁለቱም ድምፆች ያውቃቸዋል አንደኛው የመንደሩ አዋቂ አቶ መኮንን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የአቅራቢያቸው ከተማ አስተዳዳሪ አቶ ለማ ነበሩ።

ከዚህ በላይ በበረንዳው መቆየት ህይወቱን አደጋ ላይ መጣል መሆኑ ስለገባው ደግሞም ዝናቡ ቀስ በቀስ እያባራ ስለነበር ላሞቹን ይዞ ለመንቀሳቀስ ከተጋደመበት ሲሚንቶ ለመነሳት ቢሞክር አቃተው መላ

ሰውነቱ በቅዝቃዜው የተነሳ ደንዝዞ አላንቀሳቅስ ቢለውም አልሞት ባይ ተጋዳይ እንዲሉ ብሩክ አንዴ በሚያምር መልኩ የተሰራው የበረንዳውን ምሰሶ እየያዘ አንዴ እየወደቀ ከወደቀበት ቀጥ ብሎ በመቆም መንቀሳቀስ ጀመረ።

ወደ ላሞቹ እያዘገመ ሲሄድ ጓደኛው ጥላሁን ለካ ከሩቅ ተመልክቶት ኖሯል በፍጥነት ደረሰበት : በአሁኑ ሰዓት ጥያቄ ማቅረብ ልፋት መሆኑ የተረዳው ጥላሁን ልብስ ደርቦለት ወደ ቤቱ ደግፎ አስገባው ቤት ውስጥም አክስቱ አጎቱ እና እህቶቹ በጥያቄ ጥላሁንን ሲያዋክቡት ግራ የተጋባው ጥላሁን ምንም መልስ ሳይሰጥ የብሩክ ላሞችን ሊያስገባ ወደ ዋርካው ሲሄድ እነ አቶ መኮንን በረንዳ ላይ የነበረውን የሰው ዱካ እና ደም እየተመለከቱ ነበር። ጥላሁን ጊዜ ሳያጠፋ ላሞቹን ወደ እነ ብሩክ ቤት አስገብቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

እንቢ ለእውነት

ብሩክ ለሶስት ቀን ከአልጋ ሳይወርድ ከአካላዊ ህመሙ እያገገመ ቁስሉም

እንደ ውሻ ቁስል እየደረቀለት ነው። ብሩክ የተሰማው ህመም ግን ከእነዚህ ይለያል ለራሱ እንዲህ ሲል ተናገረ "እስካሁን እንዴት?! እንዴት ማህበረሰቡ አልነቃም ?! እንዴት ማሰብ አቃተን ?! በአጉል ጥርጣሬና ፍራቻ ለሆዳቸው ባደሩ ሰዎች እጅ ላይ መውደቃችን ሳያንስ ለእነሱ ቀለብ እና ምግብ መስፈራችን ምን የሚሉት ነው ?! እንዴት አመዛዝነን ማሰብ ተሳነን ?! እነሱ ግደሉ ሲሉን መግደል ፤ እነሱ ሳትሰሩ ተቀመጡ ሲሉን እጅ አጣጥፎ መቀመጥ ምን የሚሉት ድንዛዜ ነው ? በሰው ክፉ አስተሳሰብ እየተመሩ ምንም እንደማያውቅ እንስሳ መሆን ?!" ሌሎችም ሀሳቦች ወደ አዕምሮው ቢመጡለትም አፍ አውጥቶ እንዳይናገር ጥላሁን ወደ ቤት እየገባ ነበር።

ጥላሁን የሆነ አይነት ጥርጣሬ ተፈጥሮበታል ባለፈው ብሩክ ከምመንደሩ አዋቂ ቤት ሲወጣም አይቶታል ምን እንደተፈጠረ ሊጠይቀው ይህችን የብሩክ ከውጫዊ ቁስሉ የሚድንበት ቀንን እየጠበቀ ነበር።

የደህንነቱ ጥያቄ ነበር ጥላሁን ያስቀደመው ፤ ብሩክም ደህና መሆኑንና በቅርቡ ወደተለመደው ስራ እንደሚመለስ ከነገረው በኋላ በመካከላቸው ለረጅም ሰአት ፀጥታ ሆነ። ጥላሁን ንግግሩን እንዴት እንደሚጀምር ሲያስብ የብሩክ አጎት ወደ ቤት ገብተው ስለነበር አልቻለም።

ንግግራቸው ሁሉ ለጠብ የሚጋብዘው የብሩክ አጎትም ለጥላሁን ቆጣ ብለው "አንተ ለምንድነው ዞራ በጠራው ስብሰባ ያልተካፈልከው ? እሱስ ይሁን ህመምተኛ ነው አንተ ምን ልሁን ብለህ ነው የቀረኸው ?" ብሎ ሲጮህበት

የአጎትየውን ባህሪ ጠንቅቆ የሚያውቀው ጥላሁን ተረጋግቶ "ጋሼ ብሩክ እዚህ ብቻውን ትቼው ብሄድ እኮ የሆነ ነገር ሊያጋጥመው ይችላል ብዬ ነው ምናልባት ውሀ ቢጠማው መንቀሳቀስ ስለማይችል እኔ ባቀብለው

ብዬ ነው የቀረሁት" ብሎ ሲመልስላቸው

ከበፊቱ ይልቅ እየተቆጡና እየተናደዱ "አንተ ኩታራ የልጄን ነገር ዞራ ማያገባው ይመስልሀል ? ቢርበው ሊያበላው ቢጠማው ሊያጠጣው ቢበርደው ሊያለብሰው የሚችል ከዞራ ሌላ ማን ይኖራል ጃል ? ይኸውልህ ስማ ለዞራ ምስጋና ይግባውና ዝናቡን እስኪበቃን አዘነበልን እና ከየቤቱ አንድ ወይፈን ግብር ተጥሏል እና ልጁ ስለማይችል ያቺን ቡራቡሬዋን ወይፈን ይዘህ ትሄዳለህ ! ሰማህ ?" ብሎ አጎትየው ከዞራውን ላይ ታች እያደረገ ሲጮህ ጥላሁን በእሺታ አንገቱን ነቀነቀ።

ጥላሁን አጎትየው ሲወጣ ታፍኖ የቆየው ሳቁን ለቀቀ ወደ ብሩክ ሲመለከት ግን ፊቱን አዙሮ የቁንጫ እና የትኋን መናኸሪያ የሆነችው ምስኪኗ መደብ ላይ ጥቅልል ብሎ ተኝቶ ነበር።

ጥላሁንም "አቡሽ ... አቡሽ እያለ ለመቀስቀስ ሲሞክር እንኳን የታመመ ሊመስል ቀርቶ የኮሶ ትል እንዲሸርለት ኮሶ ጠጣ ሰው እንኳ እንደዛ ተስፈንጥሮ አልተነሳም የሆነ ምትሀታዊ ሀይል የገፋው ይመስል ተስፈንጥሮ ሲነሳ ጥላሁን በድንጋጤ ከቤቱ ወደ አንደኛው ጥግ ተወንጭፎ ሄደ

" ምን ሆነሀል ?" በማለት ጥላሁን ጠየቀው

"እስቲ አስታውስ እዚህ ቤት ከዚህ ከይሲ መንፈስ ግብር በፊት ስንት ከብቶች ነበሩን ?" በማለት የአጎቱን አይነት ቁጣ ተቆጥቶ ጠየቀው

ጥላሁንም እንደምንም ተረጋግቶ ወደ እሱ እየተጠጋ " ቢያንስ ቢያንስ ከአርባ በላይ"

"አሁንስ ?!" በማለት በቁጣ ጠየቀው

"ሰባት "

"አየህ መንፈስ የሚባል ነገር የለም ፤ ሁሉም ሌቦች ናቸው፤ ሁሉም ውሸታም ናቸው ፤ ሁሉም ... ሁሉም አንድ ናቸው " እያለ ላይ ታች በማለት አወራ ነገር ግን የህመሙን ስሜት ሊቋቋመው ስላልቻለ መደቡ ላይ እጥፍጥፍ ብሎ ወደቀ።

ጥላሁንም ምን እንደተፈጠረ ለመጠየቅ ከዚህ ሌላ አሪፍ ጊዜ እንደሌለ ስለገባው የታጠፈውን እግሩን እያስተካከለለት

"ምንድነውየተፈጠረው ከባለፈው ዝናቡ ከደበደበህ ቀን ጀምሮ ባህሪህ ተለውጧል ፤ ከጉዳቱ ነው እንዳልል ከዚህ የበለጠ ብዙ ነገር አጋጥሞሀል ደግሞም የዛ ቀን ከእነ አዋቂው ቤት ነው እያነከስክ የወጣኸው የተፈጠረ ነገር ካለ ለምን አትነግረኝም ? " እያለ እንዲነግረው እንደ ህፃን እያባበለ ጠየቀው

ብሩክም ቅድም የመጣበት የቁጣ ሀይል እየረገበለት "ጥሌ ጮህኩኝ አደል ? ይቅርታ " እያለ አይን አይኑን ሲያየው

ጥላሁን ተረጋግቶ "እሱን እርሳው ምን እንደተፈጠረ ብቻ ንገረኝ " ብሎ ሲመልስለት ለመስማት እንደጓጓ ያሳብቅ ነበር

ብሩክም ያን ቀን ያሳለፈውን ሁሉ አንድ ሳያስቀር ዘረገፈለት ከወንዙ ቦታ እስከ እነ መኮንን ቤት ያየውን እና የሰማውን ነገረው።

ጥላሁን የእነ መኮንን ንግግር ሲሰማ ውሸት ነው ብሎ አሰቦ ነበር ነገር ግን ብሩክ አንድም ቀን ውሸት የሚባል ተናግሮ ስለማያውቅ ሳያንገራግር አመነው።

ጥቂት ቆይቶ በውስጠኛው እልፍኝ የነበሩት ከብቶች ደነበሩ እርስ

በእርሳቸው እንግዳ ድምፅ እያሰሙ ሲረበሹ ጥላሁን ምን እንደተፈጠረ ለማየት እያዘገመ ሲሄድ አንድ ጠብደል ጅብ ከሁሉም አነሰ የምትል ላምን ይዞ እየሄደ ነበር ጥላሁንም በፍጥነት ወደ ብሩክ ተመልሶ አንተ ከዚህ እንዳትንቀሳቀስ እያለው በመጣበት መንገድ ከጓሮ በኩል ሲወጣ እግሩ ስር ጉማጅ አጠና ያገኝና ላሚቱን እየጎተተ የሚሄደውን ጅብ ያሳድደዋል የእነ ብሩክ ማሳ ለጥ ያለ ስለሆነ ለጅቡም ለጥላሁንም ተመችቷቸው እየሮጡ ነው ጥላሁን በጨረፍታ ወደ ኋላ ሲያይ የብሩክ አጎትና ሌሎች ሶስት ሰዎች ከኋላው እየተከተሉት "በለው ... በለው እንዳይገድላት በያዝከው እንጨት በለው.. ወርውርበት..." እያሉ እየጮሁ ይከተሉታል ጥላሁን ግን "እንጨቱን ከወረወርኩት በኋላ የሳትኩት እንደሆነ ለኔም አደል ጉዳቱ ?" እያለ አሰቦ እንጨቱን ከመወርወር ይልቅ ፍጥነቱን ጨምሮ ተጠግቶ መምታት አሰበ እንዳሰበውም ስለደረሰበት ወደ ጅቡ ጭንቅላት ተጠግቶ ያለውን ሀይል በሙሉ በመጠቀም የያዘው ጉማጅ አሳረፈበት።

እንጨቱም የጅቡን ጆሮ ግንዱን ሲለው የያዛትን ላም ጥሎ ነፍሱን ለመታደግ እግሬ አውጪኝ አለ። ከላሚቷ እንጂ ከጅቡ ጉዳይ የሌላቸው አሳዳጆች ጅቡን ከማባረር ተመልሰው ላሚቷን ከበው አዩአት ነገር ግን ጅቡ በሚጎትታት ወቅት አንገቷን ይዞ ስለነበርና ብዙ ደም ስለፈሰሳት በህይወት መቆየት አልቻለችም።

ብሩክ ምን ተፈጥሮ ይሆን በማለት እያሰበ ሳለ ጥላሁን እያዘገመ ወደ

ብሩክ መጣ

'ምን ሆናችሁ ነው አንተ እንዳትንቀሳቀስ ብለኸኝ ሄድክ አጎቴ እና የሆኑ ሰዎችም እየሮጡ ተከተሉህ ምን ሆናችሁ ነው ?" በማለት ጠየቀው።

ጥላሁንም በአንድ ቃል "ሞተች!" አለው

ብሩክም ግራ ተጋብቶ ሁለቱን እጆቹ እንዳልገባው ሰው እያጠፈ "ማን?"

"ላሚቱ" ሲለው በመካከላቸው ፀጥታ ሰፈነ

ጥላሁንም ማብራሪያ ለመስጠት "ደርሼበት በእንጨት ጆሮ ግንዱን ብዬው..." ብሩክ አላስጨረሰውም

"አጎቴ የት ነው ?" ቆጣ ብሎ ጠየቀው

"እታች ላሚቷ ጋር ናቸው " ሲለው "ውሰደኝ ላናግረው እፈልጋለው " ብሎት ከተኛበት ከወገቡ ቀና አለ

ጥላሁንም "መውሰዱን እወስድሀለው ግን ምን ልትለው ነው" አለው ጥላሁን ከቆመበት ቦታ ሳይንቀሳቀስ

" ምን ቸገረህ ውሰደኝ !!" ብሎ አምባረቀበት

ጥላሁንም "እሺ ግን ምንም ነገር እንደማይፈጠር ቃል ከገባህልኝ እወስድሀለው " አለው

"ምንም አይፈጠርም ቃል እገባልሀለው "

ጥላሁንም ተጠግቶት በትከሻው አስደግፎት እያዘገሙ ወደ ሰፊው ማሳ ወጡ ።

ጥላሁን የሮጠበት ዱካ የጅቡ ዱካ ከዛም የአራት ሰው ዱካ ባለፈው

በወረደው የዶፍ ዝናብ ምክንያት ደለል በያዘው በተንጣለለው እርሻቸው ቁልጭ ብሎ ይታያል።

ብሩክ ህመሙ ጠንቶበት እነ አጎቱ ያሉት በኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ሆኖ ታየው። ጥላሁን ግን የብሩክን ግማሽ አካል ተሸክሞ ያዘግማል

"ቆይ ጥሌ " ብሩክ ተናገረ

"ምነው አመመህ ?" ሲል ጠየቀው

"አይ በቃ ወደ ቤት መልሰኝ"

ቀናት እየተቆጠሩ ሲሄዱ ብሩክም ከህመሙ ሙሉ በሙሉ እያገገመ ነበር ያለ ማንም ድጋፍ መንቀሳቀስ ችሏል አልፎ አልፎ የሚጥለው ከባድ ዝናብም ጎርፍ ወደ ቤታቸው እያስገባ ተቸግረዋል በተለይ ዝናሙ በውድቅት የሚዘንም ከሆነ ለቤተሰቡ ብሎም እንደነ ብሩክ አይነት የመንደሩ ነዋሪዎች አሳራቸውን ያበላቸዋል መኝታቸው የሳር ከመሆኑ የተነሳ አንድ ቀን ውሀ ከነካው ርጥበቱ እና ሽታው አያድርስ ነው። ይህም እየሆነ ግን ብሩክ በቀጣይ ቀን በጥላሁን ምክር እርሻውን ተመልክቶ ምን አይነት ሰብል እንደሚያበቅል ለማየት እና ቤት ውስጥ በህመም በቆየበት ጊዜ አደጋ ላይ የወደቀው የቤታቸው በልቶ ማደርን ለመግታት ጥቂት ነገር ለመገዛዛት ወደ ከተማ ከጥላሁን ጋር ለመሄድ አስቧል።

"ጥላሁን ... ጥሌ ... ጥላሁን "ብሩክ ነበር ወደ ጥላሁን ቤት ደጅ ላይ ቆሞ ሚጣራው ጥላሁንም በግራ እጁ የላሞች ማሰሪያ ገመድና በቀኝ እጁ ረጅም ማጭድ ይዞ ብሩክ ወዳለበት ሲመጣ ፊቱ ላይ የደስታ ምልክት ይታይበት ስለነበር ብሩክም ፈገግ አለ ፤ ብዙ ጊዜ በሱ ድጋፍ ነበር የሚንቀሳቀሰው አሁን ግን ከፊት ለፊቱ ቆሞ እየጠራው ነው። ጥላሁን የብሩክ ከህመሙ ማገገም አስገርሞት በዙርያው እየተሸከረከረ በአግራሞት አንዴ እግሩን አንዴ ጭንቅላቱን እያየ "ቁስልህ የውሻ ቁስል ሆኖ የለ!" አለው ማየቱን ለአፍታ ገታ አድርጎ አይኑን ትኩር ብሎ እየተመለከተው ።

"አዎ ጥሌ አሁን ድጋፍ አያስፈልገኝም ሸ በማለት የምፀት ሳቅ ስቆ "እረ ሰላም በለኝ" አለው ተቃቅፈው ሰላም ከተባባሉ በኋላ ጥላሁን ወደ ብሩክ ትከሻ እያመለከተ ሲስቅ ብሩክም ነገሩን ሊያይ ዞረ ላካስ ጥላሁን የያዘው ገመድ ላይ የከብቶች አዛባ እንደነበረበት ሳያስተውል ነበር ያቀፈው። ሁለቱም ተሳስቀውና ጥቂት ተተራርበው ብሩክ እርሻው ላይ መዝራት ያለበት ነገር እንዲያማክረውና ከተማ አብሮት እንዲሄድ ሲጠይቀው ጥላሁን ፈቃደኛ ስለሆነ ልብሳቸውን ሊቀይሩ ወደየ ቤታቸው ገቡ።

ማለቂያ ያለው የማይመስለው የአባቱ ውርስ ሰፊው ሜዳ ላይ እሱና ጥላሁን ላይ ታች እያሉ ምን እንደሚዘራበት ያወራሉ

ጥላሁን "እንደሄ አስተያየት በቆሎ ብንዘራበት የተሻለ ይመስለኛል ለምን መሰለህ ይሄ አፈር ጥልቀት ስለሌለውና ደለል ስለሆነ ስራቸው ወደ

ውስጥ የሚጠልቁ ሰብሎችን አይቀበልም በቆሎ ግን ስሩ ወደ ታች እምብዛም አይጠልቅም "እያለ ለማሳመን እጆቹን ወደ መሬቱ እየከተተ አፈሩን ዝቆ እየበተነ ተናገረው

ብሩክም "በቆሎ ብንዘራበት ጥሩ ነበር ግን በቆሎ ጥሩ እና የተደላደለ አፈር ይፈልጋል ይሄ አፈር ደግሞ እንደምታየው ለስላሳ ነው በቆሎ ዘርተን ቢበቅል እንኳ ንፋስና ጎርፍ ሲመጣ ይነቃቅለዋል" እያለ አፀፋዊ ምላሽ ሰጠው

"እሺ ሌላ ምን ትዘራበታለህ ? "

"አላውቅም እስቲ ወደ ከተማው እንውጣና እዛ ያሉት ዘሮችን እንይ ከዛም ለአፈሩ እና ለአየር ሁኔታው የሚስማማውን እንመርጣለን" ብሎ ብሩክ ሲመልስለት ጥላሁን አንገቱን ወደ ትከሻው ዘንበል እያደረገ እሺታውን ገለፀለት።

ወደ ከተማም ለመድረስ ብዙ ቢጓዙም ሳይረፍድ ነበር የደረሱት ጥላሁን አዘውትሮ ወደ ከተማው ቢመጣም ብሩክ ግን ከትምህርት ቤቱ አስቀያሚ ትዝታ ወዲህ ለዋንጫው እና ለአንዳንድ ሜዳልያዎቹ ሽያጭ በስተቀር እንደ ጥላሁን አዘውትሮ ከተማዋን ረግጧት ስለማያውቅ በሁለት አመት ውስጥ የሚያስተውላቸው ትልልቅ ለውጦች ነበሩ የተንጠለጠሉበት ብረት አይን የመማርከው የመንገድ ላይ መብራቶች ፣ ከስራቸው ሆኖ ወደ ላይ ለማየት የሚጥር ሰውን አንገት የሚሰብሩ ትልልቅ እና ሰፋፊ ህንፃዎች ፣ እቃ ለመግዛት አላማ የሌለውን ሰው እንዲገዛ የሚጠሩ ዘመናዊ ሱቆች ፣ በመንገዱ የሚንጎማለሉ ውብ መኪናዎች ፣ ለመርገጥ የሚያሳሱ እና የሚያማምሩ መንገዶች ፣ ከመጣበት መንደር ሲተያይ ሰማይና ምድር የሆነው የነዋሪዎቹ አለባበስ ፣ በተለያዩ ድምፅ ማጉያዎች የባለቤቶቹን እምነት የሚያንፀባርቁ መዝሙሮችና መንዙማዎች ብቻ ምን አለፋችሁ

በሁለት አመት ውስጥ ከተማዋ ውብ እና ድንቅ ሆና ነበር የጠበቀቻቸው።

ብሩክ በዚህ እየተደነቀ እያለ ወደ ገበያው መግቢያ ስለደረሱ ትኩረቱን ሰብስቦ የሚገዛቸውን እቃዎች ማሰላሰል ጀመረ። ረጅም ጊዜ የሚቆዩ እና በቶሎ የማይበሰብሱ ምግቦችን ከገዙ በኋላ ለእርሻው የሚሆን ዘር የሚገዙበት ቦታ እንዲያሳየው ጥላሁን ለብሩክ ስለጠየቀው ወደዛ እያመሩ ሳለ ብሩክ መንገድ ዳር የተፃፉ ማስታወቂያዎችን በገረፍታ ይመለከት ነበር።

ወደ ነጋዴዎቹም እንደደረሱም በጣት ከሚቆጠሩ ነጋዴዎች በስተቀር ሁሉም ነጋዴ የሚሸጠው ለዘር የሚሆን በቆሎ ስለነበር ሁለቱም ተያይዘው ወደሌሎች ነጋዴዎች ሄዱ ማሽላ ፣ ሰሊጥ እና ዳጉሳ ብቻ ስለነበሩ ያላቸው አማራጭ የበቆሎ ዘር መግዛት ነበር። የተሻለው የበቆሎ ዘር በአይናቸው ከመረጡ በኋላ ጥላሁን ወደ ነጋዴው ዞሮ በቆሎው በነቀዝ መበላቱን እና አለመበላቱን ለማረጋገጥ ወደ አፉ ልኮ በፊት ጥርሶቹ እየጨፈለቀ ካየ በኋላ የሚበቃውን ያክል እንዲገዛ ለብሩክ ለመንገር ሲዞር ብሩክ አጠገባቸው ባለ የመብራት ገመድ ምሰሶ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያ ትኩረት ስቦት ምን እንደተናገረ አልገባውም ነበር ጥላሁን ወደ ብሩክ ቀረብ ብሎ ማስታወቂያውን አብሮት አነበበው "ለትምህርት ፈላጊዎች በሙሉ ..." እያለ የሚቀጥል በቢጫ ወረቀት ተፅፎ በጥቁር ቃላቶች የተከሸነ የአስተዳደር ትምህርት በዲፕሎማ ለስድስት ወር የሚያስተምር ማስታወቂያ ነው ብሩክ አይኑን ከማስታወቂያው ነቅሎ የምዝገባ ጊዜ እና ቦታ የሚለውን ሲያነበው ለምዝገባ የቀረው አንድ ቀን ብቻ እንዲሁም ቦታው የእነ ብሩክ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ስለሆነ ጊዜ ሳያጠፋ መሄድ እንዳለበት ለራሱ ነገረው።

ለጥላሁንም ተቻኩሎ "እንሂድና እንመዝገብ " ሲለው "በቆሎውስ?"

በማለት ጥላሁን የተቻኮለውን ብሩክ በአግራሞት እያየው ጠየቀው።

ብሩክ ቢቻኮልም ከቤቱ የወጣበት ጉዳይ ፈፅሞ መጨረስ እንዳለበት ስለገባው የእርሻ ቦታቸው ሩቡን ያክል የሚሸፍን በቆሎ ገዝተው ወደ ትምህርት ቤቱ ለምዝገባ ሲያቀኑ ብሩክ ፈጠን ብሎ ይሄድ ስለነበር ጥላሁን አባቱ እንዳመለጠው ህፃን ልጅ በሩጫ ይደርስበትና አብሮት ይሄዳል አሁንም የጥላሁንና የብሩክ እርምጃ ስለማይጣጣሙ ትቶት ይሄዳል ጥላሁንም በሩጫ ይከተላል እንዲህ እንዲያ እያሉ ወደ ትምህርት ቤቱ ደረሱ።

ወደ ትምህርት ቤቱ ሲደርሱም ሰራተኞቹ ለምሳ ወጥተዋል ስለተባሉና የትምህርት ቀን ስላልነበር በቅጥር ግቢው በሚገኝ በቅንጦት የተሰራ የሚመስል ነገር ግን ትንሽ ወጪ የወጣበት ከሀያ ሰው በላይ ወደሚይዘው የቀድሞ የተማሪዎች ክበብ የነበረው ጎጆ ገብተው እስከሚመጡ መጠበቅ ጀመሩ።

ብሩክ በዚህ የተማሪዎች ክበብ የአስረኛ ክፍል እያለ የተዋወቃትና የዛው ከተማ ነዋሪ የሆነች እሱ አስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤት ሲበላሽበት እሷ ግን አሪፍ የሚባል ውጤት አምጥታ በስም ብቻ ወደሚያውቃት አዲስ አበባ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የገባችው የደስ ደስ ያላት እና የቀይ ቆንጆዋና ቀጭኗ ሀሮት ትዝ አለችው። ከሀሮት ጋር ብዙ ነገር አብረው አሳልፈዋል ፤ ወደ ቤታቸውም ለአንድ በአል መጠራቱን ያስታውሳል ፤ አባቱ የሞተ ጊዜም ከአንዴም ሁለት ጊዜ በመሄድ ሀዘኑን ገልጣለታለት እንዲበረታ ነግራዋለች ፤ ውጤት ለማየት መጥቶ ግራ ገብቶት ጭንቅላቱን ይዞ የወጣ ጊዜም ለረጅም ርቀት እየተከተለች ሰሙን እየጠራች ስታለቅስ እንደነበር አስታውሷል።

"ሀሮት" አለ ብሩክ በረጅሙ ተንፍሶ

ጥላሁን አስረኛ ክፍል በነበረ ጊዜ እንዲሁም ለአባቱ ለቅሶ ከተወሰኑ የክፍሉ ተማሪዎች ጋር መጥታ ስለነበረ ያውቃታል "ሀሮት ምን ..." በማለት ሲመልስለት ድምፁን ከፍ እንዳደረገ ያላስተዋለው ብሩክ እየተንተባተበ "ማን ... ሀሮት የት አለች "እያለ ሲደነባበር ጥላሁን ሰቆ ወደ ቢሮ መዝጋቢዎቹ መምጣት አለመምጣታቸውን ለአፍታ ተመልክቶ "አቡሽ ለምንድነው ምትመዘገበው "ሲል ቅድም ቢጠይቀው የማይመልስለት ጥያቄ ጠየቀው

"ጥሌ ታውቃለህ ልክ ማስታወቂያውን ሳነበው ውስጤ አንዳች አይነት ነገር ወረረኝ ማስታወቂያውን ካነበብኩ በኋላ በማስታወቂያ ወረቀቱ ተለጥፎ የማየው የአባቴን ምስል ነበር ፤ በቃ ህልሜ ይህ ሳይሆን አይቀርም እድሌን ልሞክር ብዬ ነው "በማለት ሲመልስለት ጥላሁን አንገቱን አቀርቅሮ ምላሽ ሊሰጠው ሲዘጋጅ የስልጠናው መዝጋቢዎች እንደመጡ የቢሮው በር ሲከፈት አወቁ።

ይዘው የነበረው እቃ የግቢው ጥበቃ ጋር አሥቀምጠው ወደ ቢሮ ከገቡ በኋላ ለመመዝገብ እንደመጡ ጥላሁን ቀደም ብሎ ሲናገር መዝጋቢዎቹ እንዲቀመጡ እየነገሯቸው የተመዝጋቢ ቅፅ እንዲሞሉ ሰጧቸው።

ሁለቱም ቅፁን እየሞሉ ድንገት ብሩክ በድንጋጤ ጥላሁንን ሲያየው ጥላሁን ቀድሞ አይቶት ብሩክን ምላሽ እየጠበቀ ስለነበር አይን ለአይን ተፋጠጡ ሁለቱም አይናቸው እስኪወጣ የተፋጠጡበት ምክንያት የመመዝገቢያ ወረቀቱ ላይ በየወሩ ለትምህርት የሚከፈል የአንድ ሺህ ብር ክፍያ ነው።

ጥላሁን በአይኑ እንዲወጡ እየጠቆመው ከተቀመጠበት በመነሳት "ይቅርታ የወርሀዊ ዋጋውን አላየንም ነበር ይቅርታ" እያለ ሲወጣ ብሩክ በልመና መዝጋቢዎቹን መለማመጥ ተያያዘው መዝጋቢዎቹ እሱን መርዳት

እንደማይችሉ ሲነግሩት ጥላሁን ደግሞ ብሩክን ይዞ ሲያስወጣው ያኔ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ግርማቸው በግርግሩ መሀል ገብተው "ምን ሆናችሁ ነው ? " በማለት ለሰራተኞቹ ተናግረው ወደ እነ ብሩክ ሲመለከት ብሩክን ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም የባለፈው ጉዳት ፊቱን ቢሞነጫጭረውም አቶ ግርማቸው ለመለየት አልከበዳቸውም "ብሩክ?" በማለት ተገርመው እያዩት ብሩክ ያኔ ከሁለት አመት በፊት የነገሩት መርዶ እና የዛሬው መጥፎ እድል ሆድ አስብሰው "ቲቸር ግርማ እባኮትን እንድማር ያድርጉ ?" በማለት እግራቸው ሰር ተደፍቶ እንባውን ሲለቀው ፈርጣማ ሰውነት ያለው አቶ ግርማቸው "ብሩክ ምን ሆነሀል?" እያሉ ከመሬት አንስተው ህፃን እንደምታባብል እናት ብሩክን በቦርጩ እየገፋ በእጁ እየሳበ ጀርባውን መታ መታ እያደረገ "አይዞህ ...አይዞህ " እያለ አባብሎ ለጥላሁን እዚሁ ጠብቀው ብሎት አቶ ግርማቸው ብሩክን ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮው ይዞት ገባ።

ህልም እንጀራ ሲሆን

ብሩክ ከዳይሬክተሩ ቢሮ ቅድም እያለቀሰበት የነበረው ጨፍጋጋ ፊቱ እንደ መስከረም ወር አደይ ፍክት ብሎ ወደ ጥላሁን ሲመለስ ዳይሬክተሩን አስከትሎ ነበር።

"ይህ የነፃ የትምህርት እድል የመጨረሻው ቅፅ ነው ሙሉ መረጃው ከኮድ ቁጥር 4321 አውጥታችሁ በዚህ ቅፅ አስፍሩት ለእኛ አይደለም ለሀገር የሚጠቅም ልጅ ነው" በማለት አቶ ግርማቸው ለመዝጋቢዎቹ ሶስት ጥራዝ ወረቀት ሰቷቸው እነ ብሩክን ይዟቸው ከቢሮው ወጣ።

አቶ ግርማቸው አመራርነትን ጠንቅቀው ያውቃሉ "ትንሽ ወጪ ብዙ ስራ" የሚለው አመለካከታቸው አንዳንድ የትምህርት ቤቱ አካላትን ባያስደስትም ለትምህርት ቤቱ ግን ቁልፍ ስራ የሰሩ የጥበብ ሰው ከመሆናቸው በላይ በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነትን አግኝተዋል።

አቶ ግርማቸው ዘበኛው ጋር ያስቀመጡትን እቃ እንዲይዙ እያገዟቸው ከግቢው ተከትለዋቸው በመውጣት በሁለቱም ትከሻ ላይ ወፍራም እጃቸውን አሳርፈው

"በሉ ልጆች እኔ ስራ አለብኝ እናንተ ጊዜው ሳይረፋፍድ ቶሎ ተመለሱ" እያሉ መጀመሪያ በጥላሁን የሱሪ ኪስ ቀጥሎም በብሩክ የሱሪ ኪስ ገንዘብ እየጨመሩ በነበረ ጊዜ ጥላሁን አልቀበልም በማለት ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ጥሮ ነበር ነገር ግን ብሩክ የአቶ ግርማቸው በጎነት እያሰላሰለ ስለነበር ያለምንም ችግር አስገብቶለት ለብሩክ ትምህርት የሚጀመርበት ቀን ደጋግሞ እየነገረው ወደ ኋላ ተመለሰ።

"አንተ ምን አይነት ደግ ሰው ናቸው ቅድም ስታለቅስ አባበሉህ ገና የነፃ የትምህርት እድል አሰጡህ ገና ደሞ አሁን ገንዘብ ሰጥቶ ሸኘን" እያለ ከብሩክ ቀደም ብሎ እየሄደ ከገበያ የገዙትን ዘር በትከሻው ተሸክሞ ወደ

ኋላ ዞሮ አይኑን እያየው ለአቶ ግርማቸው ያለውን አድናቆት ገለፀለት።

ብሩክም ጊዜያዊ ፈገግታ በማሳየት "በጣም ጥሩ ሰው ናቸው" አለው

ጥላሁንም ከዚህ በላይ ደስታ ምን ጠብቆ ነው እስካሁን ሊደሰት ያልቻለው በማለት "ደግሞ ምን ቀረ ልትል ነው ፊትህን የጣልከው ?" እያለ መልሱን በአዕምሮው በቅፅበት ፈለገው ግን ሊያገኘው ስላልቻለ ያለው አማራጭ ከብሩክ የሚወጣው መልስ መጠበቅ ብቻ ሆነ።

"አንተ ! አንተ ነህ የቀረኸው እኔ በነፃ የትምህርት እድል ስማር አንተ መንደር ያሉት ከብቶች ጋር ልትታገል ነው ? ወይስ ዘር የማይሰጠውን እርሻውን ልትታገለው ነው ? " በማለት ሲመልስለት እውነትም ለጥላሁን እንዳሰበ ያስታውቅ ነበር

ጥላሁንም ፈገግ እያለ "ይሄ ነው ያስጨነቀህ ? አታስብ ሁሉም ለአጎቴ አሳምጄ እነግረዋለው እሱ ካልፈቀደም እኔ ጋር ጥቂት ገንዘብ አለ እሱን አብቃቅቼ እማራለው አታስብ ብቻ አንተ በርታ መንደሯ ካንተ ብዙ ትጠብቃለች አሁን ትምህርትህን አስብ" ብሎ ሲመልስለት

ብሩክ ግራ በመጋባት "ታድያ የምዝገባው ጊዜ እኮ ዛሬ ነው የሚያልቀው " ብሎ ሲጠይቀው ከሚሄደው መንገድ ቆም ብሎ ነበር።

ጥላሁንም በነገር ለመንካት " ምድር ላይ ያንተ የዲፕሎማ ትምህርት ብቻ ነው እንዴ ያለው ?" እያለ ሲቀልድበት ብሩክ የጥላሁን አላማ ሌላ ትምህርት መማር እንደሆነ ስለገባው በቀልዱ እየሳቀ ወደ መንደራቸው አቀኑ።

ወደ ቤቱ ከደረሰ በኋላ በማታው ቤተሰቡ ተሰብስቦ ሳለ ቀጣይ ሳምንት ስለሚጀምረው የነፃ የትምህርት እድል ለቤተሰቡ አካላት ሲያጫውታቸው ከአክስቱ ዘንድ ማበረታቻ እና ማፅናኛ ቃል ቢያገኝም አጎቱ ግን ከዞራ እና

ከአቶ መኮንን ያላቸው ቁርኝነት ከፍተኛ ስለነበረ የብሩክ ድጋሚ ወደ ትምህርት መመለስ አላስደሰተውም ሁለቱ መንትያ እህቶቹም ቢሆኑም መመኪያቸው የሆነው እና ራበን ሲሉ ከየትም እያመጣ የሚመግባቸው ብሩክ ለስድስት ወር ከእነሱ መለየቱ የልጅ ነገር ሆኖባቸው እንዳይሄድ ተማፅነውታል ብሩክ ግን ከሁለቱ እህቶቹ አስቀድሞ አጎቱን ለማሳመን ጥረት ካደረገ በኋላ ስለተሳካለት ወደ መንትያ እህቶቹ ሄዶ ማባበሉን ጀመረ።

ነፍሷን ይማረውና የብሩክ እናት ያረፈችው እነዚህን ውብ መንታዎችን በመንደሩ አዋላጅ በቤቷ ውስጥ ስትወልድ ነበር ምንም እንኳ ብሩክ ያኔ የሰምንት አመት ልጅ ቢሆንም የእናቱ ሞት እና መልክ እስካሁን ያስታውሰዋል ። ብሩክ ግን ግርም የሚለው ቤተሰቦቹ ለምን ይህን ያክል አመት ልጆች ሳይወልዱ እንደቆዩ እስካሁን ግራ ይገባዋል።

ወደ ልጆቹ ተጠግቶ የተለቀቀው ረጅም ፀጉራቸውን እየደባበሰ የድምፁን ቅላፄ እየቀየረ ፤ አዕምሮአቸውን ተስፋ እየሞላ ፤ ማባበያ ቃላትን እየተጠቀመ በመሄዱ ከማዘን ፈንታ እንዲደሰቱ አደረጋቸው።

በዚህ መሀል ብሩክ አንድ ሀሳብ ወደ አዕምሮው መጣለት "ግን ለምን ለህፃናት የማባበያ ቃላትን ተጠቅሜ ለአጎቴ ግን ማሳመኛ የተጠቀምኩት ?" በማለት ለራሱ ሲጠይቅ መልሱን ቶሎ ነበር አዕምሮው ያቀበለው "ምክንያቱም ህፃናት ያልዳበረ ነገር ግን በቶሎ የሚዳብር ጭንቅላት ስላላቸው በሽንገላ ይታለላሉ አዋቂዎች ግን ህይወት ብዙ ስላስተማረቻቸው የሽንገላ ወይም የማባበያ ቃላት አይጥማቸውም ይልቁንም ጭንቅላታቸው የዳበረ ስለሚሆን የማባበያ ሳይሆን የማሳመኛ ቃላትን መቀበል ስለሚወድ ይሆናል ።" በማለት የአዕምሮውን መልስ አሰላሰለው።

በነጋታው ብሩክ ከገበያ የገዛውን የበቆሎ ዘር ለመዝራት ወዳ ሰፊው እርሻ ሲወጣ አጎቱ ለመከተል አስበው ድካማቸውን እና መስራት አለመፈለጋቸው በቤት እንዲቆዩ ስላስገደዳቸው ብሩክ ብቻውን ለመዝራት አነስተኛ የሳር ማጭድ እና በከረጢት የታጨቀውን የበቆሎ ዘር ይዞ ወጣ።

መሬቱን በማጭዱ ጠለቅ አድርጎ መሬቱን እየወጋ በክፍተቱ በቆሎውን እየከተተ ባለፈው ከወንዝ ሲመለስ ያጋጠመው የሀገሬው አዋቂና የከተማ አስተዳዳሪ የነበረው ሰው የተነጋገሩትን ማሰላሰል ጀመረ "ዞራ የሚባል መንፈስ እውነትም ከሌለ ይህ ሁሉ ሰው ለምን ሆ ብሎ ይከተለዋል ? ወይስ ያኔ አሞኝ ስለነበር እራሴ የተናገርኩትን ድምፅ ነው እንደዚህ የሚያውከኝ? አይ አይሆንም ሰምቻለው ተናጋሪዎቹ ራሳቸው አቶ መኮንን እና አስተዳዳሪው ናቸው ፤ ታድያ እኔ ዝም ብዬ መቀመጥ አለብኝ ? ፤የመንደሩ ሰዎችንስ ነፃ ማውጣት የለብኝም ? አለብኝ ! ግን እንዴት ? እነሱ የመንደሩ ሰዎች ይከተሉአቸዋል ፣ ይሰሟቸዋል ፤ ደግሞም እኔን ውሸታም ለማስባል አቅም አላቸው ስለዚህ ሁሉም በጊዜው መሆን አለበት ሀይለኛውን ለመጋፈጥ ሀይለኛ መሆን ፤ ተሰሚውን ለጋፈጥ ተሰሚ መሆም ፤ፈጣኑንም ለመጋፈጥ ፈጣን መሆን አለብኝ ፡ ግን ለማሸነፍ ከፈለኩ በእነሱ አቅም ልክ ሳይሆን ከእነሱ አቅም በላይ መሆን አለብኝ ።"

በማለት እየዘራ የነበረውን በቆሎ አስቁሞ ህመም የተሰማውን ወገቡን ለማሳረፍ የዛፍ ጥላ በአይኑ ፈለገ ግን አንድም የዛፍ አይነት በቦታው ስላልነበር ባለበት ቦታ ብዙም ያልተላጠ ሳር ያለው እና ጭቃ የሌለው መሬት ፈልጎ ለትንሽ ጊዜ አይኑን ጨፍኖ በጀርባው ጋደም አለ።

ቀን ቀንን እየተካች ነገ ዛሬ እየሆነ ዛሬ ደግሞ ትናንት እየሆነ የብሩክ ትምህርት መጀመሪያ ቀን አንድ ቀን ሲቀረው በቤታቸው ደጃፍ አክስቱ እና ሁለቱ መንታ እህቶቹ አይናቸው እንባ አርግዞ ለመወለድ የብሩክን የመጨረሻ የስንብት ሰላምታ ሲጠብቅ ፤ አጎትየው በበኩሉ የቤት ውስጥ የስራ ሀላፊነትን እየተረከበ ስለነበር የስራው ድካም እና አሰልቺነት እየታወሰው በከዘራው ደገፍ ብሎ ተክዟል ፤ ጥላሁን ደግሞ የብሩክን ቅያሪ ልብሶችና አንዳንድ አስፈላጊ የቤት ውስጥ መገልገያዎች በሁለት እጁ በትልልቅ ፌስታል አንጠልጥሎ ለመጓዝ እያኮበኮበ ሳለ ብሩክ በቅድሚያ አክስቱን ቀጥሎም ትንንሽ እህቶቹን ከዛም አጎቱን በየተራ እያቀፈ ሲሰናበታቸው ብሶት ያስረገዘው የአይናቸው እንባ የብሩክ ስንብት ስላፈነዳው እንባቸው እየተንፎለፎለ አፍንጫቸውንና ጉንጫቸውን እያሳበረ ከመሬት ጋር ተላተመ።

ብሩክ ሆድ እየባሰው ለአክስቱ በየወሩ እየመጣሁ እጠይቃችኋለው እነ ሚጣን አደራ እያለ የአክስቱን እጅ እየጨመቀ ሰሞ ለአንዳንድ ነገር መግዣ በማለት ከነበረችው ጥቂት ገንዘብ ቀንሶ በእጃቸው አድርጎ የኋሊት እየተጓዘ በእጁ የመጨረሻው ሰላምታ ሰጣቸው።

በመንገዳቸውም የመንደሩ አዋቂ አቶ መኮንን ቤትን እያቋረጡ ስለነበር የሀገሬው አዋቂ ያለ ልማዳቸው ከሚቆዩበት ቤት ያለ አጃቢ ወጥተው ብሩክንና ጥላሁንን ቆዳን ከስጋ በሚለይ የንቀት አይን እያያቸው እየገላመጠ አይኑን ሲያፈጥባቸው ሁለቱም ተያይተው ሳቃቸውን አፍነው መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ብሩክ ወደ ከተማው እንደገባ በተማሪ አቅሙ አነሰተኛ የሆነች ቤት ለመከራየት ከጥላሁን ጋር ያመጡአቸውን የቆዩ የቤት ውስጥ እቃዎችን ደግሞ እንደ ወጉ ለማስተካከል የሚከራይ ቤት ከጥቂት አሰሳ በኋላ በጥላሁን ጥቆማ ለትምህርት ቤቱ በማይርቅ ቦታ ስላገኙ የአንድ ወር ቅድመ ክፍያ ከፍለው ቁልፍ ተቀብለው ወደ ውስጥ ገቡ።

የተከራየው ቤት አቀማመጥ ከአከራያቸው ቤት በስተ ቀኝ ካሉት አምስት ቤቶች አንዱ ነው ዋናው ቤት በደረጃ ከፍ ተደርጎ የተሰራ ሲሆን የኪራይ ቤቶቹ በዝቅታው ስለሚገኙ አንጋጠው ትልቁን ቤት የሚመለከቱ ይመስላሉ።

የቤቱ ስፋት ፣ ቅዝቃዜው አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚገባው ምንጣፍ አልባው ሲማንቶ ፣ እየረገፈ ያለ ቢጫ ቀለም የተቀባ ግድግዳ ፣ በሹጉርጉር ማዳበሪያ ተወጥሮ የተሰራው ነገር ግን የቀድሞ ተከራይ ቤቱን በማዕድ ቤትነት ይጠቀመው ይመስል የጠቆረው ኮርኒስ ፣ ሲከፈቱ የስቃይ ድምፅ የሚያሰሙ በርና መስኮቶች እንዲሁም ኣይጥ የቦረቦራቸው ጥቃቅን ቀዳዳዎች የቤቱ ገፅታ አካሎች ነበሩ።

እነዚህ ሁሉ ለብሩክ ምቾት አልነሱትም ይልቁንም በከተማው በመዞር ጊዜ ለማጥፋት ስላልፈለገና ለቤቱ ኪራይ የሚከፍለው ገንዘብ ካሰበው በታች ስለነበር በዚያው ለመቆየት በመወሰኑ ከጥላሁን ጋር ቤቱን አፅድተው ፤ ሸረሪት ያደራቸውን ድሮችን በጣጥሰው ፤ ያመጠአቸውን እቃዎች በወጉ ደርድረው ፤ በመንገዱና በስራ የተጎዳው አካላቸውን ሊያድሱና የድረሱልኝ ጥሪ እያሰማ ያስጨነቃቸው ሆዳቸውን ሊፈውሱ ከቤቱ ተያይዘው ወጥተው አንድ ምግብ ቤት ገቡ።

"ጥሌ ስለ ሁሉም ነገር አመሰግናለው ምን እንደምል አላውቅም ብቻ አንተ ባትኖር ትምህቱን የማገኝ አይመስለኝም ደሞ ባገኝም እንዳንተ ነገሮችን የሚያቃልልኝ ሰው አይኖርም ነበር ብቻ ስለሁሉም አመሰግናለው።" አለው ወደ ምግብ ቤቱ መታጠቢያ ደርሰው እጃቸውን እየታጠቡ

ጥላሁንም በተራው እጁን ለመታጠብ የለበሰውን ቹጉርጉር ሸሚዝ ወደላይ እየሰበሰበ " ምን አደረክልኝ ልትል ነው ? የትምህርት ማስታወቂያውን ያነበብከው አንተ ፤ የነፃ የትምህርት እድል እንድታገኝ የለመንካቸው አንተ ባይሆን ከአሁን በኋላ ላደርግልህ ምትፈልገው ነገር ካለ ንገረኝ ቢያንስ በእሱ አግዝህና ምስጋናውን ትሰጠኛለህ ...ገባህ!" እያለ በእጁ ይዞት የነበረው ያልተደራረቀ ውሀ ፊቱ ላይ ረጨበት

ብሩክም ሳያስበው ፊቱ ላይ ውሀ ስለተረጨበት ደንግጦ የፊቱን ውሀ እየጠረገ " በል በል እዚሁ ከቆየን የጋኑን ውሀ ትደፋብኛለህ ና እንግባ "እያለው ለጥላሁን የውሀ ቀልድ የሚሆን በቀል እያሰበ ቀደም ብሎ ሲሄድ ጥላሁንም ፈጠን ብሎ ተከተለው።

በሁለቱም ሀሳብ ስምምነት የታዘዘው የአይነት ምግብ ቀርቦ እየተመገቡ ብሩክ አነስተኛ እንጀራ በሁለት ትልልቅ ቃሪያዎች ጠቅልሎ በአትክልት ሸፋፍኖ ለጥላሁን እንዲጎርስ እጁን ሲዘረጋለት ለክፋት ነው ብሎ ያላሰበው ጥላሁን ሳያንገራግር ምግቡን ጎረሰለት። ጥላሁን ምግቡን ሁለት ጊዜ ካላመጠው በኋላ አይኑ ከበርበሬ ብሶ ቀይ ሆነ ትንፋሽ ቶሎ ቶሎ እየወሰደ በላብ ተጠመቀ ምግብን በሰው ፊት መትፋት ነውር ስለሆነበት ሳይወድ በግዱ እንደ እሳት የሚፋጀውን ቃርያ ሲበላው ብሩክ እጁን በምግብ ጠረጴዛው አስደግፎ ከልቡ ሳቀ።

ጥላሁንም " ባንተ ቤት ቀለድክ አይደል" አለው ከጎረሰው በኋላ ከንፈሩ እና ምላሱ ላይ ያለውን ቃጠሎ ለማብረድ ደረቅ እንጀራ እየቆረሰ

"ጥሌ አዝናንተኸኛል አንተ ባታስታውሰኝ አላደርገውም ነበር " ብሎ መለሰለት እንባውን በክንዱ እየጠረገ።

እንዲህ እንዲያ እያሉ የቀረበላቸውን ምግብ ጨርሰው ረሀባቸውን አስታግሰው ከምግብ ቤቱ ሲወጡ ጥላሁን ለብሩክ "አቡሽ በቃ እኔ ወደ ሰፈር ልመለስ እነዛ ከብቶችን ልያቸው አንተ ደግሞ መንገዱና ሰራው ስላደከመህ ራስህን አሳርፍ መልካም የትምህርት ጊዜ ይሁንልህ ደግሞ ራስህን ጠብቅ እኔ በቅርቡ ትምህርት ስለምጀምር እንገናኛለን ፤ ይሄ ደግሞ አጎቴ ለልብስ መግዣ የሰጠኝ ነው ከኔ ይልቅ ለአንተ ስለሚያስፈልግ አንተ ተጠቀምበት።" እያለ ገንዘብ ከኋላ ኪሱ አውጥቶ ሲሰጠው ብሩክ ተቆጥቶ እሱ ጋር ገንዘብ እንዳለ እና እንዲመልሰው ነገረው ከአቋሙ ውልፍት ያላለው ጥላሁንም የብሩክን ሀሳብ በበላይነት አሸንፎ ገንዘቡን ሰጠው።

ጥላሁንም "እንደዚህ ደረቅ አትሁን እንዳደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለ ?" በማለት ጠየቀው

ብሩክም "አዎ ጥሌ እነሚጣን ተከታተልልኝ ምንም እንዳይቸግራቸው አጎቴንና አክስቴንም እንደዛው እሺ ጥሌ " በማለት ሲመልስለት

ጥላሁንም "እሺ ስለ እነሱ አታስብ እኔ እከታተልልሀለው አንተ ብቻ ትምህርትህን አጥብቀህ ያዝ ከተማም ስለሆነ ጠንቀቅ በል።"

"እሺ ጥሌ ደህና ሁን" በማለት ትንሽ ከተቃቀፉ በኋላ ጥላሁን በከብት ማሰማሪያ ሜዳው ከልጅነታቸው ጀምሮ ያሳለፉት ትዝ አለው ፤ አብረው ከብት ሲጠብቁ ፣ ጥሻ ለጥሻ ድብብቆሽ ሲጫወቱ ፣ ወደ ትምህርት በአንድ እጃቸው ደብተር በአንድ እጃቸው ደሞ ተቃቅፈው ሲሄዱ ፣የአባቱ ሞት ጊዜ አብሮት ሆኖ ሀዘኑን ሲካፈል ፣ አብረው ያሳለፉት ሁሉም

አዕምሮው ላይ ተሰሎበት እንዳቀፈው እንባውን ለቀቀው ።

ብሩክም የጥላሁን ሁለቱን ትከሻ ይዞ ፊት ለፊት እያየው "ምን ሆነሀል ? እንኳን ቦታ ሞትም እኮ ይለያል "እያለ የራሱን ስሜት ተቆጣጥሮ መልሶ ሲያቅፈው ስሜቱ ይበልጥ የበረታበት ጥላሁን ከእቅፉ ተመንጭቆ ወጥቶ ወደ መንደራቸው አቅጣጫ በሩጫ ሄደ።

ብሩክም እንባ ተናንቆት ልክ እንደ ጥላሁን ከልጅነታቸው ጀምሮ ያሳለፉት አዕምሮው ላይ ተራ ሳይጠብቁ ተዘበራርቀው ተደረደሩበት ጥላሁን ከፊት ለፊቱ የላሞች መጠበቂያ በትር ይዞ ጥያቄ ሲጠይቀው ፣ ትምህርት ቤት መሄድ ሰልችቶት ብሩክን ሲያስቸግረው ፣ ብሩክ አቅም አንሶት በዝናብና በበረዶ ተደብድቦ ጥላሁን ከሀገሬው አዋቂ ደጃፍ ደግፎ ወደ ቤቱ ሲያስገባው ፣ የቤታቸው ላም በጅብ ተወስዳ እንዳትሞት ያደረገው ጥረት ፣ ብሩክ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት በቁጣ ብሩክ ላይ ሲጮህበት ፣ በአደጋው ጊዜም ደግፎት መራመድ እንዲችል ሲያለማምደው ፣ የሰራቸው አስቂኝ ተንኮሎች በሙሉ በብሩክ አዕምሮ ተዘበራርቀው ስለተቀመጡ አንድ በአንድ አውጥቶ ምማሰብ ስላልቻለ እሱም እንደ ጥላሁን ፍጥነቱን ጨምሮ የተከራየው ቤቱ ገብቶ በሩን ከውስጥ ቆልፎ በአሮጌ ሸራ ላይ ጥላሁን አስተካክሎ ባነጠፈለት ፍራሽ ላይ በደረቱ ወድቆ ሰቅሰቅ ብሎ አለቀሰ።

ዲፕሎማው

የመኪናዎች ጥሩንባ ፤ በከፍተኛ ድምፅ የሚነጋገሩ የመንገደኞች ድምፅ ፤ ከተከራየው ቤት ፊት ለፊት ያለው ሰልክ መጠገኛ የከፈተው የሀይማኖት መዝሙር ፤ ድብልቅልቅ ያለ ድምፅ ከእንቅልፉ ቀሰቅሶታል ይሄን ጊዜ ብሩክ ሀገር ቤት ቢሆን ኖሮ የወፎች ዝማሬ በጆሮው እየሰማ ለቁርስ መስሪያነት አክስቱ የምታቀጣጥለውን መልካም መአዛ የሚወጣውን የወይራ ጪስ በአፍንጫው እየማገ ሰውነቱ ብቻ ሳይሆን አዕምሮውም እረፍት አድርጎ ነበር ከእንቅልፉ የሚነሳው።

ከተኛበት ፍራሽ ተነስቶ ራሱን ሲያስተውል ትናንት ከጥላሁን እንደተለያዩ የለበሰው ልብስ እና ጫማ አልተነኩም ነበር።

ድንገት ቀኑ የትምህርት መጀመሪያ ቀን እንደሆነ በሀሳቡ ውልብ ያለበት ብሩክ የትምህርት መጀመሪያው ሰአት እንዳያመልጠው ባለቤትነቱ የወላጅ አባቱ የነበረውና አባቱን ሁል ጊዜ ለማስታወስ በግራ እጁ ላይ ያሰረውን ሰአት ተመለከተ " ጉድ ፈላ !" በማለት በድጋሚ ሰአቱን ተመለከተ ፤ ትምህርት ሊጀመር አስራ አምስት ደቂቃ ቀርታለች ።

ብሩክ ጥድፊያውን ጀመረ ፊቱን የሚታጠብበት ውሀ ከያዛቸው እቃዎች መካከል ሰለሌለ ግቢው ውስጥ ካገኘሁ በማለት በሩጫ በመውጣት ከቤቱ አጠገብ በትልቅ ውሀ ማጠራቀሚያ የተጠራቀመ ውሀ ሰላገኘ የፊቱን መታጠብ ጉዳይ ጨርሶ የተከራያት ደሳሳ ቤቱን በመዝጋት በሩጫ ወደ ትምህርት ቤቱ አቀና።

የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ እንደደረሰ በጥቆማ የተማሪዎቹ ክፍል ተነግሮት ገባ " ኡፍፍፍፍፍ " በማለት በረጅሙ ተነፈሰ ተማሪዎች ቢሰበሰቡም ትምህርት ግን አልተጀመረም ነበር።

የሚቀመጥበት ወንበር ከመረጠ በኋላ በክፍል ያሉት ተማሪዎችን

ማስተዋል ጀመረ

የለበሱት ልብስ የሚማርክ ውብ የሆኑ ሴቶች እና ለመማሪያነት የያዙት በብሩክ የገንዘብ አቅም የማይታሰበው ላፕቶፕ ፣ በሴቶቹ እይታ ለመግባት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚስቁ በቡድን ተሰብስበው የተቀመጡ የፀጉራቸው አቆራረጥ የሚያምርባቸው ወንዶች ፣ በትምህርቱን አለመጀመር ተሰላችተው ከሞባይላቸው የተፋጠጡ ጥቂት የማይባሉ ልጆች ፣ ስካርቭ አንገቱ ላይ ጠምጥሞ ፀጉሩን አሳድጎ ትልቅ መነፅር አድርጎ አቀርቅሮ የሚፅፍ በእድሜ ከብሩክ የሚበልጥ ወንድ ልጅ፣ በጆሮዋቸው ባስቀመጡት ማዳመጫ አንዳች ነገር የሚሰሙ ውስን ልጆች ፣ ጥንድ ጥንድ ሆነው የተቀመጡ እና በዝግታ የሚያወሩ ፡ በቁጥር ከሀምሳ የማይዘሉ ተማሪዎች በክፍሉ ውስጥ ተከማችተው የትምህርቱን መጀመር እየተጠባበቁ የራሳቸውን ስራ እየሰሩ አስተዋለ።

"እንደምን አደራችሁ ? " የሚል ጎርናና ድምፅ ከአንድ በራ እና አጭር ቦርሳ በትከሻው አንግቦ ከሚገባው ሰው ተሰማ በክፍሉም ፀጥታ ሰፈነ ።

****

የብሩክ አጎት የእርሻውን አደራ ከብሩክ ቢቀበልም የመስራት ፍላጎት ግን ስለሌለው አደራውን ለመጠበቅ ብዙም ፍላጎቱ የለውም ለዛም ይመስላል ወደ ሰፊው እርሻ ከወጣ በኋላ የተንጣለለው ማሳን በገረፍታ ተመልክተው ወደ ቤታቸው ተመልሰው የሚገቡት ነገር ግን ጥላሁን ለአብሮ አደጉ በገባለት ቃል መሰረት ማሳውን እየተከታተለ ፣ አረሙን እየነቀለ እና እየኮተኮተ ቃሉን እየጠበቀ ነው። የቤተሰቡ ሀላፊነት በጫንቃቸው

የተሸከሙት የብሩክ አክስት አቅም እስኪያንሳቸው ድረስ ከአቅራቢያቸው ጫካ እንጨት ተሸክመው ሸጠው ፣ ከሲታ ላሞች በጥላሁን እገዛ አግደው ፣ የአጎትየው የመሰራት ወኔን የሚያከስሙ ነበልባል የሆኑ ዘለፋዎችን ችለው ቤተሰቡን እንደ አቅማቸው ደግፈው ቢይዙም የሰፈራቸው ማህበረሰብ አስተሳሰብ ግን ሩቅ አላስኬዳቸውም። የመንደሩ ቡና መጣጫ ከሆኑ ሰንብተዋል "ሴት አደለች ለምን ዝም ብላ ትደክማለች ?" "የት እንደምትደርስማ እናያለን !" እያሉ የመንደሩ ሰዎች በተሰበሰቡ ቁጥር የቤተሰቡን ጉሮሮ ለመድፈን የምትደክመውን የብሩክን አክስት ያማሉ ፤ ስጋዋን ይቦጭቃሉ እንዲሁም በተለያዩ የመንደሩ ቅኔዎች ባገኟት ቁጥር ሩህሩህ የሆነው ልባቸውን በቃላት ጦራቸው ይወጉታል።

የሰራው አድካሚነት ተቋቁመው ላይ ታች ሲሉ የሰነበቱት የብሩክ አክስት የመንደሩ ሰዎችን ዘለፋና ወሬ መስማት ቢታክታቸው "ስራ ለምኔ ?" ብለው ሰራቸውን እርግፍ አድርገው ባይተውትም የመንደሩ ሰዎችን ወሬ እና ዘለፋ ለመከላከልና ለማስቀረት የሚሰሩትን ስራ በእጅጉን ቀነሱት።

****

ቀን ቀንን ተክቶ ያለ አንዳች ከልካይ ይነጉዳል ብሩክም የሚማረው ትምህርት ተስማምቶታል ፣ ከተማሪዎቹ በሙሉም ተግባብታቷል ፤ የሚሰጡት የመመዘኛ ፈተናዎችም ያለ አንዳች እንከን እያስረከበ በመምህራኑ ዘንድ ሙገሳን አትርፏል ፤ ብሩክ የትምህርቱ ሁኔታ እንዲህ ይሁንለት እንጂ የቤተሰቡ ናፍቆት በተለይም የሁለቱ ውብ እህቶቹ ናፍቆት አላስችል ብሎታል ቃል በገባላቸው መሰረትም በወሩ ማጠናቀቂያ በመሄድ

ሊጠይቃቸው ቀን መቁጠር ቢያያዘውም ይዞት የመጣው ገንዘብ አለት ተለት መጉደል ትልቅ ችግሩ ሆኗል ስለሆነም አንድ ስራ መስራት እንዳለበት በማመን በእረፍት ቀኑ ስራ ለማፈላለግ እና ለመስራት ወሰነ።

****

ቀኑ እሁድ ነው በማለዳ ከቤተ ክርስትያን የሚሰማው ቅዳሴ ጊዜው ሳይገፋ ከተኛበት ቀስቅሶታል የተኛበትን ፍራሽ አሰማምሮ ፤ በሳምንቱ የተሰጡት ጥያቄዎችን በሚገባ ሰርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ከደሳሳዋ ኪራይ ቤት አጎንብሶ ሲወጣ " ቅዳሜን ሞተህ አሳለፍከው እንዴ ?" የሚል የአከራይዋ ወይዘሮ የትናየት ድምፅ ሰምቶ ከአንገቱ ቀና አለ

ወይዘሮ የትናየት ባለቤታቸው የሞቱባት እመቤት ሲሆኑ ብሩክ የተከራያት ትንች ደሳሳ ቤት ጨምሮ አምስት ቤቶችን አከራይተው ነው የሚተዳደሩት ቀይ ወፍራም እና ግራ እግራቸው በብርድ ምክንያት በትንሹ የሚያነክሱት ሲሆን ባለቤታቸው ባደረበት የኩላሊት ህመም ከሞተ ከሶስት አመት በላይ ሆኖታል እንዲሁም አንድ ለእናቷ የሆነች የብሩክ እኩያ የምትሆንና የከፍተኛ ትምህርቷን በነፃ የትምህርት እድል ምክንያት ኖርዌይ የገባችው ሄኖን እናት ናቸው።

በግቢው ውስጥ ወይዘሮ የትናየት ከአንዲት መልካም ሰራተኛ ጋር ይኖራሉ በቤቱ ተከራዮች ዘንድ ይወደዳሉ ከልጅ ጋር እንደ ልጅ ፤ ከወጣት እንደ ወጣት ብቻ ከሁሉም ሰው ጋር የሚጣጣሙ እመቤት ሲሆኑ ማንንም ከማንም አስበልጠውና አሳንሰው አያውቁም ሁሉም ተከራዮች ወይዘሮ የትናየትን እማማ በማለት በመጥራት የልባቸውን ትህትና እንዲሁም

የአክብሮታቸው መጠን ያሳያሉ።

ብሩክም ፈገግ በማለት "ቢቻልማ በምን እድሌ አንድ ቅዳሜ አይደለም መቶ ቅዳሜዎችን ነበር ሞቶ ማሳለፍ "በማለት ሲመልስ ወይዘሮ የትናየት ካጎነበሱበት የበረንዳቸውን ወፍራም ከእንጨት የተሰራ ምሰሶን ተደግፈው እየተነሱ "ወዴት ወዴት ገና ለገና የቤቱ ክፍያ ጊዜ ደረሰ ብለህ ከኔ ለመደበቅ ከሆነማ የአያቴ ቆሌ ማይገባበት የለም ጉሮሮህን ይዞ ነው የሚያመጣህ "ብለው ከውሀ ማጠራቀሚያ ገንዳው ውሀ ለመቅዳት አዘመሙ

በንግግራቸው ፈዞ የቀረው ብሩክም "ኧረ እከፍላለው እውነት እማማ እኔ ቀን ሳላጎድል ነው ምከፍለው "እያለ ተንተባትቦ ሲመልስ ወይዘሮ የትናየት "ምን ያወነባብድሀል እንደ ወንድ ቆፍጠን በል እንጂ ደግሞ ጨዋታን ከቁም ነገር ለይ ፤ እንካ ያዝ !" በማለት የቀዱትን ውሀ አቀበሉት

ብሩክም ውሀውን እየተቀበለ "እውነት እማማ እኔ እንደርስዎ አይነት እናት የመሰሉ አከራይ በማግኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ ፍቅር እኮ ናችሁ "እያለ ፊቱን ታጥቦ የተመናመነው የገንዘብ አቅሙን ለመመለስ ስራ ፍለጋ ከግቢው ለመውጣት ወደ ግቢው በር ሲቻኮል ወይዘሮ የትናየት "እኔ ምልክት ብሩክ ?" በማለት ብሩክን ላፍታ መለሱት

"አቤት እማማ "በማለት ከደረሰበት ቦታ በቀስታ ተመለሰ

"ቁርስ በልተሀል ?" በማለት ሲጠይቁት ልጅ እያለ እናቱ የምታደርግለት እንክብካቤ እና ስስት በአዕምሮው ተሰሎ "አይ እማማ አልበላሁም የምሰራው ስራ አለ ደሞም እንደለመድኩት ውጭ ነው ምበላው "በማለት ከበፊቱ በከሰመ ወኔ መለሰላቸው

"ግድ የለህም ዛሬ እዚሁ እኔ ቤት ቁርስህን በልተህ ትወጣለህ ና ግባ "

በማለት ለማቅማማት የሞከረው ብሩክን እጁን ይዘው ወደ ቤት አስገብተው ወደ ጓዳ ገቡ።

የቤቱ የውስጠኛው ክፍል ውበት ከውጭ እንደሚታየው አይደለም የጌጥ መብራቶች ፤ ውብ የመስኮት መጋረጃዎች ፤ የቅንጦት የሚመስሉ መቀመጫ ሶፋዎች ፤ ሰፋፊ መስታወት የተገጠመላቸው የምግብ ጠረጴዛዎችና ረጃጅም እግር ያላቸው ወንበሮች ፤ ከቤቱ ሰፊው ክፍል ላይ የተሰቀለው እንጨት የተሸከመች እናት ስዕል ብቻ ብሩክ የቤቱን ገፅታ ከተመለከተ በኋላ ከሚያምር ቴሌቪዥን የሚወጣው የወይዘሮ የትናየት እምነት የሆነው ለስላሳ ዝማሬ ወደ ጆሮው ገባ በዝማሬው እየተደሰተ ወይዘሮ የትናየት ከገቡበት ጓዳ በትልቅዬ ትሪ ምግባቸውን ይዘው ብቅ አሉ።

"እማማ ግን ለምን ይቸገራሉ እኔ እኮ ወጥቼ መብላት እችል ነበር " በማለት ንግግር ለማስጀመር ሞከረ

ወይዘሮ የትናየትም "ይሄንን ነው ችግር ያደረከው በል ምግቡን ቅመስ ምትጠጣውን ላምጣልህ ምን ይሻልሀል ? ከውሀ ይልቅ ሰሞኑን የጠመኩት መውደድ አለ እሱ ይሻልሀል ? ወይስ ለስላሳ ነገር ይሁንልህ ?" በማለት በጥያቄ ሲወጥሩት

"እንዴ እማማ እንኳን ውሀ መርዝ ቢሆንም እንኳ እርሶ ከጋበዙኝ እጠጣለው " በማለት ለመቀለድና ከጥያቄዎቹ ፋታ ለመውሰድ ሞከረ

"ጉደኛ ነህ በል ጀምር ሌላ ማንን ትጠብቃለህ ?" በማለት ወደ ጓዳ ሲገቡ ከፍትፍቱ ፊቱ የሰመረለት ብሩክ ፊቱን ወደ ፍትፍቱ አዞረ ።

ወይዘሮ የትናየትም የወደዱትና የሙያቸው ማመሳከሪያ የሆነው መውደዳቸውን ከጓዳ ይዘው ብቅ እያሉ " ሰሞኑን ሄኖን ደውላ ነበር ስለ

ተከራዮቹ ጠይቃኝ ስላንተ ስነግራት ተደስታለች ልታናግርህ እንደምትፈልግና ስልክ ቁጥር እንድሰጥህ አደራ ብላኛለች በል ዛሬ ስልክ ቁጥሯን እሰጥህና ትደውልላታለህ "በማለት ያመጡትን መውደድ ቀድተው መልስ መጠበቅ ጀመሩ

"ብሩክም ግራ በመጋባት ከነዚህ ሁሉ ተከራይ ለምን እኔን ተለየሁ ? ደግሞስ ይሁን ብዬ ስንኳን ብቀበልዎት በምኔ ነው ምደውልላት ? ደውዬስ ምንድነው የምላት ? "በማለት በተራው በጥያቄ ሲሞላቸው

"አንተ ደግሞ ረሳኸው እኩያህ እኮ ናት እና ሁለታችሁም ተማሪ ናችሁ ከሌላው በዚህ ትለያለህ ምናልባት መንፈሳችሁም ተሳስሮ ይሆናል ደግሞ በምን እንደምትደውልላት አሳይሀለው "በማለት ፈገግ እያሉ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ቴሌቪዥኑ ተጠግተው አንድ ሰፊ ገፅ ያለው ስልክ ካነሱ በኋላ ተመልሰው መጥተው

"ይሄ ሄኖን እዚህ እያለች ምትጠቀመው ስልክ ነበር አሁን ግን ማንም ስለማይጠቀምበት መያዝና መደወል ትችላለህ ደግሞስ ወንድ አይደለህ ኧረ በፈጠረህ ቆፍጠን በል አትንበጭበጭ ደውለህ ማንነትህንና እኔ እንድትደውልላት እንዳደረኩ ንገራት "በማለት ሰትመልሰለት

የጎረሰው ምግብ ከጉንጩ የተጣበቀ ይመስል አይኑን ፈንቅሎ ወይዘሮ የትናየትን ሲያፈጥ "በእየሱስ ስም ብሩክ ብሩክ "በማለት ስሙን ደጋግመው ጠሩት

ብሩክም "እምምም.....ማማ ለምን ይሄ ለኔ ያደርጋሉ ? እኔ እኮ ... " በማለት ሲንተባተብ ንግግሩን አቋርጠው

"በል በል መልካምነት ምክንያት አይፈልግም ደግሞም ለኔ ሁላችሁም ልጆቼ ናችሁ በተለይም አንተና ሄኖን "በማለት መለሱለት

ብሩክም በእሺታ አንገቱን ነቅንቆ ደንገጥ በማለት "ውይ እማማ እንብላ ሳልሎት ? "ሲላቸው

"በቤቴ ይሉኝታ የሚይዘኝ መስሎህ ነው ? መብላት ብፈልግ ምን አስለፈለፈኝ ካንተ እኩል ትሪው ላይ አልሰማራም ነበር ? "በማለት እየቀለዱ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት።

ብሩክም ፈገግ በማለት "እሺ እማማ የሄኖንን ሰልክ ቁጥር ይሰጡኝና በኋላ ወይም ማታ ጊዜ እደውልላታለው "በማለት የሄኖንን ሰልክ ቁጥር ከነ ወይዘሮ የትናየት ስጦታ ከሆነው ሰልክ ጋር ተቀብሎ ሰለ ቁርስ ግብዣው አመስግኖ ከቤቱ ወጣ ።

ከቤቱ እንደወጣ አጉል እንዳይገጥመው በማሰብ የተሰጠውን ምን እንደሚያመጣላት ወይም እንደሚያመጣበት ያላወቀው ሰልክ ቁጥርና የሰልክ ቀፎ ወደ ቤቱ አስገብቶ ሰለ ወይዘሮ የትናየት መልካምነት እያሰላሰለ ሰራ ፍለጋ ተሰማራ። በቅድሚያ የሄደው የድለላ ሰራ ወደሚሰሩ ሰዎች ሲሆን እነዚህ ሰዎችን የተገናኘው እንደ ትምህርት እድሉ ማስታወቂያ ከግድግዳ ላይ በተለጠፈ ወረቀት ነበር ።

ሶስት የድለላ ሰራ የሚሰሩ ሰዎች ጋር በመሄድ እድሉን ለመሞክር ስላሰበ ወደ አንደኛው ሰው በቅድሚያ ሄዶ በእረፍት ቀናት የሚሰራ ሰራ እንዳለ ቢጠይቅም በጎ ምላሽ አልጠበቀውም በተመሳሳይም ሁለቱ ደላላዎች ጋር ቢሄድም በስራ ቀናት እንጂ በእረፍት ቀናት የሚሆነውን ሰራ ስላላገኘ እጁን አጣጥፎ ከመቀመጥ ፋንታ በእረፍት ቀናት ሰዎች ወደሚያዘዋትሩአቸው ቦታዎች የሊስትሮ ሰራን ለመስራት አስቦ ምን ምን እቃ እንደሚያስፈልግ ለማየት ወደ ሌሎች ሊስትሮዎች በመሄድ እቃዎችን የሚገዙትን በአነስተኛ ዋጋ ገዝቶ የሚሰሩትንም ሰርቶ ወደ ወይዘሮ የትናየት ግቢ እቃዎቹን ይዞ ሲገባ አትክልቶችን ሲንከባከቡ የነበሩት ወይዘሮ የትናየት ምን እንዳሰበ

ቀድመው ስለተረዱ የ " በርታ " ምልክትን በአውራ ጣታቸው ሲያሳዩት ብሩክ በፈገግታ ወደ ቤቱ ገብቶ ከአረፈ በኋላ ከአከራዩ የተቀበለውን ስልክ ቁጥር ለመምታት ቀፎውን አነሳ።

"ሀሎ " በማለት ብሩክ ምላሽ ጠበቀ

"ሀሎ ማን ልበል ? "የሚል ቀጭን የሴት ድምፅ አደመጠ

ይህንን ድምፅ የሆነ ቦታ ያውቀዋል የት እንደሆነ ለመለየት ግን ጭንቅላቱ አቀነባብሮ ማሰብ ተስኖታል

" ብሩክ ... ብሩክ እባላለው የእማማ ተከራይ ነኝ ...ማለቴ እማማ የትናየት ናቸው እንድደውልልሽ ስልክሽንና የስልክ ቀፎ የሰጡኝ "

" ሄይ ብሩክ ሰላም ነህ ስላንተ ማም ብዙ ነገር ነግራኛለች ፤ እንደነገረችኝ በቃ ማግኘትና ማናገር ፈለኩኝ ሄኖን እባላለው "

" እእእእእሺ እሄሄ ደግሞ ብሩክ .... እባላለው "

" በል ብሩክ ነገ ጠዋት የሴሚስተር ፈተና ስላለብኝ ብዙ አላወራህም በጣም ይቅርታ እሺ ደሞ እደውላለው አንተም አትጥፋ "

" እሺ ..... አአአልጠፋም "

"good by "

ስልኩ ቢዘጋም በልቡ ማውራቱን አላቆመም " ሀሮት ወይስ ሄኖን ? ማን ነሽ አንቺ " በማለት የተመሳሰለውን የወይዘሮ የትናየት ልጅ ሄኖን እና ሀይስኩል ጓደኛው ሀሮት ቀጭን ድምፅና ችኩል ባህሪያቸውን ለማለያየት ብዙ ሞከረ " አይ በፍፁም አይሆንም ሀሮት የምትማረው አዲስ አበባ ሄኖን ምትማረው ውጭ ሀገር ነው " በማለት ልቡን ያላሳመነው ነገር ግን

ማምለጫ መንገድ ያደረጋቸው ልዩነቶችን እየዘረዘረ ለምሽት ጊዜውን ሲሰጥ የነበረውን ቀንን ተከትሎ ነገ ላይ ለመድረስ እንቅልፍ መጓጓዣውን አድርጎ በአክስቱ ጋቢ ተጠቀለለ ።

ደግነት

ከሰኞ እስከ አርብ ትምህርቱን እየተማረ ቅዳሜ ሙሉ ቀንና እሁድ ጠዋት በቤተክርስትያን ፣ በስብሰባ ቦታዎች እና ሰው በሚበዛባቸው አካባቢዎች እየዞረ ስራውን በሚገባ ሰርቶ ገንዘቡን በማጠራቀም የሰውን እጅ ላለመጠበቅና ወደ ናፈቁት ቤተሰቡ ሲመለስ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛት መስራት ከጀመረ ሁለተኛው ሳምንቱ ነው። የቤቱ አከራይ ወይዘሮ የትናየት የብሩክን ልፋትና ድካም እያዩ በቸልታ ማለፍን ሳይመርጡ ሁል ጊዜ በየሳምንቱ እሁድ ምሳ ይጋብዙታል ቡና ያፈሉለታል እየተጨዋወቱና የልባቸውን እንደ እናትና ልጅ እያወሩ ቀኑን ያሳልፉታል ። የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር አቶ ግርማቸው ቢሆኑም ወደ ብሩክ ቤት ከአንዴም ሁለት ጊዜ በመምጣት እየሰራ ባለው ስራ እንደተደሰተ እና መበርታት እንዳለበት መክሮታል።

ብሩክ እነዚህን ሁለት ደግ እና የዋህ ሰዎች ህይወት አሰናድታ ባትጠብቀው ኖሮ መቼም ቢሆን የከተማውን ኑሮ መላመድና ትምህርቱን መቀጠል እንደማይችል ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ሁለቱን ሰዎች ከልቡ ያከብራቸዋል ይወዳቸዋል።

በቀጣዩ ሳምንት ለቤተሰቦቹ ቃል በገባው መሰረት መሄድ እንዳለበት ስላመነ የትምህርት እረፍት ፈቃድ እንዲሰጡት አቶ ግርማቸውን ለምኖ

የሶስት ቀን የእረፍት ፍቃድ ስላገኘ ጊዜ ሳያጠፋ ወደሚወዳቸው ቤተሰቦቹ እና ወደ ናፈቁት እህቶች ለመሄድ መሰናዳት ጀምሯል የትናንሽ እህቶቹ ልብሶች እና ለትምህርት የሚጠቅሙ መፅሀፍቶች እንዲሁም የተለያዩ ለረጅም ጊዜ የሚሰነብቱ ምግቦችን እንዲሁም ደህንነታቸውን የሚጠይቅበት ስልክ ለአክስቱ በመግዛት ጉዞ መጀመር ማሰቡንና በቅርብ እንደሚመለስ ለመንገር ወይዘሮ የትናየትን ለማግኘት አስቧል ።

****

"እማ ብሩክ እኮ እመጣለው ካለ ቆየ መቼ ነው ሚመጣው ? " በማለት የብሩክ ታናሽ እህት ለአክስቷ በልጅ አንደበት ጠየቀቻት

" የኔ እምቦቃቅላ ናፈቀሽ አይደል ሰሞኑን ይመጣል እሺ " በማለት ሁለቱን ጉንጫቸው ዝቅ ብለው ቆንጠጥ አደረጓት

"እዚህ ቤት ሚበላ ምግብ የለም እንዴ ወይስ በረሀብ ልትገድሉኝ ፈለጋችሁ ?"እያለ የብሩክ አጎት በቁጣ ወደ ቤት ገባ

የብሩክ አክስትም ለመቆጣት እየሞከሩ ወገባቸውን ይዘው"ኡኡቴ ራበኝ ነው ያልከው ? ይሄንን ንግግር የሰማ ሰውማ በስራ ደክመህ እውነትም ተርበህ የምታወራ ነው ሚመስለው : ምናለ ለቤቱ የሚጠቅም ስራ ብትሰራ እስቲ ኑሮአችንን እናሸንፍ እኔም አንተም ሰርተን እንለወጥ : መንደር ለመንደር በየመጠጥ ቤቱ እየዋልክ የቤተሰቡን ክብር አትጣል : እረ ተዉ አንተ ሰው አደብ ግዛ : እነዚህ ልጆች ከአንተ ምን ይማሩ ?"

እያሉ ሲያናግሯቸው የብሩክ አጎት ከቆመበት እየተንደረደረ መጥቶ እህቱን በጥፊ ካጮላት በኋላ " ስሚ ሁለተኛ እንደዚህ አይነት ንግግር ብታደርጊ ሜዳ ላይ አውጥቼ ነው ምጥልሽ ገና ለገና የቤተሰቤን ኑሮ ልለውጥ ብዬ

የዞራ እርግማን በዘሬ ላይ ላውርድ ? ንገሪኝ ? የዞራን እርግማን የምሸሽበት መሸሸጊያ ሰራ ሰርቼ አገኛለው ? ሰራ ከዞራ እርግማን ጥላ ይሆነኛል ? እህ " በማለት በከፍተኛ ቁጣ ሲመልሰላቸው ሁለቱ ትንንሽ ውብ የብሩክ እህቶች እርስ በእርስ ተቃቅፈው ይመለከቱ ስለነበር አጎትየው አንድ ጊዜ እህቱን አንድ ጊዜ አጎት የሆናቸው ውብ ልጆችን ተመልክቶ ምንም ቃል ጨምሮ ሳይተነፍስ ከዘራውን ይዞ ከቤቱ ወጣ።

****

ለቤተሰቦቹ በተለይም ለትናንሽ እህቶች የገዛቸው ልብሶች እንዲሁም አከራዩ ወይዘሮ የትናየት ከውጭ ሀገር የተላከላቸውንና ለአክስቱና አጎቱ እንዲልክላቸው ያስገደዱት ሁለት ብርድ ልብስን ጨምሮ የተለያዩ እቃዎች ለመያዝ በሚያመች መልኩ አሰናድቶ ጉዞ ለመጀመር የተዘጋጀው ከማለዳው ጀምሮ ስለነበር ወይዘሮ የትናየትን ለመሰናበት ከደጃፋቸው በመቆም

"እማማ .... እማማ " በማለት ተጣራ

ወይዘሮ የትናየት በማለዳ የተጠሩበትን ምክንያት ለማወቅ ልብስ እየደረቡ የሳሎኑን በር ሲከፍቱት ብሩክ ሻንጣ በትከሻው አዝሎ እግሩ ስር ትልቅ ፌስታል አስቀምጦ ፈገግ ብሎ እየጠበቃቸው ነበር ።

" ውይ ብሩክ አንተ ነህ እንዴ ?"

"አዎ እማማ በጠዋት ቀሰቀስዎት አደል ? ዛሬ ወዳገር ቤት ስለምሄድ እኮ ነው ልሰናበትዎት ብዬ ይሄ ደግሞ የወር ክፍያው ነው በማለት ገንዘብ

በእጁ ዘርግቶ እስኪቀበሉት ጠበቃቸው"

"ደግ አረክ በል : እኔም ከመንገድ አልያዝህ ደግሞም እንዳትቆይ ሰሞኑን ሄኖን ትመጣለች እንዳታመልጥህ ታገኛታለህ ፤ ቤተሰብህን ሁሉ ሰላም በልልኝ አንድ ቀን መጥቼ እንደምጠይቃቸውም ንገርልኝ እሱን ደግሞ ለመንገድህ ምንም ስላላደረኩልህ ያዘው ይጠቅምሀል በማለት የዘረጋው እጁን በእጃቸው ሲመልሱት ብሩክ የበዛበትን ውለታ አስቦ "በፍፁም ካልተቀበሉኝ ከዚህ ቤት አልወጣም "በማለቱ በግድ ገንዘቡን ተቀብለው ተሰነባብተው ተለያዩ ።

****

የብሩክን መምጣት ከሩቅ የተመለከቱት ሁለቱ መንትያ እህተማማቾች በደስታ እየፈነደቁ"እማዬ እማ .... ብሩክ እየመጣ ነው .... ብሩክ እየመጣ ነው "በማለት ሁለቱ ትንንሽ ልጆች በግቢው ውስጥ በደስታ የሚሆኑትን በማጣት አንዴ ወደ ቤት አንዴ ወደ ደጅ እየወጡ መቦረቅ ጀመሩ።

የብሩክ አክስትም የልጆቹን ደስታ እያዩ ፍጥነት ጨምረው ወደ ደጅ በመውጣት ሲመለከቱ የአደራ ልጃቸው ከሄደበት ከተማ በወሩ እየተመለሰ ነበር ፤ የመንገዱ ድካም እንዳለ ሆኖ የያዘው እቃ ሸክም ክብደት አቅሙን የጨረሰው ብሩክን ለማገዝ ወደ ብሩክ ተንደርድረው በመሄድ አንገቱ ላይ ተጠምጥመው ናፍቆታቸውን ጋብ ለማድረግ ሞክሩ ።

ተጋግዘው እቃዎቹን በመያዝ ወደ ቤቱ ግቢ ሲገቡ የናፈቃቸውና የናፈቁት ሁለቱ ትንንሽ እህቶች ወደ ብሩክ በመሮጥ ለማቀፍ ሲሽቀዳደሙ ብሩክ የተቀበላቸው ተንበርክኮ ነበር ሁለቱንም በተደጋጋሚ እያፈራረቀ

ግንባራቸውን ፣ ፀጉራቸውንና ጉንጫቸውን ከሳመ በኋላ እየተጓተቱ ወደ ቤቱ ዘለቁ።

"አጎቴስ ? የለም እንዴ ?" በማለት ቤቱን እያማተረ ጠየቀ

"አዎ እንደለመደው እየዞረ ይሆናል ግን ምን አደከመን ምሳ ሰአት ላይ መምጣቱ አይቀር " በማለት አክስቱ የአጎትየው በተደጋጋሚ ቤት ጥሎ መሄድና መንደር ለመንደር መዞር እንዳማረራቸው በሚገልፅ ገፅታ እጃቸውን እያወናጨፉ መለሱለት

የብሩክ ቤተሰቦች መኖርያ በትንሹ ከአንድ ወር በፊት የነበረውን ገፅታ ተቀይሯል የቤቱ ምሰሶ በስሌሎች በተሞላ ጋዜጣ ተሸፍኗል ፣ የእጅ ጥበብ የሆኑ የክር ስራዎች በግድግዳው እዚህም እዚያ ተሰቅለዋል እንዲሁም የቤቱ ግድግዳ በአዲስ አዛባ ተለቅልቋል ፣ የሚያፈሰው የሳር ጣርያም ቢሆን በአዲስ ሳር መሸፈኑን አስተውሏል።

ብሩክ ከአጎቱ እንደዚህ አይነት ስራ ስለማይጠብቅ አክስቱን በልቡ እያወደሳት ነው ፤ ለአጎቱና ለጥላሁን የሰጣቸው የማሳ አደራም ቢሆን ለማየት ቸኩሏል ግን አሁን ወደ ማሳው መሄድ እንደሌለበት ስለገባው ከትንሽ እረፍት በኋላ ለትናንሽ እህቶቹ የገዛላቸውን ልብሶች እያወጣ አንድ በአንድ እየሰጠ በመምጣቱ ብቻ ለተደሰቱት እህቶቹ በደስታ ላይ ደስታን ደራረበላቸው።

የማለዳው ጉዞ ሰውነቱን ያደከመው ብሩክ ወደ መደቡ በመሄድ እረፍት ለማድረግ በጀርባው ተንጋሎ አሸለበ።

"ብሩክ ... ብሩክ .... ተኛህ እንጂ ሞትክ እንዴ ብዙ ተኝተሀል ተነስ አጎትህ መጥቷል አነጋግረው " በማለት አክስቱ በቀዝቃዛውና ሸካራ እጃቸው ግንባሩን እያሻሹ አነቁት ።

ብሩክም የአጎቱን መምጣት እንደሰማ ብድግ በማለት ተነስቶ ኣይኑን በጣቱ እያሸ ከቤቱ በራፍ በበርጩማ ተቀምጠው ውጭ ውጭ ሲመለከቱ ወደነበሩት አጎቱ በመጠጋት

"አጎቴ "በማለት ተጣራ

አጎቱም ወደ ብሩክ እየዞረ "እህ አጅሬው በሰላም መጣህ ? ቆይታ እንዴት ነበር ?" በማለት ምላሹም ለመስማት አይን አይኑን ትኩር ብሎ ተመለከተው

"አዎን አጎቴ በሰላም መጣሁ ግን መንገዱ አድካሚ ነበር ቆይታም ደግሞ ጥሩ ነበር ትምህርትን ብቻ ሳይሆን መልካም ሰዎችን አግኝቼበታለው ደስ የሚል ቆይታ ነበር "በማለት ፈገግ እያለ መለሰለት

"እና መች ነው ጨርሰህ ከአቶ መኮንን ግልምጫ ምትገላግለኝ ? እኔ እኮ ዛሬ ነገ ዞራ በአንተ ጉዳይ ምን ይለኛል ምን ይፈርድብኛል እያልኩ ተሳቅቄ አልኩኝ እኮ "በማለት ለአንድ ወር ረስቶት የነበረው የዞራ መንፈስና የአቶ ግርማቸው ጉዳይ መልሶ እንዲያስብ አስገደዱት

ብሩክም መልስ ለመስጠት ሲዘጋጅ በዝናብ የደረሰበት እንግልትና ስቃይ እንዲሁም በእነ አቶ መኮንን ቤት የሰማቸው የቃላት ልውውጦች በአዕምሮው ተስለው ሰላም ስለነሱት ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ

"ዞራ ... ዞራ .... ዞራ "በማለት በዝቅተኛ ድምፅ ተናግሮ እያደገ የነበረው ሉጫ ፀጉሩን ወደ ኋላ በፍጥነት ካስተኛው በኋላ የንግግር ሀሳብ ለማስቀየር

"በነገራችን ላይ ለአንተና ለአክስቴ የተላከላችሁ እቃ አለ እማማ የትናየት ይባላሉ የተከራየሁበት ቤት ባለቤት ናቸው ይሄንን ብርድ ልብስ "በማለት ከሻንጣው በላስቲክ የታሸገ ብርድ ልብስ እያወጣ ለአጎቱ ሰጠው

አጎቱም ፊቱ እንደ አደይ አበባ ፈክቶ ብርድ ልብሱን ከላስቲኩ እየፈቱ " የተባረኩ ሰው ናቸው : ስማቸውን ማን አልከኝ "

"እማማ የትናየት "

"አቤት ዞራ ምን ይሳንሀል ብርድ እንዳይመታኝ ልብስ አዘጋጅህልኝ ? " በማለት አንገታቸውን ወደ ላይ አንስተው እጃቸውን ተርግተው ሲናገሩ ብሩክ ቀበል አድርጎ

"አንድ ቀን መጥታ እንደምትጠይቃችሁም ቃል ገብታልኛለች "ብሎ ሲመልስለት አጎትየው ከተቀመጠበት በመነሳት

"ስማ ተመልሰህ ስትሄድ ትልቅ ምስጋና ነው እንድታቀርብልኝ የምፈልገው ገባህ ... ትልቅ ምስጋና እኔ እዚህ ዞራን አመሰግናለው አንተ ደግሞሞሞ ..... ማን አልከኝ ስማቸው ?"

"እማማ የትናየት "

"አአአው እማማን ታመሰግናለህ ... ዋ ደሞ ነግሬሀለው ትልቅ ምስጋና አድርስላቸው "

ብሩክም ፈገግ እያለ "እሺ ትልቅ ምስጋና አደርሳለው "በማለት ሲመልስለት የብሩክ አክስት በትልቅዬ ሸክላ የተጠበሰ ስጋ በጎድጓዳ ሸክላ ከጓዳ ይዘው ብቅ እያሉ

"ኑ ጠጋ በሉ ምሳችንን እንብላ "በማለት ተናግረው ሸክላውን አስቀምጠው ወደ ብሩክ አጎት ዞር በማለት "አንተ ሰው ለልጁ ለምን ታደክመዋለህ ? ቢያንስ ተቀምጣችሁ አታወሩም ? ከመንገድ እኮ ነው የሚገባው "ብለው ቆጣ ሲሉ

አጎትየው ቀበል አድርገው "ወጣት ምኑ ይደክማል ብለሽ ? ከመንገድ

አይደለም ከጦር ሜዳ ቢመጣም አይደክምም ልጁ እኮ ብሩክ ነው " በማለት በያዙት ከዘራ እግሩን ለኮፍ አድርገው ወደ ማዕዱ ቀረቡ።

ብሩክ በአግራሞት "ይሄ ስጋ ከየት አመጣችሁት ?" እያለ ቢጠይቅም መልስ አላገኘም

ውብ እህቶቹ በገዛላቸው ልብስና በመረጠላቸው ቀለም ተደስተው ምግብ መብላቱን ዘንግተው የልብሶቻቸውን ጌጥ እየነካኩ ሲመለከቱ በተደጋጋሚ ከአክስታቸው ተግሳፅን እየተቀበሉ ምግባቸው ጋር ይመለሳሉ ብሩክ ተደስቷል ለሳምንታት የተለያቸው ቤተሰቡ መሀል ተገኝቶ ማዕድ መቁረሱ ልዩ ስሜት በውስጡ ተፈጥሯል ግን አብሮ አደግ ጓደኛውን ጥላሁንን ለማግኘት ስለጓጓ ለአክስቱ

" ጥላሁን ግን አለ ?" በማለት ጠየቃት

"ውይ የተባረከ ልጅ በዚህ ሁለት ቀን አልመጣም እንጂ እለት እለት እየመጣ ማጭዱን ይዞ ልክ እንዳንተ ማሳውን ሲኮተኩትና ሲያርም ነበር እኔም ከዛሬ ነገ ለምን እንደቀረ እጠይቀዋለው እያልሁ ተረሳኝ " በማለት ሲመልሱለት እንግዳ የሆነ ፍርሀት በውስጡ ስላደረ ከምሳ በኋላ ጥላሁንን መጠየቅ እንዳለበት ወሰነ።

****

"ጥላሁን ... ጥሌ ... ጥሌ " በማለት ከደጃፍ ሆኖ ብሩክ ተጣራ

ነገር ግን በጥላሁን ፈንታ የጥላሁን እናት ከቤቱ ብቅ በማለት "ማን ነው የፈለገው ? " በማለት መለሱ

" እኔ ነኝ ብሩክ .... የጥላሁን ጓደኛ "

"ውይ በሞትኩት አንተ መቼ መጣህ እኛማ ከዛሬ ነገ ትመጣለህ እያልን ስንጠብቅ ነበር : በሰላም መጣህ ? " በማለት ወደ ብሩክ እየተጠጉ በጥያቄ ሲከቡት

" ዛሬ ነው የመጣሁት በሰላም ነው የመጣሁት እማ ጥላሁን የለም እንዴ ?" በማለት ወደመጣበት ጥያቄ ሲመለስ

"እዬ ብሩክ እሱማ ድንገት እኮ ነው ከትናንት ወድያ ትምህርት ነው መሰለኝ ያለው ብቻ ወደ አዲስአባ ሄዷል እንደው አልተገናኛችሁም ? " በማለት ሲመልሱለት

"አዎን እማ አልተገናኘንም ደግሞም የመጣሁት እኮ አክስቴ 'ጥላሁን ጠፋ ' እያለች ስታወራ ሰምቼ ነው ድንገት ከቤት ሲቀር ደንግጠን እኮ ነው " ሲላቸው

" ድንገትስ አዎ ድንገት ነው ግን እኮ ለአጎትህ ሁሉንም ነገር ነግሮታል እንደሚሄድ እና የማሳውን ጉዳይ አደራ ሰጥቶት ነው የሄደው : ምነው አጎትህ አልነገራችሁም እንዴ ?" በማለት ስትመልስለት

"ቆይ እስቲ ለአጎቴ እጠይቀዋለው በሉ ደህና ይዋሉ መልካም ቀን " በማለት ሲመለስ እንዳይጠፋ እና እንዲጠይቃቸው መልሰውለት ወደ ቤቱ በጥያቄ እየተብሰለሰለ አመራ።

"እንዴት ጥላሁን ትምህርት ማግኘቱን አልነገረኝም ? ከተማ ያለውን ቤቴን ያውቀዋል ለምን መጥቶ አላናገረኝም ? ደግሞስ አጎቴ ይህንን መደበቅ

ለምን ፈለገ ? " በማለት ወደተንጣለለው ማሳ ሄደ ።

ማሳው ዘር የተዘራበት ቦታ በሚገባ አፈሩ ተይዟል ነገር ግን ሌላው መሬት አልፎ አልፎ በሚጥለው ከባድ ዝናም እየተጠረገ በመወሰዱ በረሃ መስሏል። ወደ ተዘሩት በቆሎዎች እየሄደ "አይ ጥላሁን ? ልክ እንደ ራስህ ተንከባክበኸው የለ ?" በማለት ጥላሁንን በልቡ እያመሰገነ ፍሬ የያዙት የበቆሎ አገዳዎችን እየዞረ ተመለከተ ብዛት ያላቸው ናቸው እንኳን ለቤት ውስጥ ይቅርና ለገበያም ማቅረብ እንደሚቻል ብዛታቸው አስረድቶታል።

ቀሪውን ጊዜ ከእህቶቹ እየተጫወተ ፤ የገዛላቸው የልጆች መፅሀፍት እንዴት እንደሚነበቡ በማስተማር ፤ ለአክስቱም የገዛላት የስልክ ቀፎ አጠቃቀም በማስረዳት ፤ ለአጎቱም የማሳውን ጉዳይ በከፍተኛ አደራ ደጋግሞ በማሳሰብ ጊዜውን ካሳለፈ በኋላ የመመለሻው ቀን በመድረሱ የጥላሁንን እናት ተሰናብቶ ዳግመኛ እንዳይሄድባቸው የወተወቱት ሁለቱ እህቶቹን አግባብቶና አባብሎ ቤተሰቡን በመሰናበት ጉዞውን ትምህርቱ ወደ ጀመረባት ከተማ አደረገ።

ወደ ከተማ በሚያቀናበት ጊዜ ያስብ የነበረው ወይዘሮ የትናየት በቅርብ ትመጣለች በማለት ስለነገረችው ሄኖን ነበረ ። ምናልባት ሰም ቀይራ ቢሆንና ራሷ ሀሮት ብትሆን ምን ሊል እንደሚችል ግራ ገብቶታል። በልቡም ሄኖን ሀሮት እንዳትሆን እየተመኘ ጉዞውን ወደ ከተማ ወይዘሮ የትናየት ግቢ አደረገ።

****

የግቢው በር ከፍቶ ሲገባ ግቢው ጭር ብሏል በሀሳቡ ትመጣለች

የተባለችውን ሄኖን እየፈለገ ወደ ኪራይ ቤቱ አምርቶ አዋጅ ነጋሪው የቤቱን አሮጌ በር ሲከፍት ወይዘሮ የትናየት የጮኸውን የብሩክ በር ድምፅ ከቤታቸው በመውጣት "እንዴ ብሩክ መጣህ እንዴ ? ምነው መጥቻለው አይባልም ?" በማለት ሲጠይቁት

"አይ እማማ እቃ አስቀምጬ እና ትንሽ አርፌ እመጣለው ብዬ እኮ ነው " ሲላቸው

"በል በል ውስጥ እንግዳ አለ እቃህን አስቀምጠህ ና ደሞ ጥሩ ሰአት ላይ መጣህ ቡናም ደርሷል ፍጠን "በማለት ወደ ቤታቸው ሲገቡ የብሩክ ፍርሀት በእጅጉ ጨመረ "እንግዳ ?" በማለት ለራሱ አወራ።

በቀስታ ወደ ቤቱ ገብቶ ጫማውን አወላልቆ በፍራሹ ጠርዝ በዝግታ ተቀምጦ "ሀሮት ብትሆንስ ምን ልላት ነው ? "እያለ እያሰበ ወይዘሮ የትናየት ከደጅ ሆናው "ብሩክ .... ብሩክ እረ ቡናው ቀዘቀዘ "በማለት ሲጣሩ ከላይ ጣል ያደረጋት ጃኬት አውልቆና ነጠላጫማውን አጥልቆ ወደ ውጭ በመውጣት "መጣሁ እማማ "በማለት መለሰ።

ወደ ቤቱ በር በቀስታ እየተጠጋ በሩን ለወጉ ነካ ነካ አድርጎ አንገቱን በቅድሚያ አስገብቶ ሲያይ ሀይስኩል ላይ የተዋወቃት ሀሮት ሳትሆን ሌላ መልክ ያላት በእድሜ የምትበልጠው ሴት ከወይዘሮ የትናየት ጋር ተቀምጠው ቡናቸውን እየጠጡ ነበር ።

"ኡፍፍፍፍፍፍ "በማለት በረጅሙ ተንፍሶ "እማማ እንኳን ከልጅዎት በሰላም ተገናኙ "በማለት ሲናገር

ወይዘሮ የትናየት እየሳቁ "ውይ ብሩኬ ልጄ ሄኖንማ አልመጣችም የሚቀረኝ ትምህርት አለ በማለት ጓደኛውን ልካ ነው "በማለት መልሰውለት ተዳፍኖ የነበረው የብሩክ ጥርጣሬ መቀጣጠል ጀመረ

"ኧረ ተቀመጥ ከመንገድ አደል ምትገባው ?" በማለት አዲሲቷ እንግዳ ለብሩክ ቦታ አሳየችው

"እሺ አመሰግናለው " በማለት ወደተጠቆመለት ቦታ በመሄድ ሲቀመጥ ወይዘሮ የትናየት ወደ ብሩክ በመዞር "ምን አጠጥተው ቢልኩህ ነው እእንደዚህ ፈዛዛ የሆንከው ኧረ በእንግዳ ፊት ነህ ተጫወት ደግሞም ሄኖን ስጦታ ብላ እቃ ልካልሀለች ትወደዋለህ ብዬ አስባለው እንድትደውልላትም አደራ ብላሀለች " በማለት ከተቀመጡበት በመነሳት ወደ ጓዳ ሲገቡ እንግዳዋ

"ተጫወት" በማለት ለብሩክ የተቀዳለትን ቡና አቀረበችለት

"እሺ " በማለት ቡናውን ተቀብሎ አንዴ ፉት ካለ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን ዝምታ ለመስበር

"አንቺም ተማሪ ነሽ ? ማለቴ ከሄኖን ጋር " በማለት ጠየቃት

"አዎ ተማሪ ነኝ ግን ከሄኖን ጋር አይደለም አንድ አፓርታማ ላይ ነው የምንኖረው እሷ ወደዚህ ለመምጣት ስትዘጋጅ ድንገት የትምህርት ቤት ፍቃድ ከልክለዋት ያዘጋጃቸውን እቃዎች የሚወስድ ሰው አጥታ ስትቸገር እንደ እድል ሆኖ ከኔ ተገናኘን እኔም አዲስ አበባ ቤተሰብ ለመጠየቅ ለመምጣት እየተዘጋጀሁ ስለነበር እቃዋንም ይዤላት መጣሁ" በማለት ስትመልስለት

"ደግ ሰው ነሽ " አላት

"ኧረ አይደለም በሰው ሀገር መቸገርን ስለምፈራ ነው ደግሞም የአንድ ሀገር ልጆች ሆነን ?"

"እና የረዳሻት ኢትዮጵያዊ ስለሆነች ነው ? "

"በትክክል "

"ተሳስተሻል"

"እንዴት ?" አለች ፊቷን እየቋጠረች

"እማማ ምን ይላሉ መሰለሽ "

"እ"

"ደግነት ምክንያት አይፈልግም ይላሉ ደግ ለመሆን ምንም አይነት ምክንያት ማስቀመጥ አይኖርብሽም ሰው ከሆንሽ ይበቃሻል "

"አመንኩህ በቃኝ ካሁን በኋላ ያለምንም ምክንያት ደግ ለመሆን እጥራለው "

"እንደዛ ነው ሚባለው "በማለት ቡናውን ፉት ሲል ወይዘሮ የትናየት ከጓዳቸው ፌስታልና ቦርሳ በማምጣት "ይሄንን ልካልሀለች እኚህ ደሞ ልብሶች ናቸው" በማለት ፌስታሉን መሬት ላይ ቦርሳውን በእጁ ሲሰጡት ማመን አልቻለም ትምህርት በጀመረ ቀን በልጃገረዶችና በአንዳንድ አስተማሪዎቻቸው ትከሻ ላይ የማይታጣው ላፕ ቶፕ ነበር "እንዴ ?" በማለት በአግራሞት አፉን ያዘ ለምስጋናም ቃላት ሰላጠረው ምንም ቃል ሳይተነፍስ እየቀዘቀዘ የነበረውን ቡና በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው።

በል ደክሞሀል እረፍ ለሄኖን ሰልክ መደወል እንዳትረሳ እንግዳህንም ተሰናበታት ነገ ትመለሳለች ሰላሉት : ደጋግሞ እያመሰገነና አጎቱ "ትልቅ ምስጋና አድርሰልኝ" ያለውን በመናገር እንግዳዋን ተሰናብቶ ለሄኖን ምስጋና እንድታቀርብለት ተናግሮ ወደ ቤቱ ሊያመራ እግሩን ሲያነሳ ወይዘሮ የትናየት ከተቀመጡበት ደንግጠው በመነሳት "ቆይ ቆይ ብሩክ ባለፈው አገር ቤት የሄድክ ጊዜ አንድ ልጅ መጥቶ ይሄንን ወረቀት ለብሩክ

ስጡልኝ ብሎኛል ካልተሳሳትኩ ስሙ ጥላሁን ነው "በማለት ደብዳቤ ይዘውለት እንደመጡ ከእጃቻው ለቀም አድርጎ ወሰዶ ወደ ቤቱ ገባ።

የጥላሁን እጅ ፅሁፍ እንደሆነ አውቆታል ለማንበብ ቢያስቸግርም አነበበው የትምህርት እድል አግኝቶ አዲስ አበባ እንደሄደና ሊያየው ቢመጣም አገር ቤት እንድትመለስ ከወይዘሮ የትናየት መስማቱን ፤ አደራ ያለውን የማሳ ስራ አቋርጦ በመሄዱ ይቅርታ እየጠየቀው እንደሚወደውና ሊያየው እንደጓጓ አስፍሮበታል። ብሩክም ከጥላሁን ሀሳብ ጭንቀት "እፎይ" በማለት የተላከለት ላፕቶፕ ከከፈተ በኋላ ሀይስኩል እያለ በተማረው መንገድ አጠቃቀሙን በቀላሉ ለመደው ስልኩንም አንስቶ የሄኖንን ስልክ ካወጣ በኋላ በረጅሙ ተንፍሶ ደወለ።

"ሀሎ ሄኖን "

"ሄይ ብሩኬ how are you doing ?"

"ደህና ነኝ ስለላክሽልኝ እቃ በጣም አመሰግናለው ለትምህርቴ በጣም ያስፈልገኝ ነበር "

" don't worry ብሩኬ ቀለል አድርገው ማም family ጋር ሄደህ እንደነበር ነገረችኝ ሰላም ናቸው ?"

"ኣዎን ደህና ናቸው ፤ አንቺ ጋርስ ህይወት ፣ ትምህርት ጥሩ ነው?"

"Ya ጥሩ ነው አንድ ነገር ልጠይቅህ ብሩኬ ?"

"አዎን"

"ካላስቸገርኩህ እስቲ ስለ ቤተሰብህ ንገረኝ ስለ አባትህ እናትህ ስላንተም "

"እሺ ችግር የለውም እናትና አባቴ በህይወት የሉም ..... እናቴ ሁለት ታናናሽ እህቶቼን ስትወልድ ነው የአስር አመት ህፃን እያለሁ ያረፈችው አባቴም ከሶስት አመት በፊት ነው ህይወቱ ያለፈው ከአጎቴ እና ከአክስቴ ጋር እና ከሁለት መንትያ እህቶቼ ጋር ነው ምኖረው አሁን ግን ለትምህርት እዚህ እናንተ ከተማ መጥቼ ነው ያለሁት" በማለት ሲናገር ሄኖን እያለቀሰች መሆኑን አላስተዋለም ነበር

"ሰለ አባትና እናትህ አዝናለው Please ብሩኬ ሌላ ቀን እንገናኛለን " በማለት ሳግ እየተናነቃት መለሰች

ብሩክም "እንዴ ምን ተፈጠረ ? ለምንድነው ምታለቅሺው ?" ሲላት

"ብሩኬ እደውልልሀለው ቻው "በማለት ስልኩን ዘጋችው

ብሩክ ጥርጣሬው እውነት ወደመሆን እያደገ ይመስላል "ብሩኬ" በማለት የሚያቆላምጠው ሰው ቢኖር ሀሮት ብቻ ናት ብቻ ነገሩን ጊዜ ይፈታዋል ብሎ በማሰብ ሙሉ ትኩረቱን ትምህርቱ ላይ ማድረግ እንዳለበት አስቦ ለነገው ትምህርቱ አስፈላጊ ነገሮችን አዘገጃጅቶ ከቤት የተቋጠረለትን ምግብ በልቶ ወደ መኝታው ሄደ።

ጥቁሩ ካባ

ቀን ቀንን እየተካች ሳምንት ስትሆን ሳምንትም ሌሎች ሳምንቶችን እየወለደች ወር ስትሆን ብሩክ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት በማምጣት

የዲፕሎማ ወረቀቱን ለመቀበል የመጨረሻ ወር ፈተናውን እየጠበቀ ነበር። ባሳለፋቸው አራት ወራት ይህ ነው የሚባል የከፋ ችግር ሳይገጥመው የሊስትሮ ስራውን እየሰራ ትምህርቱንም በሚገባ እየተማረ ፤ የአገር ቤት ቤተሰቦቹ ደህንነት በስልክ እየጠየቀ ችግር ካጋጠማቸውም ከሚያጠራቅማት ትንሽ ብር እየቆነጠረ በመልእክተኛ እየላከ ፤ አንዳንዴ የምትደውልለትና ስለ ራሱ ጠይቃው በእንባ የምትሰናበተው የወይዘሮ የትናየት ልጅ ሄኖንን እያገኝ ፤ ከወይዘሮ የትናየት ጋርም ጊዜው ሲመቻችለት አንዳንዴ ወደ ገበያ አብሮ በመሄድ እቃ እየያዘላቸው እያገለገላቸው ነው ያለፉትን ወራት ያሳለፈው።

በቀጣይ ሳምንት የመጨረሻው የዲፕሎማ ትምህርት ፈተና ስለሚኖረው የሊስትሮ ስራውን አቁሞ ትምህርቱን በከፍተኛ ጥልቀት መከታተል ፣ ማንበብና ለፈተና መዘጋጀት ጀመረ።

እለት እለት ያለመታከት ከደብተሩ እና አንዳንድ መፅሀፎች ካሉበት ላፕቶፕ እየተፋጠጠ እንቅልፉን ቢረሳውም ለትንሽ ጊዜ መሆኑንና ነገ የተሻለ ቦታ እንደሚደርስ እያሰበ በእንቅልፍ እጦት የሚመጣበት ዱካክን ለማስወገድ ፤ እንቅልፍን ከራስ አይደለም ከሀገር የሚያባርረውን የወይዘሮ የትናየት ቡና እየተጎነጨ ለፈተናው ዝግጅቱን ቀጥሏል።

ወይዘሮ የትናየትም ቢሆኑ ለእንግዳ የወለዱት ልጅ እስኪመስል ድረስ እለት እለት ቡና በፔርሙስ እያመጡለት ያስቀምጡለታል ፤ በሌሎች ተከራዮችም ዘንድ የብሩክ ጥረትና ታታሪነት ስለሚደነቅ የወይዘሮ የትናየት እንክብካቤ አያስቀናቸውም ይልቁኑም እነሱ ለብሩክ ምንም ድጋፍ ባለማድረጋቸው የሚቆጫቸው ነበሩ።

****

የፈተናው ሳምንት ሊጀምር አንድ ቀን ሲቀረው ወይዘሮ የትናየት ብሩክን ወደቤታቸው ምሳ እንዲበላ ይጋብዙታል ፤ ብሩክም ያለማመንታት ግብዣውን ከተቀበለ በኋላ ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት ያመራል ፤ ወደ ቤቱ እንደገባም ለወትሮው መንፈስን በሚያነቃው መንፈሳዊ ዝማሬ የሚሞቀው ቤታቸው ጭር ብሏል

"እማማ ቲቪው ምን ሆነ ? ዛሬ ዝማሬ አልከፈቱም እኮ "በማለት መምጣቱንና የቤቱን ጭር ማለት ገለፀላቸው

"አይ ቲቪውማ ማታ ይቺ ድመታችን ከገመዶቹ እየተላፋች በአንዴ ጭጭ አለ ፤ እኔ እንደሆንኩ ምኑ ከምኑ እንደሚደረግ የማውቀው ነገር የለ እስቲ ምሳ እስከማቀራርብ ነካ ነካ አድርገው "ብለው ከጓዳ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስላዘዙት ከተቀመጠበት በመነሳት በሰፊ እና ውብ መደርደርያ ላይ ወደተቀመጠው ሰፊው ቲቪ አመራ

ከቴሌቪዥኑም ጀርባ በመሄድ የተነቃቀሉት ገመዶችን አንድ በአንድ ከሰካ በኋላ አንድ ገመድ ወደ መሰኪያው ስላልደረሰለት ሳብ ለማድረግ ቢሞክርም በመደርደሪያው ላይ ከተሰሩት መሳቢያዎች አንዱ ገመዱን ይዞበት ስለነበር ገመዱን ለማላቀቅ መሳቢያውን ከፈት ሲያደርግ የተመለከተው ፎቶ ሰውነቱ እንደ ድንጋይ ደርቆ እንዲቀር አደረገው እጁን በቀስታ ወደ መሳቢያው በመውሰድ የተመለከተውን ፎቶ ብድግ አድርጎ ትኩር ብሎ ተመለከተው

"ሀሮት ? እንዴት ሊሆን ይችላል ? "በማለት ከመሳቢያው ያወጣው ፎቶ

ላይ ፍጥጥ ብሎ ቀረ

"ዛሬ ምሳውን የሰራሁት እኔ ነኝ ትወደዋለህ ሰራተኛዬ ደሞ ቡና እንድታፈላ ነግሬያታለው "በማለት ወይዘሮ የትናየት ከጓዳ እየገቡ ቀና ሲሉ ብሩክ በልጃቸው ፎቶ አፍጥጦ ፈዞ ቀርቷል

ቀበል አድርገውም "ቲቪው አስቸገረህ አይደል ? ተወው ጦስህ ይውሰድ እጅህን ታጠብና ና ደሞ ምንድነው የያዝከው ?" በማለት ከገባበት የሀሳብ ባህር ለማውጣት ሞከሩ

ብሩክም እየተንተባተበ "እማማ ...ይይይይቺ ልጅ ሀሮ... ማለቴ ሄኖን ናት ?" እያለ ፎቶውን ወደ ወይዘሮ የትናየት አዞረው

በመንተባተቡ ግራ የተጋቡት ወይዘሮ የትናየትም ያመጡትን እንጀራ እያስቀመጡ "አዎን ልጄ ሄኖን ናት አይ የዘንድሮ ወጣት ,ይሄን ጊዜ ሁሉ በስልክ የምታዋራት ልጅ አንድ ቀን ፎቶዋን ሳትጠይቀኝ በራስህ ጊዜ አገኘኸው አይደል ?"

በማለት ሲመልሱለት ፎቶውን ወደ ነበረበት መልሶ ያጠረውን የሶኬት ገመድ እየሰካና ላለመንተባተብ እየሞከረ "አይገርምም እስከዛሬ ፎቶዋን ሳላይ ?" በማለት ድንጋጤውን ደብቆ ቲቪውን እያበራ ወደ ሶፋው በዝግታ ተመለሰ

"እጅህ ይባረክ ሰራኸው ? "እያሉ ቀና ብለው ወገባቸውን ይዘው ቲቪውን መመልከት ሲጀምሩ

"ቀላል ነገር እኮ ነው ሶኬቶቹ ተነቅለው ነበር "እያለ የወትሮው ዝማሬ በሚጠብቅ እይታ ወይዘሮ የትናየትን እየተመለከተ መቆጣጠሪያውን ሰጣቸው

ወይዘሮ የትናየትም መቆጣጠሪያውን ተቀብለው ብሩክ የፈለገውን መንፈሳዊ ዝማሬ በመክፈት ለሰራተኛቸው ውሀ እና ሳህን እንድታመጣ በማዘዝ ወደ ሶፋው እየተቀመጡ

"እኔ ምልህ ብሩክ ከሄኖን በስልክ እያወራችሁ ነው ?" በማለት መልሱን በጉጉት በመጠበቅ ጠየቁት

"አዎን እናወራለን ግን ብዙ ጊዜ ስለ እኔ ትጠይቀኝና ትንሽ ነገር ከነገርኳት በኋላ እያለቀሰች ስልኩን ትዘጋዋለች ምን እንደሆነ ግራ ገብቶኛል "እያለ አንገቱን ደፍቶ እጆቹን አሻሸ

"ልክ ነህ ለኔም ትነግረኛለች ሀይስኩል እያለች ልክ እንዳንተ ብሩክ የሚባል የልብ ጓደኛ ነበራት ታሪካችሁም ተመሳሳይ ሲሆንባት ነው ያሳለፉት ትዝታ እየመጣባት ስልክ ምትዘጋብህ "

ብሩክም አይኑን ፍጥጥ አድርጎ "ቆይ እማማ እኔም እኮ ሀይስኩል ላይ ልክ እንደርሷ አይነት ጓደኛ ነበረኝ ግን የተለያዩ ናቸው የሀይስኩል ጓደኛዬ ሀሮት ስትሆን የእርስዎ ልጅ ግን ሄኖን ናት "እያለ ምላሹን በጉጉት ጠበቀ

ወይዘሮ የትናየትም "በእየሱስ ስም ቆይ ጠብቀኝ አንዴ "በማለት ወደ ቲቪው ሄደው መሳቢያ ከከፈቱ በኋላ ወረቀት ማገላበጥ ጀመሩ

ይሄን ጊዜ ብሩክ "ሀሮት ... ሄኖን ማን ነሽ አንቺ አስጨነቅሽኝ "እያለ ጣቱን እያፍተለተለ በልቡ ተናገረ

ወይዘሮ የትናየትም ብዛት ያላቸው ወረቀቶችን ይዘው በመምጣት "እነዚህን ተመልከት እስቲ ከዛም ሁሉም ይገባሀል "በማለት ወረቀቶቹን ዘረጉለት

ወረቀቶቹን ተቀብሎ ሲመለከት የትምህርት ቤት የክፍል መሸጋገርያ

ወረቀቶች ነበሩ ሁሉም ወረቀቶች ላይ "ሀሮት ክፍሌ" የሚል ፅሁፍ ተፅፏል ከወረቀቶቹ ራሰጌ ላይም ውቧ ሀሮት እንዳማረባት ፎቶዋ ተቀምጧል

አሁንም ብሩክ እየተርበተበተ ቆመው የሚያዩትን ወይዘሮ የትናየትን "እና .... ሀሮት ....ሄኖን የእርስዎ ልጅ ናት ?" በማለት በተቀመጠበት ቀና ብሎ ጠየቀ

"አዎን አጋጣሚው በጣም ደስ ይላል ፤ ሀሮት ለትምህርት ቤቷ የምትጠቀመው ብዙዎች የሚጠሩባት ስም ሲሆን ሄኖን ደግሞ እኔ ያወጣሁላት ስም ነው ስላንተ ባለፈ የመጣው ጓደኛህ ጥላሁን የመጣ ጊዜ ነግሮኛል ፤ ሄኖንዬ የምታወራው ስላንተ ነው ፤ ሁሉም በጊዜው ውብ አድርገህ የሰራ ጌታ ምን ይሳንሀል ፤ለሄኖንም ደግሞ እኔው ራሴ ቀስ ብዬ አስረዳታለው አይ አምላኬ ምን ይሳንሀል ? ሁሉ በእጅህ ነው " እያሉ ወደ ላይ አንጋጠው ካመሰገኑ በኋላ የሰጡትን ወረቀት ለመቀበል እጃቸውን ሲዘረጉ

ብሩክ በአግራሞት ወረቀቱን እየሰጣቸው " እና ሄኖን ሀሮት ናት ?" እያለ የውስጡን ልክ ያጣ ደስታ የሚገልፅበት ምክንያት አጥቶ ለወይዘሮ የትናየት ሲጠይቃቸው "አዎን ሄኖን ሀሮት ናት " በማለት ሳቅ እያሉ ወደ መደርደሪያው ተመለሱ ።

ምሳቸውን እየተደሰቱ እና እየተጨዋወቱ ከበሉና ቡናቸውን ከጠጡ በኋላ ብሩክ " እማማ ሰሞኑን እንቅልፍ ስላልተኛሁ ገብቼ ልተኛ ነገ ደግሞ የፈተና ቀን ስለሆነ አካሌን ላሳርፈው " በማለት ሲጠይቃቸው

"እሺ ልጄ አደራህን ለሄኖን ያ ብሩክ መሆንህን ድንገት እንዳትነግራት ልጄ ድንጉጥ ናት የሆነ ነገር ትሆንብኛለች እሺ አደራህን እኔ ቀስ ብዬ እነግራታለው ፤ በል ሂድ መልካም ፈተና ይሁንልህ " በማለት በስስት አይን

እየተመለከቱ ሲያናግሩት ሆዱ የባባው ብሩክ "እሺ እማማ እንዳሉት አደርጋለው "በማለት ወደ ቤቱ ሄደ ።

በደስታ ሲቃ የተናነቀው ብሩክ "ሀሮት ናፍቀሽኛል "እያለ ስልክ ለመደወል ቢፈልግም በስሜት ተገፋፍቶ የወይዘሮ የትናየት አደራን እንዳይጥስ ስለፈራ ፍራሹ ላይ በመተኛት ትራሱን ከጭንቅላቱ በማሸሽ እቅፍ አድርጎ እረፍት ለማድረግ አሸለበ።

****

የፈተና ውጤት መግለጫው ቀን ስለደረሰ በጉጉት ውጤቱን ለማየት በጠዋት ወደ ትምህርት ቤቱ ነበር የገሰገሰው : ፈተናውን ሲሰራ የከበዱት ጥያቄዎች መኖራቸው ትዝ አይለውም ግን ውስጡ በፍርሀት ተሞልቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የማስታወቂያ ሰሌዳ ከሩጫ በማይተናነስ እርምጃ ደረሰ ።

ፍርሀቱ ስለጨመረ ከታች ወደ ላይ ስሙን ሲፈልግ በስድስተኛ ረድፍ የራሱን ስም አገኘ በልቡም "ስድስተኛ ይበቃኛል ጥሩ ውጤት ነው "እያለ በድጋሚ ወረቀቱን ሲመለከት የወረቀቱ ቅደም ተከተል በስም እንጂ በውጤት ደረጃ ስላልተቀመጠ ወረቀቱን ትኩር በማለት ሲመለከት "ብሩክ ፈይሴ አማካይ 100 "የሚለው ፅሁፍ ላይ ላይኑ እንዳረፈ አቶ ግርማቸው ብሩክን ተመልክተው ከቢሮአቸው እየወጡ

"ብራቮ ብሩክ እድሉን ላንተ በመስጠቴ ኮርቻለው በታሪክ እንደዚህ አይነት ውጤት አላየንም ብራቮ "እያሉ በመጠጋት ከከሻውን መታ መታ እያደረጉ "ሌላ መልካም ዜና አለህ ና ወደ ውስጥ እንግባ "እያሉ እጁን ይዘው ወደ

ቢሮው አስገቡት

"ስላመጣኸው ውጤት ኮርቼብሀለው ታታሪ ነህ ለብዙዎችም ምሳሌ የምትሆን ልጅ ነህ "

"አመሰግናለው"

"የፊታችን ቅዳሜ ሁለት ሰአት እዚህ ግቢ የምቃርት ስነስርአት ስለሚኖር በጊዜ ትመጣለህ "

"እሺ"

"ሌላው ይህንን የዲፕሎማ ትምህርት በከፍተኛ ውጤት ላጠናቀቁ ሰዎች የተዘጋጀ ነፃ የትምህርት በዲግሪ እና ማስተርስ መርሀ ግብር በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ስለተዘጋጀ በሚመጣው ወር በመሄድ ትምህርትህን መጀመር ትችላለህ እነዚህንም በሚገባ ካጠናቀቅክ ምናልባት የውጭ ሀገር ነፃ የትምህርት እድል ልታገኝ ትችላለህ ደሞም እተማመንብሀለው እድሉን ታገኛለህ እስከዛው የቤት ኪራይ እና የተለያዩ አስፈላጊ ሰራዎችን መጨረስ ይኖርብሀል። በሚያስፈልግህ ነገር ሁሉ ትምህርት ቤቱ ከጎንህ ይቆማል እኔም ከጎንህ ነኝ ።" በማለት የምስራቹን አበሰሩት ።

ብሩክም የደስታ እንባ ከአይኑ እየጠረገ በረጅሙ ተንፍሶ "አመሰግናለው " በማለት ሲመልስ አቶ ግርማቸው ቀበል አድርገው

"አይዞህ የምን ማልቀስ ነው ገና ብዙ ታሪክ ትሰራለህ " እያሉ ለማበረታታት ሞክረው የነፃ ትምህርት የፍቃድ ደብዳቤውን እየፃፉ የግል ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመሩ

"አዲስ አበባ ዘመድ አለህ እንዴ ?"

"አይ የለኝም " በማለት ከመለሰ በኋላ አባቱ ከመሞቱ በፊት 'በፈተና ጥሩ

ውጤት ካመጣህ ' በማለት ወደ አዲስ አበባ የሚጠቁም ወረቀት እንደ ሰጡት ትዝ ሲለው ምናልባት የዘመድ ቤት ጠቁሞኝ ይሆናል በማለት "አው ...ማለቴ ይኖራል "

"ኦው ጥሩ ነዋ ! ብዙም የምትቸገር አይመስለኝም " በማለት ፅፈው የጨረሱት ወረቀት ላይ ማህተም አሳርፈው ወረቀቱን በጥንቃቄ እንዲይዝ አስጠንቅቀው ተሰነባበቱ።

****

"እማማ ...እማማ "

"አቤት ማነው?"

"እኔ ነኝ ብሩክ "

"ምነው ልጄ በሰላም "

"አዎን እማማ የምስራች !"

"ምስር ብላ ምን ተገኘ ?"

"ፈተናውን በአንደኝነት ጨርሼ የነፃ ትምህርት እድል አዲስ አበባ ላይ አግኝቻለው "

"እሰይ ! አምላኬ ምን ይሳንሀል እሰይ ! ና ሳመኝ ምን ያፈዝሀል እሰይ ! እሰይ !"

የወይዘሮ የትናየት እና የብሩክ ንግግር የሰሙ ተከራዮች ከቤቶቻቸው ብቅ

ብቅ እያሉ ለብሩክ "የእንኳን ደስ ያለህ " ምኞት አስተላልፈውለት ተመልሰው ገቡ ።

ጊዜ ሳያጠፋም ሀገር ቤት ላለችው አክስቱ በመደወል የሆነውን ሲነግራቸው በደስታ ብዛት ስልኩን ሳይዘጉ እልልታቸውን አቅልጠው በምርቃት ማዕበልም አጥለቀለቁት።

የተናፈቀችው የምርቃት ቀን የሆነችው ቅዳሜ ደረሰች ብሩክ ይህቺን ቀን በከፍተኛ ጉጉት ይጠብቃት ነበር ወላጅ እናትና አባቱ ከጎኑ ቆመው የልፋታቸውን ዋጋ ቢያዩ ደስታው ነበር ነገር ግን እንደ እናት የሆኑለት ወይዘሮ የትናየት ምንም መጥፎ ስሜት እንዳይሰማው በማሰብ አብረውት ለመሄድ እየተዘገጃጁ ነው ከሄኖን የተላከለት ነጭ ሸሚስ እንዲሁም ጥቁር የሱፍ ሱሪ በጥቁር ቆዳ ጫማ አድርጎ ከቤቱ በመውጣት ወይዘሮ የትናየትን ወደ ምርቃት ቦታው ለመውሰድ

 "እማማ አልጨረሱም ?" በማለት እየጠየቀ ወደ ውስጥ ገባ

ወይዘሮ የትናየትም ነጭ የሀበሻ ልብስ ለብሰው የእጅ ቦርሳቸውን እያነሱ "ጨርሻለው ና እንሂድ " በማለት ቀና ብለው እያዩት "ቱፍ ቱፍ ከአይን ያውጣህ ልጄ ሸበላ ሆነህ የለ?" እያሉ የሸሚዙን ኮሌታ ካስተካከሉ በኋላ ተያይዘው ከግቢው በመውጣት ወደ ትምህርት ቤቱ አቀኑ።

ወደ ትምህርት ቤቱ ዘግይተው ስለደረሱ ፕሮግራሙ ተጀምሮ ነበር የጠበቃቸው : የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ኣቶ ግርማቸው የአዳራሹ በር ላይ ቆመው ሰአታቸውን እየተመለከቱ እየተቁነጠነጡ የእነ ብሩክን መምጣት ሰላዩ በፍጥነት በመሄድ

"አረፈዳችሁ እኮ በሉ እማማ እርስዎ እኔን ይከተሉኝ አንተ ደግሞ ያኛው ክፍል ላይ "እያሉ በጣታቸው እየጠቆሙ " የቀረ ጋወን አለ በስነ ስርዓት

ለብሰኸው ና "በማለት እያዋከቡት ወይዘሮ የትናየትን በዝግታ ይዘዋቸው ገቡ

ብሩክ ወደተጠቆመው ክፍል በመሄድ ጋወኑን አጠለቀ ኮፍያውንም ደፋ ከፊት ለፊቱ በሚታየው መስታወት ራሱን ትኩር ብሎ እያየ "አባዬ ቃልህን ጠብቄ ጥሩ ውጤት አምጥቼ ጥቁር ካባ ደርቤያለው "በማለት ኮስተር ብሎ መስታወቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶ ወደ አዳራሹ አቀና።

የእለቱ የምረቃ ስነስርአት በተለያዩ አዝናኝ ጨዋታዎችና በትምህርት ቤቱ ሀላፊዎች ንግግር እየተከናወነ ቀጥሎ በመጨረሻ የተማሪዎች የእውቅና እና የሽልማት ጊዜ ስለደረሰ ሁሉም ትኩረቱን ወደ መርሀ ግብር መሪው አደረገ የተለያዩ የእውቅና ሽልማቶች ለተለያዩ ሰራተኞች ከተበረከተ በኋላ ድምፅ ማጉያውን ይበልጥ እንዲህ ወደ አፉ እያስጠጋ

"ለስድስት ወር በዲፕሎማ መርሀ ግብር ሲሰጥ በነበረው የአስተዳደር ስልጠና በታሪክ ከፍተኛውን ውጤት የሆነውን አማካይ ውጤት አንድ መቶ በማምጣት አንደኛ በመሆን ትምህርቱን ያጠናቀቀው ተማሪ....."እየተባለ ሲነገር ወይዘሮ የትናየት ስልካቸውን አውጥተው መቅረፅ ጀመሩ

"ብሩሩሩክክ ፈይሴ "

ሰፊውን አዳራሽ ያጨናነቁት ተማሪዎች ፣ የተማሪ ወላጆች እና ጓደኛዎች ከተቀመጡበት ለአክብሮት በመነሳት በጭብጨባቸውና በፉጨታቸው አዳራሹን አናወጡት።

ብሩክም ፈገግ በማለት ከተቀመጠበት ተነስቶ በግርማ እየተራመደ የምስክር ወረቀቱን ተቀብሎ ከመድረክ ወረደ። የምርቃት ስነ ስርዓቱ ሲጠናቀቅ ወይዘሮ የትናየት እቅፍ አድርገው ከሳሙት በኋላ "እንኳን ደስ አለህ" በማለት አበባ አሳቀፉት አቶ ግርማቸውም በጠንካራ እጃቸው

እያቀፉት "በርታ" በማለት አበባ እና ደብዳቤ ሰጡት አበባውን ተቀብሎ ደብዳቤውንም በኪሱ ከትቶ የፎቶ ስነስርዓት ለማድረግ ከወይዘሮ የትናየትና ከክፍል ጓደኞቹ እንዲሁም ከአቶ ግርማቸው ጋር ተሰበሰቡ።

ቃል

ከምርቃት ስነስርዓቱ ከተመለሱ በኋላ ወይዘሮ የትናየት ወዳዘጋጁት የምሳ ፕሮግራም ሁሉም ተከራይ ተሰብስቦ ጨዋታ መድመቅ ከጀመረ ቆይቷል ወይዘሮ የትናየትና ሰራተኛቸው ተከራዮቹን ለማስተናገድ ጉድ ጉድ በማለት አቅም ስላነሳቸው ብሩክ ለማገዝ ሸሚዙን እየሰበሰበ ወደ ወይዘሮ የትናየት እየሄደ

"እማማ ስራ ይስጡኝ ላግዝዎት እንቢ እንዳይሉኝ " ሲላቸው

" ተው ልጄ በምርቃትህ ቀን መስተናገድ ሲገባህ እንደ እኛ ኩሽና ለኩሽና ዞረህ ጪስ ጪስ ልትል ነው በል አርፈህ ተቀመጥ " በማለት ቆጣ ሲሉት ብሩክ ፈገግታ እያሳያቸው "እይሆንም እማማ ላግዝዎት " እያለ ወይዘሮ የትናየት ሊያነሱት የነበረውን እጅ ማስታጠቢያ ውሀ በማንሳት ወደ ተስተናጋጆቹ ሲሄድ ወይዘሮ የትናየት ካገነበሱበት ቀና እያሉ "እይ አንተ እንዴት የተባረክ ልጅ ነህ " በማለት ሲመልሱለት በፈገግታ ዞር ብሎ ተመልክቷቸው እጅ ማስታጠብ ጀመረ።

****

ቀኑ በጣም ደስ ይል ነበር ከልጅነቱ ጀምሮ ሲመኘው የነበረው ለማሳካት የስኬት ቁልፎቹን አንድ በአንድ መክፈት ጀምሯል። በተለይ ወይዘሮ የትናየት የሚያደርጉለት እንክብካቤ እና ውለታ በምን መመለስ እንደሚችል በማሰብ መብሰልሰል ከጀመረ ብዙ ጊዜ ቢሆነውም የዛሬው ግን ፈፅሞ ባልጠበቀው መልኩ ምርቃቱን የግቢውን ተከራይ በሙሉ ሰብስበው በማክበራቸው ውለታው መመለስ የማይችለው ሆኖበታል።

በትንሿ ክፍሉ ውስጥ ሆኖ ከወይዘሮ የትናየትና ከአቶ ግርማቸውና የተበረከቱለት ሁለት ጥቅል አበቦችን ቁልቁል እየተመለከተ "አባዬ ቃልህን እየጠበኩ ነው መንገዱን ጀምሬዋለው ዞራንም እታገለዋለው ያሳደገኝ ማህበረሰብንም እለውጠዋለው ቃል እገባለው " በማለት የደከመው ሰውነቱን ለማሳረፍ ልብሶቹን ማወላለቅ ሲጀምር ዳይሬክተሩ አቶ ግርማቸው የሰጡት ደብዳቤ ከሱሪው ኪስ ወደቀ : ብሩክም የአቶ ግርማቸው ደብዳቤ መሆኑን አውቆ ደብዳቤውን ከወደቀበት በማንሳት ከፍቶ ማየት ጀመረ ደብዳቤው እንደጠበቀው ትልቅ ወረቀት አይደለም ብዙም የተፃፈበት ነገር የለውም ግራ በመጋባት ወደ አንደኛው ጎን ሲገለብጠው የብሩክ ትምህርት ቤት ሰም ፣ አሰር ሺህ ብር እና የአቶ ግርማቸው የእጅ ፊርማ ተመለከተ።

"ኦ ውውውው አሰር ሺህ ብር ?" በማለት ገንዘቡን በድጋሚ ተመለከተው ከትምህርት ቤቱ የአሰር ሺህ ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጎለት ገንዘቡን በማናቸውም ሰዓት ወደ ባንክ በመሄድ ማውጣት እንዲችል የተሰጠው ቼክ ነበረ።

ስለ ገንዘቡ አወጣጥና አያያዝ እውቀቱ ውስን የሆነው ብሩክ ሱሪውን መልሶ እየታጠቀ ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት በመሄድ የተሰጠው ቼክ እና

እንዴት ማውጣት እንዳለበት ሲጠይቃቸው የባንክ ደብተር ማውጣት እንዳለበትና ገንዘቡ ባንክ እንዲቀመጥ ማድረግ እንደሚቻል ተነጋግረው ለነገ ቀጠሮ በመያዝ ተሰነባበቱ።

****

ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል ከጥቂት ወራት በፊት ገጠር እንስሳትን በማገድ ላይ የነበረው ብሩክ ዛሬ ታሪክ ተቀይሮ ባለ ዲፕሎማ ለመሆን በቅቷል ፣ ለአገር ቤት ላሉት ቤተሰቦቹ እና ትናንሽ እህቶቹ ምን መያዝ እንዳለበት ነጋሪ አያስፈልገውም ምክንያቱም ከአምስት ወራት በፊት ምን ይዞ ሄዶ ምን እንደጎደለ ተመልክቷልና።

ዛሬ ግን ውስን ሻንጣዎችን አልያዘም ቤት ለቆ የሚወጣ ይመስል እንደ ከበሮ የተወጠሩ ሁለት ትላልቅ ቢጫ ፌስታሎችና ትልቅ ጥቁር ሻንጣ በማዘል እንደለመደው ወይዘሮ የትናየትን ለመሰናበት እና ሀገር ቤት ለመሄድ በራፍ ላይ ቆሟል

"እማማ "

"አቤት ማነው ?"

"እኔ ነኝ "

"ውይ ብሩክ ለመሄድ ተነሳህ ? " በማለት የቤታቸውን ደረጃ እየወረዱ ተጠጉት

"አዎን እማ መሄዴ ነው ልሰናበትዎት ብዬ ነው "

"እሺ ልጄ መቼ ትመለሳለህ ?"

"ምናልባት ከሶስት ሳምንት በኋላ "

"ብዙ ትቆያለት ማለት ነዋ "

"አዎን እማማ በሉ ልሂድ ምናልባት ወደዚህ የማልመጣ ከሆነም ስልክ ደውዬ አገኛችኋለው ፤ ደግሞ እማማ በቆይታዬ መመለስ የማልችለው ውለታ ውለውልኛል የምታመልኪው እሱ ይክፈልሽ እውነት እማማ ከልብ ነው ማመሰግነው የእናቴን ምስል በእርስዎ ኣይቻለው የዋህ ፣ ቅን ፣ሩህሩት ፣ተግባቢ ፣ደግ ፣ አሳቢ ናችሁ በጣም በጣም አመሰግናለው " በማለት ሲያወራ ሳያስበው የእንባው ዘለላዎች ጉንጩን ተንተርሰው እተንዘረገጉ ከመሬት ተላተሙ

ሆደ ቡቡዋ ወይዘሮ የትናየትም እንባ እየተናነቃቸው "ተው ልጄ አታልቅስ " በማለት ተቃቅፈው ከተላቀሱ በኋላ የቀሪ ቤት ኪራይ ክፍያ በባንክ ባሳዩት መንገድ እንዳስገባላቸውና ከቻለ ተመልሶ እንደሚመጣ ተናግሮ የኋሊት እየተጓዘ ከግቢው ወጣ።

ወይዘሮ የትናየትም "ልጄ ከሄኖን ተደዋወሉ እሺ አደራህን : በል ሂድ እግዚአብሔር ከፊትህ ይሁን " በማለት መርቀው በረጅሙ ተንፍሰው ወደ ቤታቸው ደረጃውን እየወጡ ገቡ።

****

ከአምስት ድፍን ወራት በኋላ የተገናኙት ታናናሽ መንትያ እህቶቹ ባመጣላቸው የትምህርት መፅሀፍ ደብተርና እስክሪብቶ ስዕል እየሳሉ

ፊደል መፃፍ እየተለማመዱ እየተጫወቱ ነው ናፍቆቱ ባይወጣላቸውም የልጅ አዕምሮ ነውና ባመጣላቸው እቃዎች መጫወትና መደሰትን መርጠዋል።

አጎትየውም ቢሆን የመጀመሪያው ቀን ላይ ብዙ አውርተው ቢጨዋወቱም በቀጣይ ቀናቶቹ ባህሪው አስቸግሮታል ነገር ግን ከመጣ ጊዜ ጀምሮ የምታጫውተውና የሆድ የሆዷን የምትነግረው አክስቱ ከጎኑ አልተለየችም ነበር ባሳለፉት አምስት ወራትም ምን እንዳጋጠማቸው ምን አዲስ ነገር እንደተፈጠረ ትዘከዝክለታለች : በማሳው ላይ በቅለውና አፍርተው የነበሩት በቆሎዎች ብዙ እንደጠቀማቸው ወደ ገበያ አውጥተው ሸጠው ገንዘብ ማግኘታቸው ፤ በመንደሩ የዞራ መንፈስ አለቃ አቶ መኮንን ትዕዛዝ አማካይነትም ላሞቻቸው ለግብር እንደተሰጡና አሁን አራት ላሞች ብቻ መቅረታቸው እንዲሁም እንደኛዋ ታናሽ እህቱ በጠና ታማ እንደነበርና ወደ ባህል ሀኪም ተወስዳ ለውጥ ማሳየቷ ሎሎችም የተፈጠሩ አዳዲስ ነገሮች ነግራዋለች።

ብሩክ ዞራ የሚባለው የውሸት መንፈስና ተዋናዩ አቶ መኮን በመንደሩ ማህበረሰቦች ላይ ተፅኖ ማሳደር መቀጠላቸው ተረድቷል በብሩክ መማር ምክንያትም የተናደዱት አለቃው አቶ መኮንንም በቤተሰቡ ላይም መች ምን ጉዳት እንደሚያደርስ ሰለማይታወቅ በቀጣይ ቀናትም ሙሉ ቤተሰቡን በማሳመን ይኖርበት ወደነበረው ከተማ ተለቅ ያለ ቤት ተከራይቶ ቤተሰቡን ከመንደሩ ለማውጣት አስቧል በመሆኑም ሁሉንም አንድ በአንድ በማሳመን ሀሳቡ እንዲሰምር ጥረት ጀምሯል።

በቅድሚያ የሄደው ወደ ትናንሽ እህቶቹ ነበር ትምህርት መማር እንደሚጀምሩ ፣ ከተማ የተሻለ እንደሆነ ፣ ጥሩ ጥሩ ሰዎች እንዳሉ ፣ ብዙ ጓደኛዎች እንደሚያፈሩና መዝናኛ ቦታ እንዳለ እነሱም ሄደው እንደሚዝናኑ

እያባበለ መልካም መልካሙን ስለነገራቸው በደስታ ለመቀበል አላንገራገሩም ።

በመቀጠል ወደ አክስቱ በመሄድ ያሰበውን ሁሉንም ተናግሮ ገቢ ማስገኛ የሆነ የንግድ ሀሳብ እንደማይጠፋ ሲነግራቸው የመንደሩ ሰው ነበልባል አፍ ፣ የአቶ መኮንን ዛቻ እና ተደጋጋሚ ቁጣ እና የተሻለ ኑሮ ለመኖር የቤተሰቡ መሄዱን ቢወዱትም ደግና የዋህ የሆኑትን ጎረቤቶቻቸው ጥለው ላለመሄድ ግን የተቃውሞ ሀሳብ ቢያቀርቡም ብሩክ ሌሎች ደግና የዋህ ጎረቤቶች ማፍራት እንደምትችልና በየጊዜው እየመጡ መጠየቅ እንደሚችሉ አሳምኖ ባህሪው እየከበደው የመጣውና ቁጡ የሆነው አጎቱን ለማሳመን ምቹ ቀን ጠብቆ አናገረው።

"አጎቴ " በማለት በተለሳለሰ አነጋገር ቀረበው

"ኧ አንተ ኩታራ ምነው ?"

"የዚህ የገጠሩ ኑሮ ግን ወደኸዋል ?"

"እንዴታ ! ምስጋና ለዞራ ይግባው ቀላል ወድጄዋለው "

ዙርያ ገባው የታጠረበት ብሩክም አሰብ አድርጎ " ግን እኮ እኔ ያለሁበት ከተማ ከዚህ ኑሮ የሚሻል ኑሮ አለ በተለይ ..." በማለት ለመቀጠል ሲሞክር

" አንት ኩታራ ምኑ ነው ሚሻለው ? ዞራ በሌለበት በረከት የለም ፣ ዞራ በሌለበት ደስታ የለም ኧ ትሰማለህ ? ዞራ ምቾታችን ነው ደግሞ ምን እንዳሰብክ ሰምቻለው ወዴትም ንቅንቅ የለም ! " በማለት እየተቆጡ መለሱለት

ብሩክ ቆሸቱ እርር ድብን ቢልም እየተረጋጋና የአጎቱን ትከሻ በሁለት እጁ

እየያዘ በተለሳለሰና ለማሳመን በሚመች አነጋገር "አጎቴ የወንድምህ አደራ የሆኑት እነዚህ ልጆች አምሮባቸውና ትምህርት ተምረው አድገው እንዲለወጡ አትፈልግም ? እህትህስ ብትሆን በጪስ የሚቃጠለው አይኗ በሸክም የሚጎብጠው ወገቧ የዛለው ጉልበቷ አያሳዝንህም ? አንተስ ብትሆን : የተሻለ ኑሮ አይናፍቅህም ? ግድ የለህም ሁሉንም እኔ አስተካክላለው አንተ ብቻ ከእኛ ጋር ለመምጣት እሺ በል "በማለት አይን አይኑን እያየ ሲያናግረው

ትከሻው ላይ የተጫነበት የብሩክ ሁለት እጆችን በእጁ በቀስታ እያወረደ ጠበቅ አድርጎ በመያዝ በረጅሙ እየተነፈሰ " የአባትህ አደራን አታንሳብኝ አደራ በልቻለው ፤ ደግሞስ እኔ የዚህ ቤት ኑሮ እንዳይለወጥ የምፈልግ ይመስልሀል ? የያዘ ይዞኝ እንጂ በል የአባትህን አደራ ፈፅም አክስትህንም ለልጆቹ ታስፈልጋቸዋለች ውሰዳት እኔ ግን ከዞራ ተለይቼ መኖር አልችልም ተወኝ እነሱ ከተሰማሙ ፍቃድ አልከለክልህም እኔ ለማሳውና ለከብቶቹ እበቃለው ዞራ ይርዳህ "በማለት እጁን ጨመቅ አድርገው ሲመልሱለት የሌላ ሰው ንግግር ነው እንጂ በፍፁም የአጎቴ ንግግር አይደለም በማለት ትኩር በማለት ሲመለከተው አንገቱን ከታች ወደላይ አነቃንቆ ወደ ራሱ ሳብ በማድረግ ካቀፈው በኋላ "ዞራ ይርዳህ ልጄ አደራህን ጠብቅ "እያለ ከግቢው ወጣ ።

ብሩክ ደስታው ወደር አጥቷል መቼም ቢሆን የማይጠብቀው ንግግርና መልስ ከአጎቱ በማግኘቱ እየተደሰተ የሚከራይ ቤት ፍለጋ እና ወይዘሮ የትናየትን ለመጠየቅ ወደ ከተማው አቀና።

****

ከተማው ያለወትሮው ጭር ብሏል መንገድ ላይም የሚታዩ ብዙ መኪናዎች የሉም አልፎ አልፎ ከሚታዩት ክፍት ሱቆች በስተቀር ሱቆቹም ተዘግተዋል መንገዶቹም ላይ ሰዎች አይታዩም ብሩክም ግራ በመጋባት ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት የሚወስደውን መንገድ በመከተል አስፓልቱን ተከትሎ ሲሄድ ብዛት ያላቸው ወጣቶች የተለያዩ መፈክሮችን በመያዝ እየጮሁ ከፊት ለፊቱ ሲመጡ ተመለከተ።

ለእንደዚህ አይነት ሁኔታ እንግዳ የሆነው ብሩክ በቀስታ እየተጓዘ ወደ ሚጓዙት ወጣቶች ሲደርስ "ለማ ሌባ ነው "፤ "ለማ ከስልጣን ይውረድ"፤ "ለማ በህግ ይጠየቅ"፤ "የተዘረፈው የህዝብ ገንዘብ ይመለስ "እያሉና እጆቻቸውን ጨብጠው ወደ ላይ እያነሱ ከአጠገቡ አለፉ በወቅቱ የወጣቶቹ ቁጥር ከፍተኛ ስለነበር እነሱን ለማሳለፍ በፍጥነት ወደ መንገዱ ጠርዝ የሄደው ብሩክ ተደናቅፎ የወይዘሮ የትናየት ስጦታ የነበረው ሰፊው ስልክ አስፓልቱ ላይ ጣለው።

"ለማ .... ለማ .... ለማ "ይሄ ስም ለብሩክ አዲስ አይደለም ያኔ በዝናብና በረዶ ተደብድቦ አቶ መኮንን ቤት በረንዳ ላይ በወደቀ ጊዜ ከአቶ መኮንን ጋር በመንደሩ ሰዎች ላይ ሲያላግጥ የነበረው የከተማው አስተዳዳሪ ስም ነበር። ወጣቶቹን ላፍታ ዞር በማለት ከተመለከተ በኋላ "አይ ለማ እዚም ትሰርቃለህ ?" በማለት እያፌዘና የተሰበረው የስልኩ ገፅታ እየተመለከተ ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት አመራ።

ወይዘሮ የትናየት የታጠቡ ልብሶቻቸውን እያሰጡ ብሩክ በሩክ ከፍቶ ሲገባ ቀድሞ ስለተመለከታቸው "እማማ ልጅዎት መጥቷል "በማለት ፈገግ እያለ ወደ ውስጥ ሲገባ ወይዘሮ የትናየት ሰራቸውን ትተው ወደ ብሩክ ፈጠን በማለት በመሄድ "አንተ ጥጋበኛ እማማ እንዴት ናቸው ብለህ

አትጠይቅም ?" በማለት ተሳስቀው ከተቃቀፉ በኋላ ብሩክ ለወትሮው ያለመደው የእማማ ልብስ ማጠብ አስገርሞት

"እንዴ እማማ ሰራተኛችሁስ ? እሷ አታጥበውም ?" በማለት የሚሰጡ ልብሶች ተቀብሎ ማስጣት ጀመረ

"ልጄ ሰራተኛዋማ ቤተሰቤን ልጠይቅ ብላ ከሄደች ይኸው ድፍን አንድ ሳምንት ሊሞላ ነው "

"መቼ እንደምትመለስ አልነገረቻችሁም ?"

"እሷማ ሶስት ቀን ብቻ ነው ምቆየው ብላኝ ነበር ግን የለችም " በማለት እየጨመቁት የነበረውን ልብስ አቀበሉት

" ደላላ ለማናገር አልሞከሩም ?"

"ወይ ደላላ ምኑ ያስኬደኛል ብለህ ልጄ ይኸው ሳምንቱን ሙሉ ስሰራ ብርዱ ተነስቶብኝ እግሬ ይጠዘጥዘኛል ፤ ደሞ ምን እግር ጣለህ በሰላም ነው ? አገር ቤትስ ሰላም ናቸው ?" በማለት የንግግራቸው አቅጣጫ ለማስቀየር ሞከሩ

"አዎን እማማ በሰላም ነው ያው እኔ ወደ አዲስ አበባ ልሄድ ስለሆነ መጥቼ እንድጠይቃቸው ቦታ እንዳይርቀኝና እህቶቼ ትምህርት ለማስጀመር እዚህ እንዲመጡ አማክሬያቸው ስለተስማሙ የሚከራይ ቤት ፍለጋና እግረ መንገዴ እርስዎን ለማየት ነው "

" እንደስምህ ብሩክ ልጅ ነህ ደሞ ከዚህ ቤት ሌላ የምትመርጥ አይመስለኝም " ልብስ ሲያጥቡ ከነበሩበት ቀና ብለው ተመለከቱት

"እማማ ብዙ ናቸው እኮ እርስዎን ከማስቸግር ሌላ ሰፋ ያለ ቤት እፈልጋለሁ "ሲላቸው ከተቀመጡበት በእጃቸው ድጋፍ በመነሳት ቆጣ

እያሉ

"ምነው ልጄ ያንተው ቤት እንደሆነ ሰፊ ነው ደግሞስ እኔ ብቻዬን አይደለሁ ስራም ያግዙኛል "እያሉ እጃቸውን እየዘረጉና ወደ ብሩክ ኪራይ ቤት እየጠቆሙ መለሱለት

ብሩክም በቆመበት ትንሽ ከአሰበ በኋላ "እሺ በዚህ ሁለት ቀን ውስጥ ሁሉም ነገር ጨርሰን እንመጣለን የሰራተኛው ጉዳይም ደላላ እንዳያናግሩ አክስቴን አናግራትና ታግዛችኋለች "

"እግዚአብሔር እሺ ይበልህ ልጄ ፤ ተባረክ እኔ ምልህ ሄኖንዬ ትደውልልሀለች ? "

"አይ እማ ገጠር እኮ ኔትወርክ ያስቸግራል እንኳን የባህር ማዶ ሰው ጎረቤትንም በስርአቱ ማናገር አይቻልም ፤ ውይ ተረስቶኝ ቅድም ስመጣ እኮ ስልኬ ወድቆ እንደዚህ ሆነ የሚሰራ ሰው አገኝ ይሆን ?"

"ተሰበረ ? ጦስህ ይውሰድ የሚሰሩ አሉ ልጆች አሉ ለነሱ ታሳያቸዋለህ "

"እሺ እማ ፤ ሄኖን ሰሞኑን ደውላለች እንዴ ?"

"አዎን ከሁለት ቀን በፊት አውርተናል ደህና ናት "

"እና ያ ነገር ነገሯት እንዴ ?" በማለት እየተሸኮረመመ አንገቱን ሰበር አደረገ

"ምን አስቸኮለህ ልጄ ቀስ ብዬ አረጋግቼ እነግራታለው "በማለት ስራቸውን ስለጨረሱ ወደ ውስጥ በመግባት ምሳ እንዲበሉ ብታግባባውም ተመልሶ ሄዶ እህቶቹንና አክስቱን ለማምጣት ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ተናግሮ ተሰነባብተው ተለያዩ።

****

ብሩክ እንደፈራው ብዙ እቃዎችን አልያዙም ፤ ብዛቱ ካሰበው በታች ስለነበር ለመጓጓዣ ብዙ መክፈል አልተጠበቀበትም ፤ በውስጡ የሚጠቁመው አድራሻ ምን እንደሆነ የማያውቀው የአባቱ ስጦታ የሆነው ወረቀትም በአስተማማኝ መልኩ ይዟል ስለሆነም አጎታቸውን ተሰናብተው በየጊዜው እየመጡ እንደሚጠይቁት ተነጋግረው ለመገናኛነት በሚል ለአክስቱ የተሰጠው ስልክ ለአጎትየው ተሰጥቶ ተሰነባብተው ወደ ከተማ ጉዞ ጀመሩ።

በጉዞአቸው ወቅት የመንደሩ አለቃ አቶ መኮንን እየሳቁ ይመለከቷቸው ስለነበር ብሩክ ተናድዶ በነገር ለመንካት በማሰብ "አቶ መኮንን ወደ ከተማ ለመኖር እየሄድን ነው ደህና ይቆዩ አቶ መኮንን " በማለት ማንም የማይደፍረው ሙሉ ስማቸውን ደጋግሞ ጠርቶ ሲሰናበታቸው የብሩክ ንዴት ወደ መንደሩ አለቃ ተሸጋግሮ "ዞራ ይቀንጥስህ ! እርጉም ! " እያሉ ተራግመው ሲገቡ ብሩክ እና ትናንሽ እህቶቹ እየሳቁ አክስታቸው ግን እርግማኑ እውነት ሆኖ በብሩክ እንዳይደርስ እየሰጉ ጉዞውን ቀጠሉ።

****

"ሀሎ የኔ ልጅ "

"ሄይ ማም ሰላም ነሽ ?"

"ምን እሆናለው ብለሽ ይልቅ አንቺ እንዴት ነሽ ? ትምህርቱ ማለቂያው

አልደረሰም ? ናፈቅሽኝ እኮ "

" ya አንድ ሴሚስተር ብቻ ነው ከዛ ፈተናዬን ወስጄ ወደናፈቀችኝና ወደናፈኳት እናቴ እመጣለው ማለት ነው "

"እሺ የኔ ልጅ ፤ እኔ ምልሽ ሄኖንዬ ከብሩክ ትደዋወላላችሁ ?"

"ማም please ቅር እንዳይልሽ እኔ እሱን ባናገርኩ ቁጥር የሀይስኩል ብሩክ እየመሰለኝ depressed እየሆንኩ ነው so አልደውልለትም ደውዬ ድምፁን ስሰማ እንባ ነው ሚቀድመኝ እሱንም እንዳላስጨንቀው ባልደውል ይሻላል "እያለች ተስፋ በቆረጠ አነጋገር መለሰችላት

" ይኸውልሽ ልጄ አደራሽን ምንም እንዳትይ ብቻ ብሩክን የምርቃቱ ጊዜ ቀርጬው ነበር ግን እስክትመጪ ብዙ ይቆያል መሰለኝ ....." እያሉ ሲያወሩ ሄኖን ንግግራቸው ላይ ጣልቃ እየገባች

" ማም ኢሞ የለሽም ?"

"ምንድነው እሱ ልጄ ?" ግራ ተጋብተው ጠየቁ

"እሺ ዋትስ ኣፕ ?"

"ልጄ ስለምንድነው ምታወሪው ?"

"ማም come on በእነዚህ መላክ ይቻላል እኮ ፤ ቆይ እሺ ቤት ብሩክ አለ ?"

" ብሩክማ ቤተሰቦቹን ወደ ከተማ ሊያመጣ ገጠር ሄዷል ዛሬ ወይም ነገ ይመጣል "

"እሺ ማም ቤት ላሉት ተከራዮች ለአንዳቸው ኢሞ ዋይም ዋትስ አፕ ከፍታችሁ ምስሉን ላኩልኝ በያቸው ምናልባት እነሱ ያውቁት ይሆናል "

በማለት ስትናገር ምስሉን ለማየት እንደጓጓች ያስታውቅ ነበር

"እሺ ልጄ አሁን እጠይቃቸዋለው ደህና ሁኝ ተባረኪ ልጄ"

" by Mom i love you እወድሻለው"

ወይዘሮ የትናየት እንኳን ይሄ ቀላል ነገር አይደለም አየር ላይ ቤት ሰሩልኝ ቢሉ ራሱ ለመስራት የሚሯሯጡት ተከራዮቹ ተንቀሳቃሽ ምስሉን የላኩት በቅፅበት ነበር።

ትንሽ ቆይቶ የወይዘሮ የትናየት ስልክ ጠራ ልጃቸው ሄኖን ነበረች

"ሃሎ የኔ ልጅ ልከነዋል ብለውኛል አየሽው ?" በማለት ጮክ ብለው ሲጠይቋት

"አዎ " በማለት እያለቀሰች መለሰችላት ወይዘሮ የትናየት የወለደ አንጀት ሆኖባቸው ሆዳቸው እየባባ

"ምነው ልጄ እሱ አይደለም ?" በማለት ፍርሀታቸውን ደብቀው ጠየቋት

ሄኖን ከትንሽ ፀጥታ በኋላ እያለቀሰች "እራሱ ነው ብሩክ እራሱ ነው ማም " በማለት ድንጋን ከፍ አድርጋ አለቀሰች

"እሰይ የኔ አምላክ ፀሎቴን ሰማህ ! ልጄ ታድያ ለቅሶው ምንድነው መደሰት ነው እንጂ "

" ማም i have no words to say ደስታው ነው የሚያስለቅሰኝ ፤ ግን እሱስ ማን እንደሆንኩ አውቋል ?"

"አዎን ልጄ በደንብ አውቋል እኔ እስከምነግራት ድረስ ዝም በል ማን እንደሆንክ እንዳትነግራት ብዬው እኮ ነው እንጂ እሱ እንዴት እንደተደሰተ

ልነግርሽ አል ችልም "

" ማም thank you very much እውነት ደስታው ከአቅሜ በላይ ሆኖብኛል "

" በይ ልጄ እንዳወቅሽው እነግረዋለው ተደዋወሉ እሺ ልጄ "

" እሺ ማም እንደዋወላለን "

" በይ ልጄ ደህና ሁኝ ራስሽን ጠብቂ "

"እሺ ማም bye"

ወይዘሮ የትናየት በብሩክና በልጃቸው መሀል ስለተፈጠረው አስገራሚ አጋጣሚ ቀና ብለው እያዩ ፈጣሪያቸውን ካመሰገኑ ከትንሽ ቆይታ በኋላ የግቢያቸው በር ሲከፈት ሰሙ

"እማማ ... እማማ መጥተናል " በማለት ብሩክ የግቢውን በር በመክፈት እህቶቹንና አክስቱን አስገባ

"ማነው ? ..... ብሩኬ አንተ ነህ " በማለት ከጓዳ ሆነው ጠየቁ

"አዎን እማማ እህቶቼና አክስቶቼ ሊያዩሽ ጓጉተዋል " በማለት ወይዘሮ የትናየትን ከቤቱ ደረጃ ትይዩ ቆሞ ጠበቃቸው

ወይዘሮ የትናየት ከሳሎናቸው ወጥተው በረንዳ ላይ በመሆን " የማናቸው ቆንጆ ውይይይይይ ኑ ሳሙኝ " በማለት ሁለቱ የብሩክ መንትያ ህፃናትን ለማቀፍ እጃቸውን ሲዘረጉ ህፃናቱ በመሮጥ ደረጃውን ወጥተው ስለ መልካምነታቸው ብሩክ ሲያወራ የማይጠግባቸውን ወይዘሮ የትናየትን አቀፉ።

በመቀጠልም ሁለቱንም ህፃናት በቀኝና በግራ እጃቸው ይዘው ደረጃውን በቀስታ ከወረዱ በኋላ የብሩክ አክስት ጋር በመሄድ " የትናየት እባላለው እነ ብሩክ እማማ ብለው ይጠሩኛል " ብለው ፈገግ በማለት እጃቸውን ሲዘረጉ የብሩክ አክስት በተራቸው "ሰንቅነሽ" በማለት ተጨባብጠው ተቃቀፉ ። ወይዘሮ የትናየትም ወደ ብሩክ ዞረው "እንኳን ደህና መጣችሁ " በማለት ፈገግ በማለት ሰታየው የአክብሮት ምስጋናውን ከወገቡ ጎንበስ ብሎ ሰጣቸውና " ኑ ልጆች ወደ ውስጥ እንግባ " በማለት እህቶቹን እየጠራ ወደ ቤቱ ሲያመራ ወይዘሮ የትናየት ሁለቱን ልጆች እየያዙ ቆጣ በማለት " ሰማ ገብተህ ቤቱ ምታስተካክል ከሆነ አስተካክል እነሱ ዛሬ ከኔጋር ነው ሚጫወቱት " በማለት በየተራ አቅፈው ሲስሟቸው ብሩክ ፈገግ እያለ " አክስቴ እማማ አይቻሉም ነይ እኔና አንቺ እንግባ " በማለት በሩን ከፍቶ እቃዎቹን ማስገባት ጀመረ።

ወይዘሮ የትናየት እነ ብሩክ እቃ ማስገባት ሲጀምሩ ውብ ልጆቹን እያዩና ረዥም ፀጉራቸውን ወደ ኋላ እያሻሹ በየተራ ጥያቄ መጠየቅ ጀምረው ነበር

"ሚጣ ስምሽ ማነው ?"

"ህሊና "

" ጎበዝ ልጅ ፤ አንቺስ ሚጣ ?"

"ማርያማዊት"

" ሁለታችሁም ጎበዝ ልጆች ናችሁ ቶም ኤንድ ጄሪ ታያላችሁ ?"

ሁለቱም መንትዮች እርስ በእርሳቸው ተፋጠጡ

"እሺ የአሻንጉሊት ፊልም ትወዳላችሁ ?"

ወይዘሮ የትናየት ስለምን እንደሚያወሩ ግራ የገባቸው መንትዮቹ ልጆች "እይ" በማለት አንገታቸውን ወደጎን አነቃንቀው ሲመልሱ ወይዘሮ የትናየት ፈገግ እያሉ "ኑ እሺ ውስጥ እንግባና ቲቪ እንይ " በማለት ወደ ውስጥ ይዘዋቸው ገብተው ቲቪ ከከፈቱላቸው በኋላ ተመልሰው በመውጣት

" ብሩክ አንዴ ና " በማለት በእጃቸው ምልክት እየሰጡ ጠሩት

ብሩክም " ወይ እማማ " እያለ እጁ ላይ የነበረውን አቧራ እያራገፈ መጣ

" ሄኖንዬ ደውላ ነበር ብሩክ ኣንተ መሆንህን ስታውቅ እያለቀሰች ነው የደወለችልኝ ፤ ስልክህን ቶሎ አሰራውና ደውልላት ትናፍቅሀለች " በማለት እየተደሰቱ ነገሩት

ብሩክም ተደስቶ ወይዘሮ የትናየትን ለማቀፍ ቢፈልግም እጁ ቆሻሻ ስለነበር እዛው በቆመበት እጁን ጨብጦ እያወናጨፈው ደስታውን ገለፀ።

****

ትናንሾቹ የብሩክ እህቶች እና አክስቱ ቤቱን ተላምደውታል ከወይዘሮ የትናየት ጋርም ጥብቅ ወዳጆች ሆነዋል ፤ የብሩክ አክስትም ወይዘሮ የትናየትን ሳይሰለቹ ስራ እያገዟቸው እንደ አሰሪና ሰራተኛ ሳይሆን እንደ እህትማማቾች መጨዋወት ፣ መሳሳቅና መቀላለድ ጀምረዋል ።

ብሩክ ሁለቱን እህቶቹ ትምህርት ቤት ለማስገባት ወደ መንግስት መዋዕለ ህፃናት በመሄድ ጥያቄ አቀረበ ፤ የትምህርት ወቅቱ ተጋምሶ ስለነበር ሙሉ አመት ለመማር ሳይታደሉ ለግማሽ ሴሚስተር እንዲማሩ ተፈቅዶ ትምህርት ቤት ተመዘገቡ።

የቤተሰቡ ሀላፊነት የተሸከመው ብሩክ አስፈላጊ ነገሮችን ለቤቱ በማሟላትና ለእህቶቹ ዩኒፎርምና የመማርያ ደብተር በመግዛት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የራሱን የትምህርት ጉዳይ መጨረስና አስፈላጊ መረጃዎች የሚለዋወጥበት ስልክ ማሰራት እንዳለበት ስላወቀ ያለ ምንም እረፍት እዚህ እዚያ በማለት ጊዜው እንዳይሄድበት እየተሯሯጠ ነው።

አድራሻው

የቤተሰቡን አስፈላጊዎች ሰራ በመስራት በአቶ ግርማቸው ትዕዛዝ ትምህርት ከሚጀመርበት ቀን አንድ ሳምንት ቀደም በማለት ቤተሰቡንና ወይዘሮ የትናየትን ተሰናብቶና ከትምህርት ቤቱ የተሰጠው ስጦታ ግማሹን ለአክስቱ በመስጠት በማለዳ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ አደረገ።

ጊዜው ሀሩር ከሮበት በነበረበት ሰአት ብሩክ አዲስ አበባን ረገጠ ላይ ታች የሚሉ የተለያዩ ቀለምና መጠን ያላቸው መኪናዎች ፣ ያለ እረፍት የሚርመሰመሱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ፣ በመናኸርያው ጥግ ላይ ገንዘብ የሚለምኑ እናቶች ፣ መንገደኛን የሚያዋክቡ ሱቅ በደረቴዎች ፣ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎችና የቦታው ግርግር ብሩክ ቀድሞ ከነበረበት ከተማ በምንም አይስተካከሉም ነበር።

ግርግሩ ሀሳቡን ቢበታትነውም አባቱ አደራ በማለት የሰጡን ወረቀት ከኪሱ በማውጣት ወደሚጠቁመው ሰፈር ለመሄድ የሰፈሩን ስም የሚጠራ ታክሲ ስላገኘ ጉዞ ጀመረ።

የታክሲው ረዳት የተባለው ቦታ እንደደረሱ ስለነገረው ከታክሲው

በመውረድ በአባቱ ወረቀት የተጠቆመው ትልቅ ህንፃን ተከትሎ በተሰራው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በመሄድ የተጠቆመው አድራሻ ጋር ቆመ ፤ የአባቱ የአድራሻ ወረቀት የሚያሳየው የቤት ቁጥር 301 ሲሆን ብሩክ በወረቀቱ አድራሻ የደረሰበት ግን 92 ስለነበር አቅጣጫ መሳቱ ገብቶት ወደ ትልቁ ህንፃ በመሄድ ድጋሚ የቤት ቁጥር 301 አሰሳ ጀመረ።

ብሩክ ከሁለት ጊዜ ሙከራ በኋላ ግዙፍ ቪላ ቤት እና በግንብ የታጠረ ከግንቡም ላይ ሸቦ የተጠቀለለበት ባለ ግዙፍ ብረት በር ላይ የቤት ቁጥሩን ስላገኘው ወደ ቤቱ በመሄድ በሩን ለመቆርቆር ሲጠጋ በቅርቡ ተሰብሮበት የነበረውና ኋላ ላይ ያሰራው ስልኩ ጠራ ፤ ሄኖን ነበረች ፤ በደስታ ስልኩን ተመልክቶ ካነሳው በኋላ ድምጿን ለመስማት ጓጉቶ

" ሀሎ ሄኖን " በማለት ምላሽ ሲጠብቅ የእጅ አመል የተጠናወተው አንድ ጩሉሌ ሌባ ስልኩን መንትፎት ተፈተለከ ፤ ብሩክም በመደናገጥ ባለበት ፈዝዞ ቀርቶ ሌባውን ከአይኑ እስኪርቅ ድረስ ሸኘው።

ምን እንደተፈጠረ ግራ የገባት ሄኖንም

"ሄሎ ብሩኬ ሰላም ነው ?" መልስ ግን አልነበረም

" ሄሎ what's wrong? ብሩክ ፣ ሄሎ ፣ ሄሎ " በማለት ብትጣራም መልስ ግን አላገኘችም

ብሩክ ከስልኩ ጋር የተወሰዱት የደጓ ወይዘሮ የትናየት ፣ የሚወዳት ሄኖን ፣ የአጎቱ ስልክ ቁጥሮች በቃሉ ለማሰብ እየሞከረ ስለአቃተው ራሱን እያረጋጋ ወደ ቤቱ ቀርቦ በሩን ቆረቆረ።

ከሁለት ቁርቆራ በኋላ በሩ ተከፈተ ፤ ጠና ያሉ ፣ ቀጠን ብለው ረዘም ያሉ ፣ ፀጉራቸው በሙሉ ማራኪ ጥጥ የደፉ ይመስል በሸበት የተከበበና ፊታቸው የተሸበሸቡ አዛውንት ከፊት ለፊቱ በመቆምና በሩን ገርበብ አድርገው

በመክፈት

"አቤት ልጄ "በማለት በደከመ ንግግር አናገሩት

"ሰላም ዋሉ አባባ ?"

"ሰላም ውያለው ፤ ምን ልርዳህ ?"

"ካልተሳሳትኩ ወደዚህ ቤት መልእክት ተልኬ ነበር "በማለት መለሰ

አዛውንቱም ኮስተር በማለት

"አይ ተሳስተሀል መልእክቱ በድጋሚ እየው እዚህ ቤት አይደለም " በማለት በሩን ለመዝጋት ወደ ውስጥ ሲገቡ ብሩክ በመደናገጥ

"እይደለም አባባ ወደዚህ ነው የተላኩት ይኸው የቤት ቁጥሩ ልክ ነው " በማለት ከአባቱ የተሰጠውን ወረቀት ወደ አዛውንቱ በማዞር አሳያቸው

አዛውንቱም ወረቀቱን ገረፍ አድርገው አይተው ብሩክን በጥርጣሬ አይን እያዩ በሩን ዘጉት።

ብሩክ ግራ በመጋባት አዛውንቱን ለማሳመን ጮክ በማለት እያወራ "አባባ አቶ ፈይሴ ናቸው የላኩኝ ወረቀቱ ከሶስት አመት በላይ ይሆናል ከሰጡኝ ግን ስላልተመቸኝና ሁኔታው ስላልሰመረልኝ ነው ያልመጣሁት "

በማለት መልስ ቢጠብቅም ምላሽ ስላጣ ፊቱን ወደ መንገዱ በማዞር ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያስብ ከበስተ ኋላው "አቶ ፈይሴ ?" የሚል ድምፅ ሰለሰማ ዞር አለ

አዛውንቱ በተለወጠ መልክና አነጋገር በሩን በመክፈት "አቶ ፈይሴ የተባረኩ ሰው "በማለት ብሩክን ትክ ብለው ሲመለከቱ ብሩክ ፈጠን ብሎ

"አዎን አባባ አቶ ፈይሴ አባቴ ነው ከሶስት አመት በፊት ነው ይህ ወረቀት

ሰጥቶኝ እንድሄድ የነገረኝ " በማለት መለሰ

አዛውንቱም ወደ ብሩክ በመቅረብ "አባትህ መልካም ሰው ነው ፤ እኔንም በእድሜዬ ማብቂያ ተደላድዬ እንድኖር ያደረገኝ እሱ ነው ፤ ያኔ ድሮ እሱ እዚህ ለቡና ንግድ ሲመላለስ ቡናውን የሚያስቀምጠው የአባቴ መጋዘን ውስጥ ነበር እኔ ግን የሱን ቡና ብቻ እየመረጥኩኝ በማውጣት እየሸጥኩ አስቸግረው ነበር በእድሜም እኩዮች ስለነበርን ለአባቴ ተናግሮ እኔን ከማሳጣት ይልቅ ፈልጎ እያገኘኝ እንዳልሰርቅና ሰራ እንድሰራ ይመክረኝና ገንዘብ ይሰጠኝ ነበር። እኔም ስመከር አልሰማም ብዬ በስርቆቴ ቀጠልኩ ፤ ከዛሬ ነገ ለአባቴ ነግሮ ያቆራርጠኛል ብዬ በምፈራበት ጊዜም እቃው የተሟላ አነስተኛ ሱቅ ተከራይቶ የአመት ክፍያን ከፍሎልኝ ልመልሰው የማል ችለው ውለታ ዋለልኝ ፤ ልጄ አቶ ፈይሴ ጥሩ ሰው ናቸው ካየኋቸውም ብዙ ጊዜ ሆኗል ፤ መልካም ሰው ፤ ሰላም ናቸው ይሆን ?" በማለት ከትዝታቸው እየተመለሱ ጠየቁት

ብሩክም በአዘነ መንፈስ ሆኖ "አባባ ጋሼ ካረፈ ሶስት አመት አልፎታል " በማለት የገዛ አባቱን ሞት አረዳቸው

"ወይ ጉድ!" በማለት አንዴ ጭንቅላታቸውን አንዴ አፋቸውን በመያዝ "ፈይሴ ጀግናው ? ፈይሴ መልካሙ ሰው አረፉ ?" በማለት ድንጋጤያቸውንና ሀዘናቸውን ጥቂት ለማይባሉ ደቂቃዎች ደጅ ላይ እየተመላለሱ ከገለፁ እና ከተረጋጉ በኋላ ብሩክ የመጣበትን ምክንያትና መቆያ ቤት እንደሚፈልግ ሲነግራቸው ከድንገተኛው ሀዘን እየተላቀቁና ደስ እያላቸው በቤቱ ውስጥ እሳቸው ብቻ እንደሚኖሩና ብዙ ክፍት ክፍሎች እንዳሉ ነግረውት ለፈለገው ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚችል ነግረውት ቤቱን ለማሳየት ወደ ውስጥ አስገቡት።

ግቢው ሰፊ ነው ፤ ዋናው ቤት በሰለጠነ ግንበኛ የተሰራ ነው የሚመስለው

የበሮቹ ስፋትና ርዝመት ፣ የመስኮቶቹ ውበት እንዲሁም በቄንጠኛ እምነበረድ የተሰራው በረንዳ አዛውንቱ ደህና የሚባል ኑሮ እንደሚኖሩ ያሳብቃሉ።

ከበሩ በስተ ግራ በኩል በሚያምር ቤት የተቀመጠ ቡናማ መልክ ያለው ድንክዬ ውሻ አለ ፤ ዋናው ቤት በደብዛዛ ብርቱካናማ ቀለም የተቀባ ሲሆን ከፊት ለፊቱ በአነስተኛ መደብ የተሰራ የአትክልት ስፍራ ይገኛል ከዋናው ቤት ጀርባ እንደተባለውም ብዛት ያላቸው ቤቶች ነበሩ። ከጀርባ ከሚገኙ ቤቶች መካከል ሰፋ ወደሚለውና ለብቻው ነጠል ብሎ ወደተሰራው በመውሰድ

"ልጄ ይህ ቤት ሳይሻልህ አይቀርም ሙሉ እቃ አለው ፤ ከኔ ጋር ባዳብልህ ነፃነትህን የምወስደው ስለመሰለኝ ነው ብቻህን የምተውህ ደግሞ ተማሪም አደለህ ስታነብ ልታመሽ ትችላለህ" በማለት አባቱን እየመረቁና በሞቱ እያዘኑ የግቢውንና የቤቱን ቁልፍ ሰጡት።

****

"ሄሎ ማም"

"ወዬ የኔ ልጅ ደህና ነሽልኝ ?"

"ደህና ነኝ ፤ ብሩክ ቤት አለ እንዴ ?"በማለት ሄኖን ተቻኩላ ጠየቀቻት

"ኧረ የለም ባለፈው ያልኩሽን ትምህርት ሊማር ዛሬ እኮ ነው አዲስ አበባ የሄደው ፤ ስልኩን አሰርቶታል አትደውይለትም ?"

" ማም አሁን እኮ ነው ደውዬለት ሀሎ ካለኝ በኋላ ዝም አለኝ ደጋግሜ ስሞክርም አልሰራልኝም"

"ውይ ውይ ውይ ልጄ ምን ሆኖ ይሆን ?"

"I don't know ማም ጨንቆኝ እኮ ነው እስቲ አንቺም ሞክሪለት እኔም እሞክርለታለው "

"እሺ የኔ ልጅ አይዞሽ ምንም አይሆንም ወንድ አይደል ይልቅ በርትተሽ ተማሪ" በማለት ወይዘሮ የትናየት ልጃቸው እንዳትጨነቅ በማሰብ መልሰውላት ከተሰነባበቱ በኋላ በብሩክ ስልክ መቋረጥ ግራ እየተጋቡ ወደ ብሩክ ስልክ ደጋግመው ቢሞክሩም መልስ ስላላገኙ በጭንቀት ተዋጡ።

****

ስልኩ ከተወሰደበት አምስት ቀን ቢሆነውም ሌላ ስልክ ለመግዛትና ሲም ካርድ ለማውጣት አላሰበም ምክንያቱም ከአዛውንቱ ጋር ስለ አባቱ የቆየ ታሪክ እየተጨዋወቱና በዲግሪ መርሀ ግብር የደረሰው የአስተዳደር ትምህርት ለመመዝገብና አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ እያሟላ ነበር ።

ዛሬ ግን አዛውንቱ ስልኩ መነጠቁ ነግሯቸው ስለነበር በአዛውንቱ ምክርና ትዕዛዝ ሌላ ስልክ ለመግዛት ወደ ሱቅ በመሄድ ኪሱን የማትጎዳውን ስልክ በመግዛትና ሲምካርድ በማውጣት ወደ ወይዘሮ የትናየት ለመደወል ቢሞክርም በቃሉ ይዞት ስላልነበር አልቻለም ።

የትምህርት ወቅት ደርሶ ስለነበርም ተመልሶ ወደ ወይዘሮ የትናየት መሄድን አልመረጠም በመሆኑም የሚሆነውን በትዕግስት መጠበቅ እንዳለበትና

ተረጋግቶ ትምህርቱን መቀጠል እንዳለበት ራሱን አሳምኖ ዝምታን መረጠ።

****

የብሩክ አጎት በገጠር ብቻውን ማሳለፍ ተስኖታል ፤ ልብሶቹ እድፍ ወሯቸዋል ፤ ማሳውም ቢሆን በአረም እየተወረረ ነው ፤ የቤቱ ገፅታም ዝርክርክነቱ ሳያንስ ሸረሪት አድርቶበት አይጥ ይርመሰመስበታል ፤ የሚታገዱ ላሞቹም ጠዋት ከቤት አውጥቶ ሰፊው ማሳ ላይ በረጅም ገመድ ከአሰራቸው በኋላ ወደ ቤት የሚመልሳቸው አመሻሽ ላይ ነው ፤ የሚበላው ምግብ ተሯሩጦ ሰርቶ ከማግኘት ፈንታ በየአረቄ እና ጠላ ቤቱ እየዞረ ብሩክ የሰጠውን ጥቂት ገንዘብ አንድ ሁለት እያለ በመጠጥ ማጥፋትን መርጧል ዛሬ ግን ገንዘቡ ስላለቀና የመንደሩ አበዳሪዎች ፊታቸውን ስላዞሩበት ከቀሩት ሶስት ላሞች አነስተኛዋን ላም ለመሸጥ በመወሰኑ ከታሰረችበት በመፍታት ወደ ገበያ እየነዳት ሄደ።

****

ወይዘሮ የትናየት በብሩክ መጥፋት ተጨንቀዋል ለብሩክ አክስትና ሁለቱ መንትዮች እየደወለ መሆኑንና ሰላም መሆኑን ከአንዴም ሁለቴ ሲጠይቋት ብትነግራቸውም እሳቸው ግን በጭንቀት ከመብሰልሰል አልታቀቡም ነበር ። ከልጃቸው ሄኖን ጋርም ስለ ብሩክ መጥፋት በተደዋወሉ ቁጥር ያነሱታል እናትና ልጅ እጅግ ስለተጨነቁ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስላላወቁ ዝምታን መርጠው በራሱ ጊዜ እስኪደውል መጠበቅ ብቸኛ አማራጭ ስላደረጉት ጭንቀቱንና ፍለጋውን ጋብ አደረጉት።

****

የትምህርት ቀን ስለደረሰ በአዲስ ተስፋ እና ዝግጅት ነበረ በማለዳ የተነሳው ባለፉት ቀናት መንገዶች ስፍር ቁጥር በሌላቸው መኪናዎች ተጨናንቀው ለወጣበት ጉዳይ ሲያዘገዩት ስላስተዋለ በጊዜ ለመድረስ አንድ ሰዓት ቀደም በማለት የሄኖን ስጦታ ላፕቶፕ እና ማስታወሻ ደብተሩን ይዞ ጉዞ ጀመረ ።

እንደፈራውም መንገዶች ስፍር ቁጥር በሌላቸው መኪኖች እና ጎዳናዎች በረጃጅም ሰልፎች ተጨናንቀው ቢጠብቁትም ትዕግስትን በመላበስ ረጅሙን ሰልፍ ተቀላቅሎ ወደ ዩንቨርስቲው ግቢ የሚወስደው መኪናን መጠበቅ ያዘ።

ግፊያው ፣ የማለዳ ፀሀዩና የሰዎቹ ግርግር ናላውን ቢያዞረውም ለግማሽ ሰዓት የፈጀውን ጉዞ አጠናቆ ወደ ዩንቨርስቲው ደረሰ።

ብሩክ ወደ ቦታው የደረሰው ከትምህርት ጅማሮ ሰላሳ ደቂቃ አስቀድሞ ስለነበር ባለፈው ለምዝገባና ለአንዳንድ መጠይቆች በመጣ ሰዓት ያላያቸው ቦታዎችን ተዘዋውሮ መመልከትን መረጠ።

ጥንታዊነት የሚታይባቸው ህንፃዎች ፣ መመገቢያ አዳራሾች ፣ ላይብራሪ ፣ የተለያዩ ሰዎች ስም እና ምስል ያለባቸው ግድግዳዎች ፣ አልፎ አልፎ የሚታዩ ከዘንባባ ዛፍ ጥላ ስር የተሰሩ መቀመጫዎች እንዲሁም ብዛት ያላቸው በመደበኛው መርሀ ግብር የሚማሩ የግቢው ተማሪዎችን እየተዘዋወረ ተመልክቶ የትምህርት ሰዓት ስለደረሰ ወደ ትምህርት አዳራሹ አቀና።

ብሩክ ወደ ክፍሉ እንደገባ ያስተዋለው አንድ ክፍት ወንበር ጋር በመሄድ ሊቀመጥ ሲል ከበስተጀርባው ቀጭን የሴት ድምፅ "ይቅርታ ሰው አለው " በማለት ትከሻውን ነካ ነካ ስታደርግ ብሩክ በ'ችግር የለውም' አተያይ እያያት ሌላ ቦታ ሲያማትር "ቦታውን ከወደድከው ግን እዚሁ መቀመጥ ትችላለህ "በማለት ስትመልስለት ለማናገር ፈልጋ እንጂ እውነትም ቦታው የሌላ እንዳልሆነ ስለገባው "የሰው ቦታ ላይ አይደለሁ ?"በማለት መለሰላት

"ነህ ግን የቦታው ባለቤት ትቶት ስለሄደ መቀመጥ ትችላለህ "

"ሳይፈቀድልኝ ?"በማለት ፈገግ አለ

"እኔ ፈቅጄልሀለው ፤ ትዕግስት እባላለው ከዚሁ "በማለት ፈገግታዋን ለግሳው እጇን ዘረጋችለት

ብሩክም ለመተዋወቅ ፍቃድ ሳትጠይቅ ስሟን መናገሯንና እጇ መዘርጋቷ አስገርሞት "ብሩክ ... ብሩክ እባላለው ከገጠር ነው የመጣሁት "በማለት መለሰ

"ስትታይ ግን የገጠር ልጅ አትመስልም "

"የገጠር ልጅ ምን ይመስላል ?"

"አለ አደል በቃ ከከተማው ሰው ወጣ ያለ ነገር ይታይበታል አንተ ግን የዚሁ ከተማ ልጅ ነው ምትመስለው ፤ በነገራችን ላይ መደበኛ ተማሪ ነህ ?"

"አይ እድል ደርሶኝ ነው ገና ዛሬ ነው ምመጣው "

ትዕግስት ፈገግ እያለች "ኦ እንደኛው ነሃ !"

"ይሆናል "

"ስለተዋወኩህ ደስ ብሎኛል "

"እኔም ደስ ብሎኛል " በማለት ፊቱን ወደ ነጩ ሰሌዳ እያዞረ ሲቀመጥ ትዕግስት ፊቷ እየተለወጠ " ማውራት አልፈለክም ?" በማለት አንገቷን ወደፊት አሰግስጋ ስትጠይቀው በአይን አውጣነቷ እየተገረመ "አይ እንደዛ ሳይሆን የምሰራው ስራ ስላለ ነው " በማለት ለአፍታ ዞሮ ከመለሰላት በኋላ ማስታወሻ ደብተሩን ገለጥ አድርጎ ቀን መፃፍ ሲጀምር ትዕግስት አሁንም አንገቷን ወደ ብሩክ እየለጠጠች

" እስቲ ስለ ገጠራችሁ ንገረኝ ስንት ላሞች አሉህ ? ፍየሎች በጎች ምናምን የሉህም ?" በማለት እየተቁነጠነጠች ስትጠይቀው በንዴት ንግግር ግን ድምፁን ዝቅ አድርጎ

"ይቅርታ ስምሽ ማን ነበር ?"

"ትዕግስት"

"እንደስምሽ ትዕግስት ይኑርሽ" በማለት ከነበረበት ተነስቶ ሌላ ቦታ ተቀመጠ

ከትንሽ ቆይታ በኋላ የትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ትምህርት ዘርፍ ተቆጣጣሪ ወደ ክፍሉ በመግባት የዶርም ቁጥርና የዩንቨርስቲው መታወቂያ ካደሉ በኋላ ሁሉም በመማርያው አዳራሽ ያሉት ሁሉም በከፍተኛ ውጤት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ መሆናቸውንና ጠንክሮ ሰርቶ በሁለት አመት የሚጠናቀቀውን ትምህርት በከፍተኛ ውጤት ለሚያጠናቅቁ በማስተርስ መርሃ ግብር ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖ እንደሚማሩ ተናግረው እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ እና ነገ ትምህርት በጊዜው እንደሚጀመር ተናግረው ወጡ።

ሁሉም በስርዓት ራሱን የመጣበትን ፤ የማህበረሰቡ ልማድ እና የሚማሩበትን አላማ በየተራ እየተነሳ ተናገረ ። ብሩክም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል መጥተው መሰብሰባቸውንና የሌሎች ማህበረሰቦች ልማድ መስማቱ ቢያስደስተውም የራሱን ማህበረሰብ ልማድ ምን ብሎ እንደሚያስረዳ ተጨነቀ ።

ሁሉም በየተራ ተነስቶ ራሱን ካስተዋወቀ በኋላ የብሩክ ተራ ስለደረሰ ንግግር ጀመረ

"ስሜ ብሩክ ፈይሴ ይባላል ..." በማለት የፈራውና ለመናገር ያልፈለገው የነበረው ግን ስለ ማህበረሰባቸው አስተሳሰብ እና ስላላቸው አንዳንድ አመለካከቶች እና ስለ ዞራ ትንሽ የማይባል ጊዜ ወስዶ የሚማርበትን አላማ ሲናገር በክፍሉ የተገኙት ተማሪዎች በአድናቆት አጨበጨቡ።

ብሩክ ከትውውቁ በኋላ ወደ ትምህርት ቤቱ የዘርፍ ተቆጣጣሪ ቢሮ በመሄድ የዶርም ክፍል እንደማያስፈልገውና ከተማ ውስጥ የዘመድ ቤት መኖሩን አሳውቆ ከትምህርት ቤቱ ግቢ ከመውጣቱ በፊት ራሱን ዘና ለማድረግ የተማሪዎች ካፌ በመሄድ ሻይ አዝዞ ፊቱን የግቢውን ገፅታ ወደሚያሳየው መስታወት አዙሮ ተቀመጠ ።

አላማው ልክ ነው ፤ ማህበረሰቡን መለወጥ የተሻለ ኑሮ ማኖር ፤ ሆስፒታሎች ተገንብተው አቅም የሌላቸውን እናቶችንና ህፃናትን በነፃ ማገልገል ፤ ባለፉት ዘመናት በተንኮለኞችና ስግብግቦች ጥንስስ ሴራ የተበዘበዘው የመንደሩ ሰውን መካስ ሌሎችም አላማዎች ከፊት ለፊቱ አሉት ።

በቀጣዮቹ ቀናትም ለሳምንት የተለያዩት ቤተሰቦቹን ማግኛ መንገድ ፍለጋ ለመጀመር አስቧባል።

"ሀይ ብሩክ " በማለት ችኩል የሆነችው ትዕግስት ወደ ብሩክ በመምጣት ሳታስፈቅደው ከፊት ለፊቱ ወንበር በመሳብ ተቀመጠች

ብሩክም በትዕግስት ባህሪ ግራ እየተጋባና እየተናደደ " ሰላም ትዕግስት ለመሄድ ስል ነው የመጣሽው ይቅርታ " በማለት ከተቀመጠበት የሻዩን ሂሳብ ከፍሎ ተነሳ።

ወደ ግቢው መውጫ በር እየሄደ ሳለ ከበሩ በስተ ግራ በኩል ከጫማ ጠራጊዎቹ መካከል " ብሩክ ... ብሩክ " በማለት ወደ እሱ እያመራ ተጣራ

ብሩክም ወደተጠራበት አቅጣጫ በመዞር ማን እንደጠራው ለማረጋገጥ ቆም ሲል ያየውን ነገር ማመን አቃተው " ጥላሁን ?" በማለት ጮክ አለ

"ብሩክ አንተ ራስህ ነህ ?" በማለት ጥላሁን እየተጠጋው ጠየቀው

ብሩክም የተጎሳቆለው የጥላሁን ፊትን ትኩር ብሎ ተመልክቶ በደስታ ተቃቀፉ ።

"እዚህ መሆንህን እናትህ ነግራኝ ነበር ግን የማገኝህ አልመሰለኝም " በማለት ብሩክ ካወራ በኋላ በድጋሚ ተቃቅፈው ናፍቆታቸውን ጋብ ለማድረግ ሞከሩ።

ወደ ዩንቨርስቲው የተማሪዎች ካፌ እየሄዱም ጥላሁን ገጠር የተለመደውን ስራ እየሰራ ይሄ እድል መጥቶ ለምዝገባ የቀረው ሁለት ቀን ብቻ ስለነበር ድንገት ከገጠር መውጣቱንና በአጎቱ ድጋፍ በማታ መርሀ ግብር የህግ ትምህርት እየተማረ መሆኑንና የትምህርት ቤት አንዳንድ ወጪዎችን ለመሸፈን ቀን ቀን በሊስትሮነት ግቢው ውስጥ እንደሚሰራ የቤት ኪራይ ወጪ ለመሸፈንም ይህንኑ ስራ እየሰራ መሆኑንና የመጀመሪያው ሴሚስተር ጨርሶ ወደ አገር ቤት እንደሚመለስ እየነገረው ወደ ካፌው ገብተው ያሳለፉትን ሁሉ እየሳቁና እየተቀላለዱ ካሳለፉ በኋላ ብሩክ ወደሚኖርበት

ቤት እንዲመጣ እንደሚያደርግና አክስቱን እና እህቶቹን ለመጠየቅ ሰልክ ቁጥራቸው እንደጠፋበት ሲሄድም ምን እንደተፈጠረ ተናግሮ አዲሱን ሰል እንዲሰጣቸው ነግሮት ሰልክ ተለዋውጠው ተለያዩ።

ብሩክ ከአብሮ አደግ ጓደኛው ጋር ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ስለተገናኙ በጣም ተደስቷል ነገር ግን ብሩክ ባሳለፈው አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ጥላሁን እያሳለፈ ትምህርቱን መማሩ አልተዋጠለትም ነበር ስለሆነም በቀጣይ ጊዜያትም የብሩክ ዋነኛ ጥያቄ የሚሆነው እና ጥላሁንን የሚያስለፋው የገንዘብ ችግር ለማስቀረት በሚያስብበት ወቅት ወደ አዕምሮው የመጡት የአባቱ ጓደኛ የነበረው አዛውንት ግቢ የነበሩት አራት ባዶ ቤቶች ስለነበሩ እነሱን በማከራየት አዛውንቱ ድጋፍ እንዲያደርጉለት ለመጠየቅ አሰበ።

****

ብሩክ አንዳች ሀሳብ ሊያማክራቸው እንደሚፈልግ ከፊቱ ገፅታ የተረዱት አዛውንቱ "ምነው ልጄ ፊትህ ልክ አይደለም ምን ሆነሀል ?" በማለት ጠየቁት

ብሩክም የአዛውንቱ ውስጥ አዋቂነት እያስገረመው "አባባ አንድ ነገር ላማክርዎት ነበር ?"

"ምነው ልጄ ? ንገረኝ "

"አባባ እነዚህ ቤቶች ቢከራዩ ብዙ ገንዘብ ያስገኙልን ነበር እኮ " በማለት ፈራ ተባ እያለ ተናገረ

ሸማግሌውም "አዬ ልጄ እኔ ምን ጎደለኝ ? ሁሉም ሞልቶልኛል እኮ ደግሞ ተከራይ በኔ እድሜ አሰገብቼ ጨጓራዬን ላቃጥለው ? " በማለት ፈገግ እያሉ በጥያቄ ሲመልሱ

"አደለም አባባ እርሶ እንዳልተቸገሩ አውቃለው ግን ገንዘብ ሰለቸገረኝ እኮ ነው ደግሞ የሚገቡት ሰዎች ጉዳይ ለኔ ተወው እኔ እቆጠጣጠራቸዋለው "

" በሰመ አብ ወልድ ወመንፈሰ ቅዱሰ " በማለት ካማተቡ በኋላ

"ልጄ በል በል አባትህ ያን ሁሉ ውለታ ውሎልኝ እንቢ የምል ይመሰልሀል ? እግዚአብሔርሰ አይታዘበኝም ? ከዛሬ ጀምሮ ቤትህ ነው እኔ ምንም አይነት ገንዘብ አልፈልግም ተጠቀምበት ግን የተከራዮቹን ጉዳይ አደራህን ሰርዓት ያላቸው ይሁኑ " በማለት ድንጋጤያቸውን ፣ ለብሩክ አባት ውለታ ምላሽ የሚሆን ምክንያት በማግኘታቸው እየተደሰቱ እና ሰለሚገቡት ተከራዮች እያሳሰቡ ነገሩት።

ብሩክ የአባቱ ጓደኛ አዛውንትን እያመሰገነ ከዛሬ ጀምሮ ማስታወቂያ እንደሚያወጣ ተከራይ እንደሚፈልግ ለአዛውንቱ በመንገር በድጋሚ ከልቡ እያመሰገነ ተለይቶ ወደ ጥላሁን ሰልክ በመደወል ቤት እንዳገኘለትና ከቻለ ዛሬ መግባት እንደሚችል ከነገረው በኋላ በግቢው በር ላይ የኪራይ ቤት ማስታወቂያ አወጣ።

ከጠበቀው ጊዜ በፊት ነበር ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ወደ ብሩክ በመደወል የ "እንከራይ" ጥያቄ ያቀረቡት ፤ ነገር ግን በዋጋ እና ብሩክ አዛውንቱ ባስጠነቀቁት መንገድ ያስቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ባለመመቻቸቱ ጥቂት ሰዎች ብቻ በዋጋ እና በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ቢስማሙም

ከሚያስፈልገው የሰው ቁጥር በላይ ስለነበር ከሶስት ሰዎች ጋር ብቻ በመስማማት ወደ አዛውንቱ ግቢ ተቀላቀሉ።

ሁሉም ባሰበው መንገድ እየሄደለት በመሆኑ በራስ መተማመኑ ከፍ ብሏል በሚወስናቸው ቁልፍ ውሳኔዎች ውስጥም የአባቱ አደራ ትዝ ስለሚለው ምን እንደሚወስን ለማረጋገጥ ደጋግሞ ውሳኔውን ያጤነዋል በመሆኑም ብሩክ ለውሳኔ አይቸኩልም።

ጥላሁን ወደ ብሩክ መኖርያ ወደሆነው የአዛውንቱ ግቢ ከከተመ ሰንብቷል የቤት ኪራይ ወጪም አያሳስበውም ለዚህም ብሩክን ደጋግሞ ያመሰግነዋል ፤ ያሞካሸዋል ሰሞኑን ግን የትምህር ጊዜው ተጠናቆ እረፍት ስለተሰጣቸው ወደ አገር ቤት በመሄድ እግረ መንገዱንም ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት ጎራ ብሎ ስለ ብሩክ ሊያጫውታቸው አስቧል።

****

ወይዘሮ የትናየት ብሩክን ካገኙ ሁለት ሳምንት ሊደፍኑ ነው በልጁ ጉዳይ በጭንቀት መብሰልሰል ማቆም ተስኗቸዋል በተለይ የልጇ ሄኖን ከልክ ያለፈ ጭንቀት ከምንም በላይ አሳስቧቸዋል። አክስቱ ሰንቅነሽና ትናንሾቹ እህቶቹም ቢሆኑም ከወይዘሮ የትናየት ከሚደርሳቸው አንዳንድ የውሸት ሰላምታዎች ባለፈ የብሩክን ድምፅ ለመስማት ናፍቀዋል።

ወይዘሮ የትናየት ዛሬ ቀኑ መልካም ነገር ይዞላቸው እንደሚመጣ

ውስጣቸው ይነግራቸዋል ምክንያቱም ቀኑ መልካሙ ቀን እሁድ ነበር ዘወትር እንደሚያደርጉት በማለዳ ተነስተው በአልጋቸው ጠርዝ ላይ ተንበርክከው ፀሎት ካደረጉ በኋላ ቤቱን በመንፈሳዊ ዝማሬ ሞቅ ሞቅ በማድረግ ቡና እና ቁርስ በማዘጋጀት የብሩክን አክስት ስንቅነሽንና ትንንሾቹን እህተማማቾቹን ጋበዟቸው።

ሲሳሳቁ ፣ ሲጨዋወቱና ሲደሰቱ ካረፈዱ በኋላ የፀሀዩ ንዳድ ከረር ሲል ጥላሁን ደጅ ቆሞ ተጣራ "እማማ ... እማማ "

በድንገት የተጠሩት ወይዘሮ የትናየትም ሶፋውን ተደግፈው እየተነሱ " ማነው ? መጣሁ "እያሉ ከቤቱ ወጡ

"ሰላም ቆዩ እማማ አስታወሱኝ ? የብሩክ ጓደኛ ነኝ ጥላሁን "በማለት ከቤቱ ይወጡ ለነበሩት ወይዘሮ የትናየት ማንነቱን ገለፀ

ወይዘሮ የትናየትም ከቤታቸው በረንዳ ደረጃውን እየወረዱ "አዎን ልጄ አስታውሼሀለው እንደው እባክህ ንገረኝ እስቲ ብሩክን አግኝተኸው ታውቃለህ "በማለት ወደ ሳሎኑ በር እያዩ ጠየቁት

ጥላሁንም ብሩክን ማግኘቱን ፤ ስልኩ እንዳይሰራ ያደረገበት ምክንያት ፤ ትምህርት መጀመሩን እና የሚኖርበትን ቤት ሁኔታ ገልጾላቸውና አዲሱን የብሩክ ስልክ ሰጥቶአቸው ወደ ገጠር ለመሄድ እንደሚቸኩልና ምናልባት ሲመለስ ሊጠይቃቸው እንደሚሞክት ተናግሮ ተሰነባበቱ።

ይሄ ለወይዘሮ የትናየት ተዓምር ሆኖባቸዋል እንደጠበቁትም ቀኑ መልካም ነገርን ይዞላቸው መጥቷል ። አምላካቸውን እያመሰገኑ ጥላሁን በሰጣቸው ስልክ ቁጥር ደወሉ

ብሩክ ስልኩን አንስቶ የወይዘሮ የትናየት ድምፅ ሲሰማ እጅግ ተደሰተ ምን አጋጥሞት እንደጠፋ ፣ የእህቶቹን ድምፅ ለመስማት መጓጓቱንና ሁሉም

እንደናፈቁት በተለይም ሄኖን እንደናፈቀችው ተናግሮ ወይዘሮ የትናየትን ከእህቶቹ እንድታገናኘው ጠየቃት። ወይዘሮ የትናየትም አክስቱ እና ልጆቹ እንዳይጨነቁ በማሰብ እስከዛሬ አለመደወሉንና ምን እንደተፈጠረ ስለማያውቁ በርጋታ እንዲያናግራቸው አስጠንቅቀው የስልኩን ድምፅ ከፍ በማድረግ ለሁለቱ ህፃናት ሰጧቸው

"ሄሎ ብሩክ "

"ሄሎ ህሊ እና ሜሪ እንዴት ናችሁ ትምህርት ጥሩነው ? ትልቋ እማማ ያጫውቷችኋል ?" በማለት በህፃን አነጋገር አናገራቸው

ሁለቱም በየተራ እያወሩ "ደህና ነን ከትምህርት ቤት ደሞ የቤት ስራ ሲሰጠን ትልቋ እማማ ታስረዳናለች እእእእ ደሞ ቲቪ ትከፍትልንና ታጫውተናለች መዝሙርም ታለማምደናለች "እያሉ ነገሩት

ብሩክም ትንሽ ካናገራቸው በኋላ ከአክስቱ ጋር ተነጋግሮና እንዳይጠፋ ማስጠንቀቂያ ተቀብሎ ስልኩን ዘጋው።

ብሩክ በውስጡ ሰላም ተሰምቶታል ጠፍተውበት የነበሩትን ቤተሰቡን አግኝቷል አሁን ከትምህርቱ ሌላ የሚያስጨንቀው ጉዳይ የአጎቱ ብቻውን በገጠር መቀመጥ ስለነበር ጥላሁን አንዳች ነገር አድርጎ ይመጣል በሚል እምነት ጭንቀቱን ረሳው።

****

"ሄሎ የኔ ልጅ "አሉ ወይዘሮ የትናየት በተደሰተ መንፈስ ሆነው

"ሄሎ ማም how are you doing ?" በማለት ሄኖን ተቀዛቅዛ መለሰችላት

" የኔ ልጅ የምስራች ! ብሩክ ተገኝቷል ስልኩን ያኔ አንቺ የደወልሽለት ጊዜ ተነጥቆ ነበር አዲሱን ቁጥር እልክልሻለው " በማለት ተቻኩለው ያምስራቹን አበሰሯት

"Are you kidding me ? ማም እየቀለድሽብኝ ነው "

"አይደለም እውነቴን ነው ፤ ደሞ ችክ አትበይ "

"ማም ይሄ ለኔ ምን ያህል ደስታን እንደሚሰጠኝ ታውቂያለሽ አደል " በማለት የደስታ ላቅሶ አለቀሰች

ወይዘሮ የትናየትም " በይ በይ ልጄ አሁን ስልክ ቁጥሩ አስልክልሻለው ትደውይለታለሽ በማለት ምላሿን ሳይጠብቁ ቁጥሩን ለማስላክ ወደ ግቢው ተከራዮች ወጡ።

****

ብሩክ የቀኑ ውሎ አድክሞትና አምሽቶ ስለገባ ከአዛውንቱ የቀረበለት የእራት ግብዣን በመተው ወደ ክፍሉ በመግባት ልብሶቹን በነሲብ ከወረወረ በኋላ አልጋው ላይ በደረቱ ለጥ እንዳለ በድንገት የብሩክ ስልክ ጠራ ብሩክም በዳሰሳ አይኑን ሳይከፍት ስልኩን አንስቶ በደከመ ድምፅ

" ሄሎ" አለ

"ሄሎ ብሩኬ ሄኖን ነኝ " በማለት ስትመልስለት ድባቴውና ድካሙ ተረስተውት ከአልጋው ተስፈንጥሮ በመነሳት

"ሄኖን ? እንዴት አለሽ ? ባለፈው የደወልሽልኝ ጊዜ እኮ ስልኬ ተነጥቆ ነው ያላናገርኩሽ ደሞ ሌላ ..." በማለት ተንተባትቦ ሊቀጥል ሲል ሄኖን

አቋርጣው

"I know ብሩኬ ማም ሁሉንም ነግራኛለች " በማለት ከተናገረች በኋላ ሁለቱም ለትንሽ ጊዜ ዝም አሉ

ሄኖንም ዝምታውን ለመስበር " ብሩኬ ታስታውሳለህ ሀይስኩል ላይ እያለን ያሳለፍነውን ?" ስትለው ብሩክ እየተደሰተ

" አዎ ... አዎ በደንብ አስታውሳለው "

"እሺ የት ነበር ለመጀመርያ ጊዜ የተገናኘነው" በማለት የድምጿን ቅላፄ በመለወጥ ስትጠይቀው ብሩክ በሀሳቡ የኋሊት ተጉዞ በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ክበብ ጋር የተፈጠረውን አስታወሰ ፤ ሄኖን ከሌሎች ጓደኞቿ ጋር እየተሳሳቀች ስትገባ አስታውሷል።

" ካልተሳሳትኩ የተማሪዎች ክበብ ?"

" you are my hero "

"ታውቂያለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ እማማ ስልክሽን ሰጥተውኝ ስደውልልሽ አንቺ መሆንሽን አለማመን አልቻልኩም ነበር ፤ ድምፅሽ ፤ ቶሎ ቶሎ የምታወሪው ነገር በቃ ጠርጥሬ ነበር"

" come on ብሩኬ አሁን አገኘኸኝ አይደል ምንድነው ማለቃቀስ " በማለት ሳቋን ለቀቀችው

ብሩክና ሄኖንም እስከ ምሽቱ ሰባት ሰዓት ድረስ እያወሩ አንዳንዴ ቁም ነገር እንዳንዴ ደግሞ ተቀላልደው እየሳቁ ጨርሰው እንደሚደዋወሉና እንደሚነፋፈቁ ተነጋግረው ስልኩን ዘጉት።

ብሩክ ቀኑን ሙሉ ያደረበት ድካም ማን እንዳንከባለለት ባይገባውም

የሄደውን ሰዓት እየተመለከተ ስለ ሄኖን ማሰብ ጀመረ።

"ወይ ጊዜ ? ምን አታሳይኝ !" እያለ በረጅሙ ተንፍሶ ስለ ሄኖን አባት መሞት ማሰብ ጀመረ እሷ አባቱ የሞተ ጊዜ በተደጋጋሚ ገጠር ድረስ በመሄድ አፅናንታዋለች እሱ ግን የሚያውቀው ነገር ስላልነበር ምንም አላደረገም ስለዚህ ራሱን መውቀስ እንደሌለበት አሳምኖ ጠዋት ለሚጠብቀው ትምህርት ለመዘጋጀት ትንሿን ሞት ሞተ።

****

ሄኖን በበኩሏ ስለ ብሩክ ማሰብ ማቆም አልቻለችም ያኔ የምታውቀው ቀይ ፣ ደልደም ያለ ሰውነት ያለውና ረጅሙ ባለ ሉጫ ፀጉሩ ብሩክ በአዕምሮዋ እየመጣ በምናብ ታናግረዋለች

"ብሩኬ ?"

"ወይ"

"እኔ ለአንተ ምንህ ነኝ ?"

" ሁሉም ነገሬ "

" ሄኖን ምን እየሆንች ነው ?" በማለት ለራሷ ከጠየቀች በኋላ ወደ እኩለ ለሊት እየተሸጋገረ የነበረው የቀኑን ክፍል በእንቅልፍ ለማሳለፍ ወደ መኝታዋ አመራች።

ዘራ

ብሩክ ይሄኛው ትምህርቱ ጠጠር ቢልበትም ያለ እረፍት በማጥናትና የሚሰጡትን ሰራዎች በቅልጥፍና እና በአግባቡ ሰለሚሰራ እንደለመደው ከአስተማሪዎቹ አድናቆት ይበረከትለታል።

ነገር ግን ዩንቨርስቲውን እንዲጠላው ያስደረገው አንድ ነገር ነበር "ትዕግስት"

ስሟ እና ምግባሯ ለየቅል የሆነበት ብሩክ እለት እለት ውሀ ውሀ ከሚሉ ንግግሮቿ እና ጥያቄዎቿ ለመሸሽ ወደ ግቢው ላለመሄድ ቢመርጥም የሚያመልጡት የትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን አስቦ አለመሄዱን ይተወዋል።

ዛሬ ግን የሱ እና የሷ ግንኙነት አንድ ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለበት ሰላመነ በግቢው ወደሚገኘው የተማሪዎች ካፌ ቀጥሯታል

ከቀጠሮው ሰዓት ሁል ጊዜ ቀድሞ የሚገኘው ብሩክ ሻዩን እየጠጣ ተቀምጧል

ከኋላውም ትዕግስት እየተፍነከነከች መጥታ አይኑን በሁለቱም እጆቿ በመያዝ ድምጿን በመቀየር " ማን ነኝ ?" ስትለው ብሩክ ሁለቱም እጆቿን ከአይኑ እያነሳ ዞር ብሎ ተመልክቶ "እባክሽ ተቀመጪ " በማለት ወደ ወንበሩ ጠቆመ

ትዕግስትም አኩርፋ ወደ ወንበሩ ሄዳ ተቀመጠች

ብሩክም የካፌውን አስተናጋጅ በእጁ ምልክት ሰጥቶ እየጠራ "የሆነ ነገር እዘዢ " በማለት ተመለከታት

ትዕግስትም አሁንም በማኩረፍ " ከፍትፍቱ ፊቱ ሲባል አልሰማህም ? ምንም አልፈልግም ይቅርብኝ " በማለት እጇን በደረቷ አጣጥፋ አንገቷን

ሰብራ ተቀመጠች

ብሩክም ለአስተናጋጁ ሁለት ለስላሳ እንዲያመጣ አዘዘ

"ለምን እንደጠራሁሽ ታውቂያለሽ ?" በማለት ከገባችበት ድብርት ለማውጣት ጥያቄ አቀረበለት

ትዕግስትም ትከሻዋን ወደ ላይ ሰብቃ መለሰችለት

ብሩክም በዚህ ሁኔታ መቀጠል ስላልፈለገ "እሺ በቃ ይቅርታ " በማለት ተናገረ

ትዕግስትም ቀና ብላ እያየችው " ካሁን በኋላ አይለመድህም ?"

"አዎ"

"እሺ ይቅርታ አድርጌልሀለው እንታረቅ" በማለት የቀኝ እጇ ትንሿን ጣት ዘረጋችለት

ብሩክም እየሳቀ ጣቱን ዘርግቶላት ከታረቁ በኋላ

" እሺ ለምን ነበር የጠራኸኝ ?" በማለት ጠየቀችው

ብሩክም " ምን መሰለሽ የአንቺን ባህሪ መላመድ በጣም ከብዶኛል ችኩል ነሽ ፣ ስለምን እንደምታወሪ አታስቢም ፣ ስነምግባርሽ ልቅ ነው ደሞ ስርዓት የለሽም " ለማለት አሰቦ

" በእኔና በአንቺ መካከል ምን አይነት ግንኙነት እንዲኖር ነው ምትፈልጊው ?" አላት

ትዕግስትም የመጣላትን ለስላሳ አንዴ ተጎንጭታ " የጓደኛ ነዋ !"

" ምን አይነት ጓደኛ ?"

"አለ አደል የክፍል ምናምን ምናምን የሚባል "በማለት ደንታ በሌለው አነጋገር መለሰችለት

ብሩክም "እንጂ የፍቅር ጓደኛ አይደለም ?" በማለት መልሱን በጭንቀት ጠብቆ ሲጠይቅ ትዕግስት እየሳቀች "ያምሀል እንዴ ? አይደለም "በማለት ጭንቀቱን አረገበችለት ።

****

ብሩክ ነገሮች ሁሉ አልጋ ባልጋ ሆነውለታል ባይባልም ከሞላ ጎደል የማህበረሰቡን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችለውን መንገድ በአግባቡ እየተጓዘው ነው ።

ምስጋና ለአባቱ ጓደኛ አዛውንት ይሁንና ከቤቶቹ ኪራይ የሚያገኘው ገንዘብ ከአክስቱ ፣ ከአጎቱ ፣ ከጥላሁንና ከራሱ አልፎ መቆጠብ ጀምሯል።

ታናናሽ እህቶቹን ፣ አክስቱን ፣ ወይዘሮ የትናየትን ፣ አጎቱንና ሄኖን ጋር በየጊዜው እየደወለ ደህንነታቸውን ይጠይቃል ።

ብሩክ የአመቱ መጠናቀቂያ ላይ የሚሰጠው ጠቅላላ ፈተና ዝግጅት ጀምሯል ጥላሁንም ቢሆን የፈተናው ወቅት ስለደረሰ በራሱ ውጥረት ውስጥ ገብቶ ለፈተና እየተዘጋጀ ነው።

ብሩክ ሀገር አማን ብሎ ለፈተና እየተዘጋጀ በነበረበት ወቅት እንግዳ የሆነ ስሜት ቀኝ እግሩ ላይ ይሰማዋል ስሜቱ የነበረበት ያኔ ወደወንዝ ወርዶ ዝናብ ከደበደበው ጊዜ ጀምሮ ቢሆንም ከዛሬ ነገ ይሻለኛል በማለት ችላ ብሎት ነበር። የዛሬው ግን እረፍት ስለነሳው ወደ ሆስቲታል በመሄድ ለመታየት በማሰብ ለጥላሁን እንዲያብረው ለመጠየቅ ፈልጎ የፈተና

ዝግጅት ላይ ስለነበር ብቻውን ወዳ ሆስፒታል ሄደ።

ሆስፒታሉ ደሰ የሚሉ ህንፃዎች አሉት የታካሚን መንፈስ በሚያነቃቁ ነጭ ቀለማት የተዋቡ ግድግዳዎችና ነጭ ካባ ለብሰው ወድያ ወዲህ የሚራወጡ ሀኪሞችና ዶክተሮች ተመለከተ ጊዜ ሳያጠፋም ወደ ካርድ ክፍል በመሄድ ካርዱን አውጥቶ ወደ ተጠቆመው ክፍል በሩን አንኳኩቶ ገባ።

ፈገግታው በሸታን የሚሸር ፣ ጠይም ፊት ያለው እና የጉንጩ እና የአገጩ ፂም የተንዠተገገ ዶክተር ከመቀመጫው በመነሳት "ቁጭ በል " በማለት ህመሙን በትህትና ጠይቆ እግሩን ራጅ ሊያነሳው ወደ ማሽኑ ሚገኝበት ክፍል ተያይዘው አቀኑ።

ዶክተሩ የተነሳውን ራጅ እያየ " ብሩክ "

"አቤት"

"ከዚህ በፊት በጉልበትህ የወደክበት አጋጣሚ አለ ? ማለቴ ድንጋይ ላይ ወይም ደረቅ አፈር ላይ ?" በማለት ጠየቀው ብሩክም የዝናቡ ጊዜ ትዝ እያለው

"አዎን ድንጋይ ላይ ወድቄ ነበር ግን ከአንድ አመት በላይ ሆኖታል "

ዶክተሩም " እምምም አየህ እዚህ ጋር " በማለት የራጅ ምስሉን እያሳዩት "ስንጥቅ ተፈጥሯል በቶሎ መሞላት አለበት እዚህ ሀገር ውስን የአጥንት ዶክተሮች ቢኖሩም ይሄ ግን እዚህ ሀገር ሊሰራ የማይችል ነው አቅሙ ካለው ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄደህ መታከም ትችላለህ ። ታድያ መፍጠን አለብህ አለበለዚያ ስንጥቁ እየሰፋ ሄዶ እግርህን ሊያሳጣህ ይችላል ።" በማለት የእግሩ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መሆን ገለፁለት።

ብሩክም ዶክተሩን ተሰናብቷቸው ወደ ቤቱ እየሄደ ማሰብ ጀመረ "እኔን ላስቀድም ወይስ ህዝቤን ? "

"ኣይ እኔን ማስቀደም አለብኝ ለምን እግሬን ኣደጋ ላይ እጥለዋለው?"

"ኣይ ኣይ የኔ ነገር ቀስ ብሎ ይደርሳል አሁን ለመጣሁበት አላማ መጋደል አለብኝ ማህበረሰቡንም ነፃ ማውጣት አለብኝ " በማለት ከራሱ ጋር ከተከራከረ በኋላ የእግሩን ጉዳይ ወደ ጎን አድርጎ ትምህርቱን መቀጠሉን መረጠ።

****

ሰአታታት ቀን እየሆኑ ቀናት ሳምንት እየሆኑ ሳምንታት ወር እየሆኑ ወራት አመታት እየሆኑ ኣይደርስ የለም የትምህርቱ መጨረሻ ደረሰ በቆይታው ሁለት ጊዜ ወደ አገርቤት እና ወደ ወይዘሮ የትናየት ቤት በመሄድ ጠይቋቸዋል ጥላሁንም ከስድስት ወር በፊት የህግ ትምህርቱን ተከታትሎ በዲፕሎማ መርሀግብር ተመርቆ የዲግሪ መርሀ ግብሩን ቀጥሏል።

ብሩክ በቆይታው የማይረሳው ጊዜ ቢኖር ሄኖን ለሁለት ሳምንት እረፍት በመጣች ጊዜ አብረው ያሳለፉት ቆይታ ነው።

ያኔ ሀይስኩል እያሉ በችኩልነቷ የሚያውቃት ሄኖን ቁም ነገረኛ ፣ ቁጥብ እና ውብ ሆና ነው ያገኛት። ጊዜውን ወደ መዝናኛ ቦታዎች በመሄድና በመዝናናት ነበር ያሳለፉት።

ከትዕግስትም ጋር ቢሆን እንደነገረችውም መልካም ጓደኛሞች ሆነዋል ይበልጥ ደግሞ ከብሩክ ጎን ከማይጠፋው ከጥላሁን።

የፈተናው ወቅት በበቂ ዝግጅት አሳልፎ ፈተናውን ተፈትኖ የውጤት መግለጫውን ለመስማት የትምህርት ቤቱ ዘርፍ ተቆጣጣሪ በመማርያ ክፍል ውስጥ እንዲሰበሰቡ ነግሯቸዋል።

ብሩክ ከጥላሁን ጋር የመጣ ቢሆንም ጥላሁን ውጭ መቆየትን ስለመረጠ ብሩክ ውጤቱን ሊሰማ ወደ ክፍሉ ገባ።

ተቆጣጣሪው ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ በመምጣት ሰፊ ወረቀት ይዞ "እሺ ተማሪዎች ያሳለፋችሁት ጊዜ መልካም እንደነበር አልጠራጠርም ምክንያቱም ሁሉም ተማሪ ያመጣው ደስ የሚልና የሚያበረታታ ውጤት ነው።

ነገር ግን በቃላችን መሰረት ከፍተኛ ውጤት ለሚያመጡ ሁለት ተማሪዎች ነፃ የትምህርት እድል እንደምናመቻች ስለገለፅን የነፃ የትምህርት እድሉ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ተማሪዎች አሁን እጠራለው ሌሎቻችሁ ውጤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ስለሚለጠፍ ታገሱን ።

እእእእእእ ሁለቱ ተማሪዎች ..... "በማለት ተማሪውን ለማጓጓት ሲሞክሩ የክፍሉ ተማሪዎች እርስ በእርስ መተያየት ጀመሩ

ተቆጣጣሪውም ቀበል አድርጎ "ከወሰዳቸው ስምንት ኮርሶች ሰባቱን A+ በማምጣት አንዱን A- በማምጣት በአራት ነጥብ ሁለተኛ ሆኖ የነፃ የትምህርት እድሉ ተጠቃሚ የሚሆነው አንተነህ በላይ ሲሆን "በማለት ንግግሩል ለመቀጠል ቢሞክርም ክፍሉ በጭብጨባ ስለተረበሸ ዝም በማለት ጭብጨባው ጋብ እስከሚል ታግሶ ንግግሩን ቀጠለ

"እሺ ተማሪዎች ፀጥታ ! ሁለተኛው ተማሪ አንተነህ በላይ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከወሰዳቸው ስምንት ኮርሶች በማይታመን መልኩ ስምንቱንም A+ በማምጣት አንደኛ የወጣው "በማለት ተማሪዎቹን ለማጓጓት ዝም አለ

የዚህን ሰዓት ብሩክ እጁ እና እግሩ ይንቀጠቀጥ እንደነበር ለማስተዋል ፋታ ስላገኘ ራሱን ለማረጋጋት ሶስት ጊዜ በረጅሙ ተንፍሶ የውጤት መግለጫውን መጠበቅ ጀመረ።

"ብሩክ ፈይሴ "በማለት ጮክ ብለው ሲናገሩና ክፍሉ በጩኸትና በጭብጨባ ሲደባለቅ ውጪ ቆሞ ሲጠብቅ የነበረው ጥላሁን የብሩክን ስም መጠራት እና ጭብጨባውን ሰምቶ "እንደምታዳርገው አውቅ ነበር " በማለት ፈገግ አለ።

****

ብሩክ የነፃ ትምህርት እድሉን ባገኘባት እንግሊዝ ሀገር የማስተርስ ዲግሪውን ውጭ ሀገር ለመማር ዝግጅት እያደረገ ነው። ከጎኑ የማይጠፋው ጥላሁንም ለብሩክ ጉዞ የሚያስፈልጉ አንዳንድ ነገሮችን ለማሟላት ላይ ታች እያለ ነው ምክንያቱም የትምህርት እድሉ የምዝገባ ጊዜ ከአንድ ሳምንት በላይ እንደማይቆይ የትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ትምህርት የዘርፍ ተቆጣጣሪ ስለነገራቸው ነው።

"ማን ያምናል አሁን ብሩክ ከሀገር ሊወጣ ነው ቢባል ? ደሞ ውጭ ሀገር ትል ይበላሉ ይባላል ሆቴል ከገባህ ፓስታ እንዳታዝ እሺ ፤ ደግሞ ሰጋም እንዳታዝ የፈረስ ወይም የአህያ ሊሆን ይችላል "እያለ ጥላሁን ይቀልድበታል

ከሀገር ከመውጣቱ በፊትም ቤተሰቦቹን ለመሰናበት ቢፈልግም የተሰጠው ጊዜ አጭር በመሆኑ በጥላሁን በኩል መልዕክት ለማድረስና የአባቱ ጓደኛ የነበሩትና የአዲስ አበባ ቆይታው እንዲቀልለት ያደረጉት አዛውንቱን ለማመስገን ግቢው ውስጥ ግብዣ ለማድረግ አስቧል።

የጥላሁንም ትምህርት መጀመሪያ ጊዜ ስላልደረሰ ግብዣውን ለማድረግና ብሩክን ለመሸኘት ላይ ታች በማለት መድከሙን ተያይዞታል።

ብሩክ ከሀገር ሊወጣ ሶስት ቀን ሲቀረው ግብዣው በአዛውንቱ ቤት ተደረገ ሶስቱ የቤቱ ተከራዮችም ወደ ግብዣው ታድመዋል ጥላሁንም ብሩክን ወደ በረንዳው በማውጣት "ብሩኬ ሰርፕራይዝ አለህ እዚሁ ጠብቀኝ "ባለት እየተንኳኳ የነበረውን በር ለመክፈት ሮጠ

ጥላሁን በሩን ሲከፍተውና ወይዘሮ የትናየት ፣ አጎቱ እና አክስቱ እንዲሁም ሁለቱ መንትያ እህቶቹ ተከታትለው ሲገቡ ብሩክ በደስታ ከበረንዳው እየሳቀ ወረደ ። ሁሉንም በየተራ ካቀፈና ሰላም ካለ በኋላ እንዲገቡ እየነገረ ጥላሁንን ወደ ኋላ አስቀርቶ

"ጥሌ ለምን አስቸገርካቸው ? "በማለት ሲጠይቀው ጥላሁን

" ወይዘሮ የትናየት ናቸው መቸኮልህንና መጥተህ እንደማትጠይቃቸው ሲያውቁ ሀሳቡን አነሱት እኔም ተስማማሁ ፤ ይልቅ ገብተህ አስተናግዳቸው "ብሎት አልፎት ሊሄድ ሲል ብሩክ የጥላሁንን እጅ በመያዝ

"ጥሌ አመሰግናለው ትልቅ ስራ ነው የሰራኸው "ሲለው ጥላሁን "እኔ ምን አደረኩ ? ይልቅ ወይዘሮ የትናየትን አመስግን ፤ በል ና እንግባ እየጠበቁን ነው "በማለት ተያይዘው ገቡ።

አክስቱ ጪስ ያደፈረሰው አይኗ ጠርቶና ሸክም ያጎበጠው ወገቧ ተቃንቶ አምሮባት በባህል ልብስ ነው የመጣችው ታናናች እህቶቹም ቢሆኑ ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው ፍንድቅድቅ በማለት ነበረ የመጡት ፤ ወይዘሮ የትናየትም ቢሆኑ የደስደስ ያለው ፊታቸውና ልብሳቸው አብረው ልዩ

የእናትነት ውበትን አጎናፀፏቸዋል ፤ አጎትየው ግን መጠጥ በማብዛቱ ምክንያት ከሰውነት ተራ ወጥቶ ተጎሳቁሎ ነበር ።

ቤቱ በሰው ተሞላ የቤቱ ባለቤት አዛውንትም ከተቀመጡበት ሶፋ ለመነሳት እየሞከሩ "ልጆች ቆይ አንዴ የማወራው ነገር አለኝ " በማለት ተነሱ ቤቱም ፀጥ አለ

አዛውንቱም በደከመ ድምፅ ንግግር ማድረግ ጀመሩ

"ልጆቼ አንድ ጊዜ ሰሙኝ ይሄ እንደ ሰሙ ብሩክ የሆነ ልጅ እዚህ ቤት ሲመጣ ደስታዬና የሰው ናፍቆቴ ተመልሶልኛል ከሀያ አመት በፊት ሚስት አግብቼ ልጅ ወልጄ በዚህ በምታዩት ግቢ እኖር ነበር ግን አንድ ቀን ሚስቴና የወለድኩት የአምስት አመት አንድያ ልጄ የመኪና አደጋ ነጠቀኝ ከዛ እለት ጀምሮ በቤቱ አንድ ሰው እኔን ለመጠየቅ ዝር ብሎ አያውቅም ደስታዬ ተነጠኩኝ ፤ ሚስቴና ልጄን ነጠቁኝ " በማለት እንባቸውን ከአይናቸው ጠርገው ንግግራቸውን ቀጠሉ

" ልጄ ግን ደስታዬን መለሰው : ቤቱ ሰው ሰው እንዲል ደግ የሆኑ እንደልጅ የማያቸው ተከራዮች አመጣልኝ እሱ ራሱ እንደ አባቱ ደግ ነው ፣ ምንም ክፋት አያውቅም ልጆቼ አሜን በሉ ልመርቀው " በማለት ከተናገሩ በኋላ ተከራዮቹና የብሩክ ቤተሰቦች ካለ ድምፅ ይፈሰ የነበረው እንባቸውን እየጠገጉ የአዛውንቱን ምርቃት ለመቀበል እጃቸውን ዘረጉ።

****

እንግሊዝ ሀገር አየር ማረፍያ እንደደረሰ የትምህርት ጉዳዩንና አንዳንድ

ነገሮችን ለማስፈፀም ከኢንባሲው ኤርፖርት ድረስ በመሄድ ይቀበልሀል የተባለውን ሰው በአይኑ እያማተረ ወደ ፊት ገሰገሰ ከፊት ለፊቱም በቅርብ ርቀር ላይ ሆኖ ሙሉ ሱፍ የለበሰ አጭርና ጥቁር ሰው እጁን እያወናጨፈ " ብሩክ "እያለ ስለተጣራ ወደ ሰውየው አመራ።

ሰውየውም "ነህምያ እባላለው" በማለት ስሙንና ከየት እንደመጣ ካስተዋወቀው በኋላ ሻንጣውን ተቀብሎ ወደ አየር ማረፍያው መውጫ ሄዱ።

ሰውየው መኪናውን በእንግሊዝ ጎዳናዎች እያሽከረከረ "ከኢትዮጵያ ትሻላለች ኣይደል ?" በማለት ጠየቀው

ብሩክም ጎዳናዎቹ ዳር እና ዳር የተገነቡት ውብ ቤቶችና መንገዱን እያየ"አዎ በትንሹ " በማለት መለሰ

" በትንሹ ? ማለት ? " በማለት ሰውየው ግራ ተጋብቶ ሲጠይቅ

" አዎ ይቺን ሀገር እዚህ ያደረሳት የህዝቦቿ ቅን አሳቢነትና ጊዜ የሰጣት እድል ነው ኢትዮጵያም ቅን አሳቢዎች ካሏትና ህዝቦቿ ጊዜ ያመጣላቸውን እድል መጠቀም ከቻሉ ከዚህ የተሻለች ሀገር መሆን ትችላለች የጊዜ ጉዳይ ነው ፤ ሁሉም አላማውን ካወቀና ለምን እንደሚኖር ከተረዳ አንዱ በአንዱ ላይ ጥገኛ የሚሆንበትና እርዳታን የሚጠይቅበት ምንም ምክንያት አይኖርም ::" በማለት ሲመልስ ሰውየው ብሩክ ያነሳው ሀሳብ ስለተመቸው ሌላም ጥያቄ ጨመረለት

" የቅን አሳቢ ሰዎች ጉዳይ እንተወውና እንዴት ነው ጊዜ ያመጣልንን እድል መጠቀም የምንችለው ?" በማለት የትራፊክ መብራት ያስቆመውን መኪና እያስነሳ ጠየቀው

ብሩክም ከጥቂት አመታት በፊት ገጠር በሚኖርበት መንደር መጥተው

የነበሩት ባለሀብቶች ጉዳይ አንስቶ ከነገረው በኋላ

"እና በሰው አዕምሮ ማሰብ ስንጀምር ጊዜ ከሚያመጣልን እድል ጋር እንተላለፋለን ነገር ግን በራሳችን አዕምሮ ማሰብና ሁኔታውን መገንዘብ ከቻልን የትኛው ጊዜ ያመጣልን እድል እንደሆነ እንረዳለን።" በማለት መለሰለት

ሰውየው ብሩክ በነገረው ታሪክና በሰጠው ማብራሪያ እየተደሰተ እና ኢትዮጵያ ላይ እንደዚህ አይነት ልማድ በመኖሩ እየተገረመ "በእውነት አንተ ይሄ የትምህርት እድል ይገባሀል ለኢትዮጵያ ትጠቅማታለህ ። ለመሆኑ ትምህርት ከጨረስክ በኋላ አላማህ ምንድነው ?" በማለት ጥያቄ አነሳለት

ብሩክም የተለያዩ ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ ሰራዎችን መስራት እንደሚፈልግና ከቻለ ከዚሁ ሀገር በጎ አድራጊዎችን እንደሚያፈላልግ የትምህርት ወቅቱ ከመጠናቀቁ በፊትም አንድ የረባ ነገር ላደገበት ማህበረሰብ ማድረግ እንደሚፈልግ ተናገረ።

ሰውየውም አላማው ትልቅ እና አስፈላጊ እንደሆነ ስለተረዳ የሚያውቃቸው የበጎ አድራጎት ማህበራትን እንደሚያናግርለትና እርሱ ብቻ በርትቶ የመጣበትን አላማ እንዲያሳካ እየነገረው ወደ ትምህርት ቤቱ አቀኑ።

****

ምንም እንኳ እንግሊዘኛ የሁሉም ኮርሶች መማሪያና የሁሉም ተማሪዎች መግባቢያ ቢሆንም ብሩክ ግን የቋንቋ ችግር አልገጠመውም።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከእንግሊዝ ኤንባሲ ጋር ሆነው እየከፈሉ

ያስተምሩታል ፤ ቤትም ተከራይተውለታል የቤተሰቡ ናፍቆት እንዳያስቸግረውም በድምፅ ብቻ ከማውራት አልፈው በምስል ፊት ለፊት እየተያዩ እንዲያወሩ ጥላሁን አዲስ ስልክ ለአክስቱ ገዝቶ ሰጥቸዋል።

ሄኖን ብትሆንም ነፃ የትምህርት እድል ባገኘ ማግስት ደስታዋን እየጮኸች እየገለፀች እናግራዋለች ፤ እዚህ ሀገር ከገባ ጊዜም ጀምሮ ልክ እንደ አክስቱና እህቶቹ በምስል እየተያዩ ለረጅም ሰዓት ያወራሉ።

ግራ የገባውና መልስ ያጣለት ጉዳይ ግን የአጎቱ ጉዳይ ነው ። አጎቱ የወንድሙ ጓደኛ የሆኑት አዛውንት መጎሳቆሉን አይተው " ከኔው ጋር ኑር ምንም አይቸግርህም " ቢሉትም አጎትየው በዘራ መንፈስ እምነት ተተብትበው መንደሩን ለቅቄ አልወጣም እንቢ አሻፈረኝ ብለዋል።

ለነገሩ የብሩክ አባት ብቻ ሳይሆን የሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን በጥንስስ ሴራቸው ተብትበው አስተሳሰባቸው ከመንደር እንዳይዘል ያደረጉት አንዳንድ የመንደሩ ሰዎች ከመንደሩ የመውጣት እድል ሲገጥማቸው አሻፈረኝ ይላሉ። ስለዚህ የአጎቱም ችግር ከነዚህ ትብታብ ከተሰራባቸውና አስተሳሰባቸው ከመንደሩ እንዳይወጣ ከተደረጉ ሰዎች እንደ አንዱ ስለሆነ አጎቱን ከመንደሩ ሰዎች ጋር አዳብሎ ችግራቸውን ሊፈታ እየተማረ ይገኛል።

ጥላሁንም ቢሆን ከትምህርቱ ጎን ለጎን ወደ ገጠርና አክስቶቹ ወዳሉበት ከተማ በመሄድ የብሩክ ቤተሰቦች ሁኔታ እያየ ብሩክ ለጥላሁን አደራ ሰጥቶት ከሄደው ከቤት ኪራይ ገንዘብ ቀንሶ አስፈለጊው ነገር እያደረገ መሆኑን ወይዘሮ የትናየት አጫውታዋለች።

****

ብሩክ በሳምንቱ መጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ ኢንባሲ ከአየር መንገድ የተቀበለውና በጎ አድራጊ ድርጅቶች እንደሚያናግርለት ቃል የገባው ነህምያን ፍለጋ አመራ።

የተወሰኑ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ቢሮው ውስጥ ነበሩ ብሩክም ወደ አንዱ ኢትዮጵያዊ ሰራተኛ በመሄድ "ይቅርታ አቶ ነህምያን አገኘዋለው ?" በማለት በትህትና ጠየቀ

የኢንባሲው ሰራተኛም " ቀጠሮ ይዘህ ነበር ?" በማለት ጠየቀው

"አይ አልያዝኩም " በማለት ሲመልስ እሺ ቆይ አንዴ በማለት ወደ ስልኩ ተንጠራርቶ ቁጥሮችን ከመታ በኋላ ስልኩ ተነሳ

" ሀሎ አለቃ እንግዳ ፈልጎህ ነበር ላስገባው ?"

"ማን ነው ታውቀዋለህ ?" በማለት አቶ ነህምያ ስለጠየቁት የስልኩን ጫፍ በእጁ በመድፈን እያንሾካሾከ

"ስምህ ማን ነው ?"

"ብሩክ"

"አለቃ ብሩክ ይባላል "

"አስገባው አስገባው " በማለት ስልኩን ዘጉት።

ሰራተኛውም " ሶስት ቁጥር ቢሮ ግባ " በማለት በጣቱ እየጠቆመ አሳየው

ብሩክም አመስግኖ ወደ ቢሮው ሲጠጋ አቶ ነህምያ የቢሮውን በር እየከፈቱ "ብሩክ እንኳን ደህና መጣህ " በማለት ሞቅ ባለ አቀባበል ተቀበሉት

ብሩክም በአቀባበሉ እየተደሰተ "እንኳን ደህና ቆያችሁኝ "በማለት ወደ ውስጥ ገባ ።

አቶ ነህምያም እንዲቀመጥ ነግረውት እንደ ባለ ጉዳይ ሳይሆን እንደ ጓደኛ ፊት ለፊቱ በመቀመጥ ትምህርት ቤት ስለእሱ ጉብዝና እንደሚወራ እና የመጣበት መንገድ ከአስተማሪው እስከ ተማሪው ያደነቀለት መሆኑን መስማቱን ነግሮት ለምን ጉዳይ እንደመጣ ጠየቀው።

ብሩክም አመጣጡ ባለፈው ስላወሩት ጉዳይና ድርጅቶቹን አነጋግሮለት እንደሆነ ሲነግረው ።

ነህምያ ከመቀመጫው እየተነሳ "አዎ ለማነጋገር ሞክሬያለው በኢትዮጵያ ወደ አምስት የሚጠጉ ድርጅቶች በበጎ አድራጎት ስራ መሳተፍ ይፈልጋሉ እነሱን አነጋግሬ እነዚህን ማብራሪያ የያዙት ወረቀቶች ሰጥተውኛል እስከ ነገ እያቸውና ነገ የተሻሉትን መርጠህ ይዘህልኝ ና "በማለት ከመደርደሪያው ውስጥ ወረቀቶችን ማውጣት ሲጀምር ብሩክ የአባቱ አደራ የሆነ ደረጃ ላይ መድረሱ እየተሰማው አቶ ነህምያን ካመሰገነው በኋላ ነገ የእረፍት ቀን በመሆኑ ኢንባሲው ዝግ ስለሚሆን ሌላ ቦታ እንዲገናኙ የአማራጭ ሀሳብ ብሩክ ስላቀረበ ነህምያ ትንሽ ካሰቡ በኋላ ስልክ ቁጥር ተለዋውጠው እንደሚደውልለት ነግረውት ወረቀቶቹን ይዞ ወጣ።

ብሩክ ወረቀቶቹ የያዙትን መረጃ ለማየት ስለጓጓ ወረቀቶቹን ማየት የጀመረው መንገድ ላይ ነበር። የንፁህ መጠጥ ውሀ ፣ የጤና ተቋም እና የትምህርት ቤት ግንባታ ላይ የሚያተኩሩት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መርጦ የጠበቀው ገና ቤቱ ሳይደርስ ነበር። ሌሎች ወረቀቶቹ ደግሞ የቆሻሻ አወጋገድና የልጆች እንክብካቤ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ስለነበሩ ለማህበረሰቡ እምብዛም አስፈላጊ ስላልነበሩና መቅደም ያለባቸው ስላልሆኑ ተዋቸው ።

ብሩክ ከጠዋት ጀምሮ የነህምያን ስልክ ሲጠብቅ ስለዋለ እኩለ ቀን አካባቢ የተደወለለት የነህምያን ስልክ ያነሳው በፍጥነት ነበር ነህምያም ወረቀቶቹን ይዞ እንዲመጣ በመንገር የሚገናኙበት ቦታ በምልክት ነግሮት ስልኩ ተዘጋ። ብሩክም ጊዜ ሳያጠፋ ወደተባለው ቦታ በፍጥናት በመሄድ ከነህምያ ጋር ተገናኘ ።

****

ከነህምያ የተገናኙ ጊዜ እንደተነጋገሩት የተመረጡት ድርጅቶች አንድ በአንድ በማናገር ምላሽ ለመጠበቅ ስለተሰማሙ በቅድሚያ ወደ ሆስፒታል ገንቢው ድርጅት ከነህምያ ጋር ለመሄድ ቢቀጣጠሩም ነህምያ በስራ ምክንያት እንደማይመጣ እና ራሱ ሄዶ እንዲያናግራቸው በስልክ ነገሩት።

ብሩክም ወደ ድርጅቱ በመሄድ ምን ማለት እንዳለበት ባያውቅም በእሺታ ስልኩን ዘግቶ ወደ ድርጅቱ አመራ።

ድርጅቱ አንድ ሰማይ ጠቀስ ህንፃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ብሩክ ወደ ህንፃው በመግባት ድርጅቱ ወደሚገኝበት ፎቅ ለመድረስ አሳንሰሩን ለትንሽ ደቂቃ ጠብቆ ሸቅብ ወደ ላይ ተጓዘ ።

የአሳንሰሩ በር ሲከፈትም ብሩክ በረጅሙ ደጋግሞ እየተነፈሰ ራሱን እያረጋጋ ወደ ድርጅቱ ቢሮ ተጠግቶ በሩን ቆረቆረ።

****

ጥላሁን ከዩንቨርስቲ አረፋፍዶ ሲመለስ ድንገት ሰልኩ ጠራ ብሩክ ነበር

"ሄሎ አቡሽ " በማለት ካለወትሮው በማይደውልበት ሰዓት መደወሉ እያስገረመው ተናገረ

"ሄሎ ጥሌ " በማለት ብሩክ መልስ ሲመልስ እያለቀሰ እንደነበር የድምፁ ቅላፄ ያስታውቅ ሰለነበር ጥላሁን በመደናገጥ

" ብሩክ ምን ሆነሀል ? ሰላም አይደለም ? ምንድነው የተፈጠረው ?" በማለት ከመንገዱ ቆም ብሎ ጠየቀው

ብሩክም እያለቀሰና ድምፁን ከፍ እያደረገ " ጥሌ አሳካሁት ፤ እሺ አሉኝ ፤ ፍቃደኛ ናቸው " አለ

ጥላሁንም ለቅሶው የደስታ መሆኑ ሰለገባው የደስታውን ምክንያት ለማወቅ በመጓጓት መንገዱን በመቀጠል " ምንድነው የሆነው እሱ ? አታስጨንቀኝ " አለው

ብሩክም ለመረጋጋት እየሞከረ " ጥሌ ሰሞኑን ለበጎ አድራጎት ሰራ ኢትዮጵያን ከመረጡ ድርጅቶች ጋር ንግግር እያደረኩ ነው ሆስፒታል በመንደራችን ሊሰሩልን ነው ፤ ሆስፒታል ለመስራት ፍቃደኛ ሆነዋል ፤ ጥሌ እየሰማኸኝ ነው ሆስፒታል !" በማለት የምስራቹን አበሰረው

ጥላሁንም " ምን ? ሆስፒታል ? እየቀለድክ ነው ?" በማለት ለማመን አንገራገረ

ብሩክም በረጅሙ ተንፍሶ " ጥሌ አልቀለድኩም ይልቅ የምታግዘኝ ትልቅ ስራ አለ እንቢ እንዳትለኝ " ሲለው

ጥላሁን እየተደሰተ "ከምርህን ነው ? እሺ ምን ልርዳህ ? " በማለት ይሄድበት ከነበረው መንገድ ራሱን ገትቶ ላይ ታች እያለ መንጎራደድ ያዘ

ብሩክም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ምን ምን እንደሚፈልጉ በትንሹ ከነገረው በኋላ ሙሉውን ቅፅ ልኮለት ለመንደሩ ሰዎች እንዲሞሉት እንዲያደርግና የተሞላው ቅፅ በፖስታ ቤት እንዲልክለት አክሎም ይሄ ወሬ ወደ መንደሩ አለቃ አቶ መኮንን ጆሮ እንዳይደርስ ጥረት እንዲያደርግ አሳስቦ ስለ ቤተሰቦቹ ከጠየቀው በኋላ ተሰነባብተው ተለያዩ።

ብሩክ በመቀጠል ወደ ነህምያ ጋር በመደወል ያቀረበላቸው ሀሳብ እንደተቀበሉትና አስፈላጊውን መረጃ ካሟላ ሆስፒታሉ እንደሚገነቡ ቃል እንደገቡለት ሲነግረው ደስታውን የሚገልፅበት ቃላት በማጣት በጩኸት ነበር ደስታውን የገለፀው ። ነህምያ በጣም ስለተደሰተ ቃላቱን በስርዓቱ መደርደር ተስኖት በሱ በኩል ምን ማድረግ እንዳለበት ደጋግሞ ሲጠይቀው ኢትዮጵያ ካለው ጤና ሚኒስቴር ጋር እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር አስፈላጊውን ነገር እንዲያጠናቅቅ ስለነገረው የስራ ድርሻው መቀበሉንና እንደኮራበት እየነገረው ተለያዩ።

ብሩክ ቀኑን በደስታ ነበር ያሳለፈው ለአመታት ሲመኘውና ሲያልመው የነበረው በመንደሩ ሆስፒታል ተገንብቶ ማየት እውን ሊሆን ጥቂት ስራዎች ይቀራሉ ነገር ግን ብሩክ ያደገባት መንደር አዋቂ አቶ መኮንን ችግር እንዳይፈጥሩ ፈርቷል።

****

ጥላሁን ከብሩክ የተላከለት የመንደሩ ሰዎች እንዲሞሉት የሚፈለገው ቅፅ

ደርሶታል አሁን ጥላሁን ግራ የገባው እንዴት ብሎ የመንደሩን ሰዎች አግኝቶ ቅፁን እንደሚያስሞላ ነው። በቀጥታ ወደ አቶ ግርማቸው በመሄድ ስለ ጉዳዩ ካጫወቱት ጉዳዩ እንደማይሰምር ስለተረዳ ሌላ መንገድ መፈለጉን ተያያዘው ድንገት ግን ጥላሁን አንድ ሀሳብ ስለመጣለት የቅፁን አንድ ገፅ በመያዝ ከአዲስ አበባ ወደ ከተማው ግብርና ቢሮ ገሰገሰ።

ምንም እንኳን ጥላሁን መንገዱ ቢያደክመውም ደከመኝ በማለት የሚያጠፋው ጊዜ እንዳይኖር ስለፈለገ በቀጥታ ወደ ግብርናው ቢሮ ገሰገሰ ። እንደ ድንገት ሆኖ የከተማው የግብርና ቢሮ ሀላፊ ከስብሰባ ሲወጡ ተገናኙ። ጥላሁንም ለብርቱ እና አስቸኳይ ጉዳይ እንደፈለገው በመናገር ወደ ግብርናው ቢሮ ሀላፊ ቢሮ ገብተው ማውራት ጀመሩ።

ጥላሁንም ወቅቱ የክረምት ወቅት እየገባ እንደሆነ ፤ በዙርያው ያሉ መንደሮች ከከተማው ቢሮ የዘር ድጋፍ እንደሚደረግላቸው እና ይህ ቅፅ ከየመንደሩ የሚመጡት አባወራዎች እንዲሞሉት ቢደረግ ልፋትንና እንግልትን እንደሚቀንስ ቅፁም ተሞልቶ ሲጠናቀቅ ለመንደሩ ሆስፒታል ለሚገነቡት አካላት ጠቃሚ መረጃ እንደሚሆንገለፃ አደረገ።

የቢሮ ሀላፊውም ሀሳቡን እንደተቀበሉትና ለአስተባባሪዎች ቅፁ እንዲያስተላልፍ ነግሮት ሌላ ቀጠሮ እንዳለው ተናግሮ ተለያዩ ጥላሁንም የሚሞሉት ቅፆች እዛው ከተማ በሚገኝ ማባዣ ቤት በብዛት አባዝቶ ለተባሉት አስተባባሪዎች እንዴት እንደሚሞላ አሳይቶ እና አደራ ሰጥቶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

****

ጥላሁን እንዴት አድርጎ አደራ የተባለው ቅፅ እንዳስሞላ ብሩክን

አስገርሞታል ። ብሩክ ከትምህርት ጊዜው ፋታ እንዳገኘ ጥላሁን አስሞልቶ የላከለት ወረቀቶቹን ከፖስታ ቤት ተቀብሎ ወደ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ቅፁን ገቢ አደረገ። ከድርጅቱም " ቅፁን ካየን በኋላ እንጠራሀለን " የሚል ምላሽ ስለተሰጠው ቀጠሮ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ቤቱ ደርሶም በድካም የዛለውን ሰውነቱን ለመታጠብ ወደ ሻወር ቤት ልብሶቹን በሸርጥ መልክ በወገቡ ባሰራት ነጭ ፎጣ ቀይሮ ወደ ሻወር ቤት በመሄድ ባኞ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የፊት መስታወት እያየ ራሱን አስተዋለ።

የውጭ ሀገር ቆይታው ፊቱን ያፈካለት ብሩክ በፊት ከነበረው መልክ ውበቱ እየጨመረ ነው ። ፊቱ ላይ አንዳንድ ጠባሳዎች ቢኖሩበትም ችፍችፍ ብሎ ያደገው ጥቁር ፂሙ ሸፍኗቸዋል የፂሙ አቆራረጥም ለፊቱ ገፅታ ልዩ ውበትን አጎናፅፈውታል አፍንጫው አሁንም ቢሆን ሰልካካ ነው ፣ ከእንቅልፍ እጦት ምክንያት ደጋግሞ የሚደፈርሰው አይኑ መነፅር ካልተጠቀምክ አላሳይህም ያለው ይመስላል ፣ ፀጉሩም ቢሆን ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው አሳጥሮት ተቆርጦታል ።

ብሩክ በቀኝ እጁ አገጩን በመያዝ ወደ ግራና ቀኝ እያዞረ የፊቱን ገፅታ በመመልከት " ብሩክ አምሮብሀል " እያለ ሲያወራ ከመታጠቢያ ቤቱ ጎን በተሰራው መኝታ ቤት ያስቀመጣት ስልክ ስለጠራች ሊያነሳት እግሩን ለማንቀሳቀስ ቢሞክር እንቢ አለው በተለይ የቀኝ እግሩ ጉልበት ክፉኛ ስለጠዘጠዘውና ህመሙን መቋቋም ስላልቻለ ባለበት ተዘርግፎ ወደቀ።

በሁለት እጆቹ ጉልበቱን በመያዝ ትንፋሹን ቁርጥ ቁርጥ እያደረገ አቃሰተ በመንፏቀቅም ወደ መኝታው ቤት በመሄድ ህመሙን ለማስታገስ በማሰብ ከመሳቢያው ውስጥ ፋሻ በማውጣት ስቃዩን እየቻለው በማጣበቅ በጉልበቱ ዙርያ ጠምጥሞ አሰረው ።

ህመሙ ጋብ ቢልለትም አዲስ አበባ ከአንድ አመት በፊት ያገኛቸው ዶክተር የተናገሩት በአዕምሮው ላይ ተከሰቱበት"ጉልበትህ ስንጥቅ አለው .... ቶሎ ካልታከምክ እግርህን ልታጣው ትችላለህ " የሚሉት ቃላቶች ደጋግመው ወደ አዕምሮው ተመላለሱበት ።

ብሩክ ምንም እንኳ ያሰረው ፋሻ ህመሙን ቢያስታግስለትም በየወቅቱ የሚወሰድ ማስታገሻን በመውሰድ የጀመረውን ትምህርት እና የሆስፒታሉን ጉዳይ ከዳር ማድረስ እንዳለበት ራሱን እያሳመነ የህመሙን ጉዳይ ለማንም ሳይናገር በሚስጥር ለመያዝ አስቦ ልብሶቹን በመለባበስ መድሀኒት ፍለጋ ወደ ፋርማሲ እያነከሰ አቀና።

ከፋርማሲም ለጥቂት ጊዜ የሚሆን የማስታገሻ መድሀኒት ከገዛ በኋላ የተወሰነ እረፍት ለማድረግ በማሰብ ወደ አልጋው እየሄደ ቅድም ደውሎ ያልመለሰለት ማን እንደሆነ ለማየት ሰልኩን ከፈተው ። ሄኖን ነበረች ከአንዴም ሁለቴ ደውላ ስላልተነሳላት መልእክትም አስቀምጣለት ነበር ። በቅርቡ የጀመረችውን ትምህርት እንደምትጨርስና ተመርቃ ወደ ኢትዮጵያ እንደምትሄድ በመንገር መልዕክት ትታለት ነበር ።

ብሩክም መልእክቱን እንዳነበበው በአልጋው ላይ ጋደም በማለት ወደ ሄኖን ደወለ ።

" ሄሎ የኔ ፍቅር " በማለት ሄኖን ቀድማ ተናገረች

" ሀይ ሄኒ ሰላም ነው ? " አለ በደከመ ድምፅ

" ምነው ብሩኬ ሰላም አደለህም ? ድምፅህ ልክ አይደለም" በማለት እየተጠራጠረች ጠየቀችው

ብሩክም እንዳመመው ባለመናገር ቀኑን ሙሉ ሲደክም እንደዋለ እና የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ጋር በመሄድ ወረቀት እንዳስገባና ሰልክ ያላነሳላት ሻወር

እየወሰደ እንደነበር ነገራት።

ሄኖንም እረፍት አድርጎ እንዲደውልላትንና ስለ ተማረችው ትምህርት እና የምርቃት ስነስርዓቱ ምን እንደሚመስል ለመንገር እንዳሰበች ነግራው ። እንደምትወደው ደግሞም ልታየው እንደናፈቀች እየነገረችው ተሰነባብተው ተለያዩ።

****

የሀገሬው አዋቂ አቶ መኮንን በመንደራቸው እየሆነ ያለው ነገር ሎሌዎቻቸውን በማሰማራት እንዲቃኙ ቢያደርጉም የረባ መረጃ ይዘውላቸው ስላልመጡ አቶ መኮንን በራሳቸው መንገድ በመሄድ ሰሞኑን የተሞላው ቅፅ ምንነትና በሰፈራቸው ከእሳቸው ተደብቆ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማየት በማሰብ ወደ ከተማው አስተዳዳሪ አቶ ለማ ጋር መልዕክተኛ ልከው በአስቸኳይ እንዲመጡ አስደረገ።

ሁለቱም ተገናኝተው ሰላምታ ሲሰጣጡ በሁለቱም ከዚህ በፊት ያደርጉት እንደነበረው በሀይለኛ ሳቅ እና ግርግር ሳይሆን ሁለቱም በፍርሀት ተውጠው ነበር።

አቶ መኮንንም የከተማ አስተዳዳሪው የፊት ገፅታ እያየ " ምን ሆነሀል ? ፊትህ የተረበሸ ሰው ፊት ይመስላል " በማለት በጎርናናው ድምፁ ጠየቀው

አቶ ለማም ቀጥሎ " የራስህን እየው እንጂ ፈርተሀል እኮ " በማለት መለሰለት

አቶ መኮንንም በመንደራቸው እንግዳ ነገር እንዳለና ማወቅ እንዳልቻለ ደግሞም ወደ ውጭ ሀገር የሄደው ብሩክ አንዳች ነገር ሊያደርግ እንደፈራ

ነገረው።

አስተዳዳሪው ለማም በፍርድ ቤት የተያዘ የሙስና ወንጀል እንዳለበትና ከዚህ በተጨማሪ ሌላ ወንጀል ለመስራት እንደማይፈልግ ስለመለሰለት አቶ መኮንን በንዴት

"ስማ እዚህ እንደ ጠንቋይ ስቀልብህ ኖሬ በቸገረኝ ሰዓት ላትረዳኝ ነው ? እኔ መኮንን ይሄ ሁሉ የመንደሩ ህዝብ የሚከተለኝ የተከበርኩ ሰው ነኝ ይልቅ ከኔ ጋር ሆነህ ምን እየተፈጠረ እንዳለ እናጣራ የሚመጣብን ነገርም አብረን እንወጣው።" በማለት ሲያንባርቁበት አቶ ለማ ከመኮንን ንዴት በመካፈል እየተናደደ

" እንደጠንቋይ የቀለብከኝ እኮ በራስህ ገንዘብ አይደለም ታሪክ አጣመህና ትክክለኛውን ባህላቸውን ሸረህ በትብታብህ ተብትበህ ግብር በምታስገብራቸው ህዝቦች ነው ደግሞ ካሁን በኋላ የመጣው ይመጣል እንጂ ምንም አይነት ነገር ካንተ ጋር መስራት አልፈልግም ፤ የመንደሩ ሰዎችንም ለመካስ ከየዋሁ ብሩክ ጋር አይደለም ከሰይጣንም ጋር እተባበራለው። ካሁን በኋላ ከኔ ጋር ያበቃልሀል እሺ !" እያለ እጁን እያወራጨና በአቶ መኮንን እያፈጠጠ ተናግሮት ወደ መጣበት ተመለሰ።

አቶ መኮንን በንዴት መሬቱን ያለ ስስት እየረገጡ ወደ ቤቱ ገብቶ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት እየተሰማው በግድግዳው የተሰቀለው ረዥም ጦር በማንሳት በእጁ ጥብቅ አድርጎ ያዘው።

****

ብሩክ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተሰጠው የቀጠሮ ቀን ስለደረሰ ወደ ነህምያ በመደወል ለመሄድ ተነሳ።

ብሩክና የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መስራች ካለ ወትሮአቸው ብዙ ንግግር አደረጉ በጠዋት የጀመሩት ንግግርም ረዝሞ እና ተለጥጦ ማለቂያው ምሽት የስራ መውጫ ሰዓት ላይ እንዲሆን ተገደዱ።

በቆይታቸው ለመንደሩ ዘመናዊ ሆስፒታል እንደሚያስፈልግ ብሩክ ባስገባላቸው ቅፅ እንደተረዱና ተጨማሪ ስለ መንደሩ አኗኗር ባህል ፣ ስርዓት እና ሌሎች ብዙ ነገሮች ተነጋግረው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሆስፒታሉ ግንባታ እንዲጀመር እንዲያደርጉና ለግንባታው የተወሰነ የገንዘብ መጠን እንደሚለቁ ተነጋግረው ነበር።

ከስብሰባው በኋላ ነህምያ ብሩክን ወደ ቤቱ በመኪናው እያደረሰው "እውነቴን ነው ምልህ እዚህ ከተቀጠርኩ ሰባት አመት ሆኖኛል ግን እንዳንተ አይነት መልካም ሀሳብ አምጥቶ የተሳካለት ሰው አላየሁም ኮንግራ ብሩክ ሀገርህ ካንተ የምትፈልገውን ስለሰጠሀት ምስጋና ይገባሀል ።" አለው

ብሩክም የሆስፒታል ስራው እውን እየሆነ እንደመጣ ተመልክቶ "አመሰግናለው ! ግን የቀረ ስራ ሳይኖር አይቀርም ?"

"ምንድነው እሱ ?"

"አቶ መኮንን " በማለት ሲመልስለት ነህምያ ከዚህ በፊት በአቶ መኮንን ሴራ የተቀለበሰው የልማት ስራ ብሩክ ስላጫወተው ለማሰብ መኪናውን ወደ መንገዱ ዳር አውጥቶ አቆመው።

"ታድያ ምን ማድረግ ታስባለህ ?" በማለት ነህምያ ግራ በመጋባት ጠየቀ

ብሩክም ትከሻውን ወደ ላይ ሰብቆ "አላውቅም ብቻ በንግግር ላሳምነው ምችል አይመስለኝም "

ነህምያም ትንሽ በማሰብ "ለምን ወጥመድ አናዘጋጅለትም ?" በማለት ሲጠይቅ ለክፋት እሩቅ የሆነው ብሩክ በፍጥነት "ምን አይነት ወጥመድ ?" በማለት ሲጠይቅ ነህምያ መኪናውን እያስነሳ "የሱን ነገር ለኔ ተወው ድል ያለ ድግስ አዘጋጅለታለው ። ይልቅ መቼ ነው ወደ ኢትዮጵያ የምትመለሰው ?"

"ፈተናውን ሳምንት እጨርሳለው ከዛም አስፈላጊ ሰራዎችን አጠናቅቄ በሁለት ሳምንት ውስጥ እመለሳለው "

"መልካም ከመሄድህ በፊት የጓደኛህ ...ኦው ይቅርታ ስሙን ረሳሁት "

"ጥላሁን?"

"አዎ ጥላሁን የሱን ስልክ ትተውልኛለህ እና ወደ ኢትዮጵያ የምልክህ መልዕክት አለ ታገኘኛለህ "በማለት ብሩክን ሊሸኝ መኪናውን አበረረ።

****

ሄኖን ተመርቃ ሀገርቤት ከገባች ከሁለት ወር በኋላ ነው ጥላሁን የህግ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት ተመርቆ ወደ ፍርድ ቤት ሰራ የገባው።

ጥላሁን እንደ አዲስ ሰራተኝነቱ በትጋት ለመስራት የተለያዩ የክስ መዝገቦችን በማየት ለዋና ዳኛ አጋዥ ሆኖ እየሰራ የነበረ ቢሆንም ዛሬ ግን የተሰጠውን ስራ በአግባቡ ስለሰራ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን የዳኝነት ስራ ለመስራት በዙፋኑ ተሰይሟል።

በቅድሚያ ያየው መዝገብ የሰርቆት ስለነበር በተማረውና ህጉ በሚያዘው

መሰረት የፍርድ ሂደቱን አከናውኖ የለበሳትን ጥቁር ካባ አውልቆ ወደ መውጫው ሲያመራ "ጥሌ " በማለት ቀጭን የሴት ድምፅ ጠራው

ወደ ተጠራበት አቅጣጫ ሲዞርም ትዕግስት እየፈነደቀች በሩጫ መጥታ አቀፈችው ::

ጥላሁንም "እዚህ ምን ትሰሪያለሽ ?" በማለት ሲጠይቃት

" ባክህ የሆነ ሰው እጄ ላይ አርፎ ተከሰሼ መጥቼ ነው " በማለት ከት ብላ ሳቀች

" መቀለዱ ነው ?" እያለ ወደ መውጫው አመራ ትዕግስትም እየተከተለች "ባክህ አንተን ፈልጌ ነው የሆንክ ሞዛዛ " እያለች ጀርባውን በቀኝ እጇ ለኮፍ አደረገችው

ጥላሁንም "በሰላም ?"

"አዎን በሰላም ምነው ጊዜ የለህም ? አንተን ማውራት ፈልጌ ነው "

"ኧረ አለኝ ችግር የለውም"

"እሺ በጣም ስለራበኝ ምሳ እየበላን እናውራ ?" ስትለው በእሺታ አንገቱን ነቅንቆ አቅራቢያቸው ወደሚገኝ ሆቴል እየተጨዋወቱ ሲያቀኑ የጥላሁን ስልክ ጠራ

"ሀሎ "

"ሀሎ ጥላሁን ነህ ?"

"አዎን ማን ልበል ?"

"ነህምያ እባላለው የብሩክ ጓደኛ ነኝ ስለ አንድ ጉዳይ በአስቸኳይ ፈልጌህ ነበር "

"ስለምን ጉዳይ ?"

"ስለ አቶ መኮንን "

ጥላሁንም ከትንሽ ዝምታ በኋላ "እሺ አሁን ልትነግረኝ ትችላለህ ?"

"ተረጋግተህና ሀሳብህን ሰብስበህ ምልክት እንድታደርግልኝ እፈልጋለው "

"እሺ ትንሽ ቆይቼ እደውላለው ደህና ሁን "

"ደህና ሁን"

****

ብሩክ የአመቱን ትምህርት አጠናቆና አስፈላጊ ማስረጃዎቹን አሰናድቶ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞ ሊጀምር ከአቶ ነህምያ የሚሰጠውን መልእክት ለመቀበል ወደ ኢንባሲው አመራ።

"ሰላም ድንቁ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ "በማለት እጃን ዘትግቶ ተቀበለው ። ወደ ቢሮ ከገቡ በኋላም ነህምያ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጉትን ስራዎች መጨረሱን እየነገረው ከጠረጴዛው ደብዳቤ በማውጣት ድምፁን ዝቅ እያደረገ "ይሄንን ኢትዮጵያ ስትሄድ ለአቶ መኮንን ስጥልኝ "በማለት ደብዳቤውን አቀበሉት።

ብሩክም በእሺታ አንገቱን ነቅንቆ ደብዳቤውን ተቀበለው ነህምያም ወደ ኢትዮጵያ ከመሄዱ በፊት የእራት ግብዣ እንዳዘጋጀለትና ከሁለት ሰዓት በኋላ ቤቱ መጥቶ እንደሚወስደው ነግሮት ተሰነባብተው ተለያዩ።

ለምን ነህምያ ለአቶ መኮንን ደብዳቤ እንደላከለት ብሩክ አልገባውም በጥያቄም መብሰልሰል ያዘ ምናልባት ወረቀቱ ማስፈራሪያ ይዞ ይሆን

ወይስ ብዙ የገብዘብ መጠን እንደሚሰጠው እያባበለው ነው በማለት በጥያቄ ተወጥሮ ደብዳቤውን ማንበብ ቢፈልግም ልቡ መድፈር ስላቃተው ሀሳቡን ከአዕምሮው አወጣው።

ነህምያ እመጣለው ባለው ሰዓት ደቂቃ ሳያዛንፍ መኪናውን ይዞ መጥቶ ብሩክን ይዞ ወደ መኖርያ ቤቱ ከነፈ።

መኖርያ ቤቱ በአጫጭር ውብ አጥሮች የታጠረ የሌባ ስጋት የሌላባት በሚመስል ግቢ ውስጥ ነው ያረፈው ባለ ሁለት ፎቅ መኖርያ ቤት ሲሆን በቀኝ በኩል መኪና ማቆምያ ሰፊ ቦታ አለ እንዲሁም ከግቢው ወደ ቤት መግቢያ መንገድ ዳርና ዳር የተተከሉት ዛፎች ላይ ሁለት ካሜራዎች ተደቅነዋል።

ብሩክም እነዚህን በአግራሞት እያየ ነህምያን ተከትሎ ወደ መኖርያ ቤቱ በር ደርሶ ቆመ ነህምያም ሁለት ጊዜ የቤቱን መጥሪያ ከተጫነው በኋላ አንዲት ፈረንጅ እጇን በፎጣ እያደራረቀች በሩን በመክፈት የእንኳን ደህና መጣችሁ ሰላምታ አቀረበችላቸው።

ነህምያም ሰላምታውን ተቀብሎ ባለቤቱ እንደሆነች ነግሮት ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ ወደ ውስጥ ሲገቡ ሁለት ትናንሽ እህተማማቾች ከውስጥ እየሮጡ "dady!!" በማለት ዘለው በነህምያ ላይ ተጠመጠሙ ብሩክም በቅፅበት ህሊና እና ማርያማዊት ትዝ ብለውት እንደናፈቃቸው ለማስተዋል ቻለ።

ወደ ምግብ ቤቱ ክፍል ገብተው ምግባቸውን ከበሉ በኋላ ብሩክ ስለተደረገለት ግብዣ ነህምያንና ሚስቱን እያመሰገነ ከቤቱ ሲወጣ ነህምያም ሊሸኘው ተከተለው።

በመንገዳቸውም ብሩክ ስለ ቤተሰቡ ስለጠየቀው ሚስቱን ያገኛት

ከሰድስት አመት በፊት ወደ ሚሰራበት ኤንባሲ ለስራ መጥታ እንደተዋወቁና ግንኙነታቸው አድጎ ትዳር ለመመስረት እንደታደሉ እየነገረው ወደ ቤቱ ደረሱ።

****

ብሩክ አዲስ አበባ እንደገባ ጥላሁንና ባለውለታው የአባቱ ጓደኛ አዛውንትን ለመጠየቅና አንዳንድ የግንባታ አማካሪዎችንና መሀንዲሶችን ለማናገር ለአንድ ሳምንት እዛው አዲስ አበባ ቆየ በቆይታውም ለመጓጓዣነት እንዲያገለግለው ውጭ በትምህርት በነበረ ጊዜ ካጠራቀማት ትንሽ ገንዘብ ቆንጥሮ ነጭ ውብ መኪና ገዛ።

የፍቅር አጋሩ ሄኖንም አዲስ አበባ መምጣቱን ስትሰማ ናፍቆት አላስቀምጥሽ ስላላት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ አምሮበት የፊቱም ቆዳ ላይ የነበሩት ጠባሳዎች በግሩም አቆራረጥ የተቆረጡት ፂሞቹ ሸፍነውለት መልአክ መስሎ ስላገኘችው ደስታዋ ወደር አጣ።

ብሩክ ከነህምያ የተቀበለውን ደብዳቤ በቀጥታ ለአቶ መኮንን በመሄድ መስጠት ስለፈራ ለጥላሁን ደብዳቤውን ወስዶ እንዲሰጠው ለመነው ጥላሁንም ሳያቅማማ በእሺታ ደብዳቤውን ተቀብሎ እንደሚያደርስለት ቃል ገብቶለት ተለያዩ።

****

አቶ መኮንን ለረጅም ጊዜ በመንደራቸው ምን እየተፈጠረ እንዳለ

ስላልገባቸው ከአንዴም ሁለቴ የመንደሩን ሰው በዞራ ዋርካ ስር ሰብስበው ከአቶ መኮንን የተደበቀ ነገር ካለ ዞራ እንደሚቆጣ እና እርግማን እንደሚያወርድ ነግሮኛል በማለት የመንደሩን ነዋሪዎችን ለማስፈራራት ቢሞክሩም ነገርየው ከመንደሩ ሰዎችም የተደበቀ ስለነበር ማንም ምንም ማለት ባለመቻሉ አቶ መኮንን ሎሌዎቻቸውን አባርረው በብስጭት ውስጥ ናቸው።

ሁል ጊዜም ወደ ብሩክ አጎት በመሄድ "ያ ከይሲ ልጅህ ቁጣ ሊያመጣብህ ነው ተዘጋጅተሀል?" በማለት ይወተውቱታል።

ዛሬም እንደለመዱት ወደ ብሩክ አጎት በመሄድ የጠንቋይ ድንፋታቸውን ሊደነፉ ሲዘገጃጁ ከቤታቸው ደጅ ቆሞ የሚጣራ ድምፅ ሰሙ

"አለቃ ... አለቃ .... አለቃ " የሚል የጎረምሳ ድምፅ ተጣራ

አቶ መኮንንም ከቆዳ የተሰራው ድርብ ልብሳቸውን ለብሰው የአለቃነት መንፈሱን ላለማሳጣት በዝግታ ወደ በሩ ተጠግተው "ማነው ?" በማለት ለጎረምሳው ጠየቁት

ጎረምሳውም " አለቃ ከውጭ ሀገር የተላከሎት መልዕክት አለ " በማለት ሲመልስ አቶ መኮንን እየተቻኮሉ ጎረምሳው ወዳለበት ደጅ ወጥተው

"ምንድነው ?" አሉት

"ደብዳቤ ነው ከውጪ ተልኮልዎት ነው " በማለት ደብዳቤውን ሰጥቶአቸው ለአክብሮት ከወገቡ ጎንበስ ብሎ በፍጥነት ከአካባቢው ዞር አለ

አቶ መኮንንም ደብዳቤውን ሲከፍቱ ጥቂት የውጭ ሀገር ገንዘቦች እና አንድ ወረቀት ስላገኙ እየተደሰቱ ገንዘቡን በቀኝ እጃቸው ጠቅልለው

በመያዝ ደብዳቤውን ከፈቱ

"ጤና ይስጥልኝ አቶ መኮንን ነህምያ እባላለው በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ኢንባሲ ሰራተኛ ነኝ ። የምታመልከው አምላክ አገልጋይ እንደሆንክ አውቃለው ለሱም ገለታ ይድረስህ በማለት ይህንን ጥቂት ገንዘብ ልኬልሀለው። ሰሞኑን አንዳንድ እንቅስቃሴዎች አንተ ባለህበትና በተከበርክበት አካባቢ እየተደረጉ መሆኑን አውቄአለው አንትም ምን እየተፈጠረ እንዳለ በግልፅ የምታውቀው ነገር የለም ስለሆነም ነገሩን ልነግርህ ፈለኩ ነገሩን በደብዳቤ ካሰፈርኩት መልዕክተኛ ወይም ብሩክ ሊያየው ስለሚችል ነገሩን ከመፃፍ ተቆጥቤ በሌላ መልዕክተኛ የላኩልህ ጥቂት ገንዘብና ምን እየተሰራ እንዳለ የሚያሳየውን ወረቀት ተቀበል ይልቅ ጊዜ ሳታጠፋ ወደ ከተማ ሄደህ ...." እያለ የሆቴሉን አቅጣጫ ከነገረው እና የተላከለት እቃ የት እንደተቀመጠ የሚናገረውን ደብዳቤ እንዳነበበ ጫማውንና ካባውን ደርቦ በአግባቡ የተቀለበችው ፈረሱ ላይ ወጥቶ ወደ ከተማ ሸምጥ ጋለበ።

ለአቶ መኮንን ደብዳቤውን ያደረሰው ጎረምሳ ወደ ጥላሁን ደውሎ ደብዳቤውን ማድረሱ አሳወቀ።

አቶ መኮንን የተባለው ቦታ ላይ ደረሰ ቦታው የከተማው እንብርት ላይ የሚገኝ የእንግዳ ማረፊያ ሲሆን በአድራሻው መሰረት በሩ ለእሳቸው ሲባል እንደማይዘጋ ወደተነገራቸው ዶርም ቁጥር ሰባት ገስግሰው በሩን በቀስታ በመክፈት ማንም አለመኖሩ አንገታቸውን አስገብተው ካዩ በኋላ ወደ ውስጥ ገቡ።

አቶ መኮንን ለገንዘብ ያላቸው ፍቅር እና በመንደራቸው ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማወቅ ካደረባቸው ጉጉት የተነሳ ደብዳቤው እንደሚጠቁመው ከማረፍያ ቤቱ አልጋ ስር የተቀመጠ በጥቁር ፌስታል የተጠቀለለውን

ካርቶን አንስተው በመሬቱ በመንበርከክ ፌስታሉን በችኮላ በጣጥሰው ካርቶኑን ሲከፍቱ ካርቶኑን ሙሉ የውጭ ሀገር ገንዘብ እና ከጎን በኩል የተጣጠፈ ወረቀት አገኙ ።

በገንዘቡ ልባቸው የቀለጠው አቶ መኮንን በፍጥነት ወረቀቱ የሚነግራቸውን ምስጢር ከፍተው ሲያነቡት "አዝናለው መኮንን ከዚህ በላይ በህዝቤ አትጫወት ይበቃሀል " የሚል አጭር ፅሁፍ እንዳነበቡ ሶስት ፖሊሶች በሩን በርግደው በመግባት መሳሪያቸውን በአቶ መኮንን ላይ አነጣጠሩ።

ነገሩ ወጥመድ ይሆናል ብሎ ያልጠረጠረው አቶ መኮንንም በድንጋጤ ባለበት በላብ ተዘፈቀ ምን እንደሚል ግራ ስለገባውም እየተንተባተበ "እኔ አይደለሁም ..... ደብዳቤው ነው እውነት እውነት "እያሉ ቢያወሩም ፖሊሶች እጃቸውን በሰንሰለት አስረው እያካለቡ ከቤቱ አወጧቸው።

ከቤቱ እንደወጡም ጥላሁን በረንዳ ላይ በመቆም በኩራት ፈገግ እያለ ሲመለከተው ሁለቱም አይን ለአይን ተገጣጠሙ። አቶ መኮንንም "እሱ ነው ... እሱነው ያጭበረበረኝ ..... እሱነው ይሄን ያደረገው "እያለ እየተወራጨ ሲያስቸግር ጥላሁን ወደ አቶ መኮንን ተጠግቶ " የሰው ቤት ንብረት ለመዝረፍ መሞከርህ ሳያንስ የገንዘቡ ባለቤት ላይ አፍህን ትከፍታለህ ? ይልቅ መልካም እረፍት ይሁንልህ !" በማለት በስላቅ እየሳቀ ሲያናግረው አቶ ግርማቸው በንዴት ምራቃቸውን ፊቱ ላይ በመትፋት ከፖሊስ ግብ ግብ ሲገጥሙ ፓሊሶች ለሶስት አቶ ግርማቸውን በመያዝ ከቤቱ አስወጥተው በመኪና ጀርባ ላይ ከሰቀሏቸው በኋላ ይዘዋቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተፈተለኩ።

ጥላሁንም ከኪሱ መሀረቡን አውጥቶ ከአቶ መኮንን የተለገሰው ምራቅ እየጠረገ ወደ ቤቱ በመግባት በድንጋጤ እዛው የተዋቸውን የነህምያ

ደብዳቤ እና ካርቶኑ ላይ ያስቀመጠለት ደብዳቤን በክብሪት ዶግ አመድ አደረጋቸው።

****

"ሄሎ ነህምያ "

"አቤት ጥላሁን "

"ስራችንን በአግባቡ ሰርተነዋል ዛሬ ወደ ማረፊያ ቤት ወስደውታል ፤ የተለያዩ ማስረጃዎችን አጠናክሬ ክሱን አከብድበታለው "

"ብራቮ ጥላሁን ! ጓደኛህ አሁን ያለ ምንም ጭንቀት ማህበረሰቡን ያገለግላል "

"አዎ እኛም ከጎኑ ነን "

"በትክክል "

"መልካም ቀን አቶ ነህምያ "

"እሺ ላንተም መልካም ቀን"

****

ብሩክ የአዲስ አበባ ቆይታውን ከሄኖን ጋር በሚገባ እየተዝናኑ አሳልፏል በመቀጠል ወደ አክስቱ እና እህቶቹ እንዲሁም ወይዘሮ የትናየትን ለመጠየቅ ከሄኖን ጋር አስፈላጊውን ነገር ካደረጉ እና ለመሀንዲሶች የጊዜ ቀጠሮ ከሰጡ በኋላ ብሩክና ሄኖን በብሩክ አዲሲቷ መኪና ወደ ከተማ

በረሩ።

የብሩክ አክስት መልኳ ተመልሶ ወጣት መስላለች ትናንሾቹ እህቶቹ በጣም አድገዋል የተከራዩትም ቤት ብቻ ሳይሆን የወይዘሮ የትናየት ዋናው ቤት ጭምር ታድሶ ገፅታው ተቀይሮ ውብ ቤት ሆኗል አብዛኞቹ የወይዘሮ የትናየት ቤት ተከራዮች ቤቱን ለቀዋል ።

ወይዘሮ የትናየትም ብሩክን ሊያየዩ ናፍቀው ስለነበር ከመጣ ጀምሮ በወሬ ጠምደው ይዘውታል ሄኖንም ብትሆን ከብሩክ ትናንሽ እህቶቹ ጋር በጨዋታ ልቧ ጥፍት ብሏል።

የብሩክ ስልክ ስለጠራ ወይዘሮ የትናየት ጫወታቸውን ጋብ እንዲያደርጉ ለልጆቹ እና ለሄኖን ምልክት ሰጧቸው

"ሄሎ ጥሌ "

"አቡሽ ሰላም ነህ ?" አለው በሚቆራረጥ ትንፋሽ

ብሩክም በመደናገጥ "አዎን ሰላም ነኝ ምንድነው ?" አለው ግራ በመጋባት

"ይኸውልህ ባለፈው ከሁለት ቀን በፊት አቶ መኮንን ታስሮ ነበር ዛሬ ግን ከእስር ቤት ወደ ፍርድ ቤት ሲወስዱት ፖሊሶቹን ደብድቦ መሳሪያ ቀምቶ አምልጧል፤ እስር ቤት ውስጥ 'እነዚህ ከይሲዎች እገላቸዋለው' እያለ ሲዝት እንደነበርም ሌሎች እስረኞች ቃላቸውን ሰጥተዋል ራስህን ጠብቅ ሰውየው ታጥቋል በጣም ተጠንቀቅ "እያለ በችኮላ ማስጠንቀቂያውን ሰጠው

ብሩክም "እና ከኔ ጋር ምን ያገናኘዋል ? ለምንድነው የሚገድለኝ " በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያወራ በቤቱ ውስጥ የነበሩት የብሩክ አክስት ፣ ወይዘሮ የትናየት ፣ ሄኖንና እህቶቹ አፍጥጠው ተመለከቱት

ጥላሁንም ባለፈው ከነህምያ ጋር ተመካክረው ጥላሁን ወጥመድ ላይ አስገብተው እንዳሳሰሩትና አቶ መኮንን ይህ ሁሉ ሴራ የጠነሰሰው ብሩክ ነው ብሎ እንደሚያምንና ሁለታቸውንም መግደል እንደሚፈልግ በዝርዝር አስረድቶትና ራሱን እንዲጠብቅ ነግሮት ተለያዩ።

ስልኩን ከዘጋው በኋላ በቤቱ የታደሙት በአንድ ድምፅ ምን እንደተፈጠረ አዋክበው ጠየቁት ብሩክም ሁሉም ሰላም እንደሆነና ለጥቂት ጊዜም ከቤቱ ማንም እንዳይወጣ አስፈላጊ ከሆነም ብሩክ ሁሉንም ነገር እንደሚያመጣ አግባብቶ ከተናገረ በኋላ ለብቻው ስለ አቶ መኮንን ማሰብ ጀመረ ።

ይሄ ጊዜ ቁርጥ ጊዜ ነው ወይ የመኮንን የተጣመመ ታሪክና ባህል የሚቀጥልበት ወይ ደግሞ መንደሪቷ እንደሌሎች የሀገሪቱ ክፍል የምትበለፅግበት ብሩክ ይህንን እያሰበና ለማህበረሰቡ መክፈል ያለበት ዋጋ ከፍሎ ከዚያ ጨቋኝ አስተሳሰብ መገላገል እንዳለበት እያሰበ እንቅልፍ አሸልቦ ወሰደው።

****

ቀናት እየተቆጠሩ ሲሄዱ ብሩክ ምንም አይነት ጥቃት ወይም ጉዳት ከአቶ መኮንን ስላልደረሰበት አጉል ጥርጣሬ ጠርጥሮ እንጂ እውነትም አቶ መኮንን ሊገሉት እንዳላሰቡ እየገመተ ከቤት አዘውትሮ መውጣት ጀምሯል በተደጋጋሚም አዲስ አበባ ያለው ጥላሁን የብሩክ በተደጋጋሚ ውጭ መውጣት ከሄኖን ስለሰማ ለኣቶ መኮንን ተጋላጭ እንዳይሆን በመፍራት በተደጋጋሚ ቢያስጠነቅቀውም ብሩክ ማስጠንቀቂያውን ከመስማት ተቆጥቦ እንቅስቃሴውን ቀጥሏል።

ከከተማው አስተዳዳሪ ለማ ጋርም ጥብቅ ወዳጆች በመሆን አቶ ለማ የብሩክ ቀንደኛ ወዳጅ ሆኗል ። ወደ ቢሮው በመሄድም በተወለደበት መንደር ሊያሰራ ስላለው ሆስፒታል በተደጋጋሚ አጫውቶት መንግስት መሬት በነፃ እንዲቀርብለት እንዲያመቻች ስለጠየቀው ምላሹን ለማግኘት አቶ ለማ ለብሩክ ቀጠሮ ሰጥተውታል።

ብሩክ የሚሰራው ስራ መልካም እየሆነለት እንደሆነና ከከተማው አስተዳዳሪ ለመሬት ጉዳይ ቀጠሮ መያዛቸው ለጥላሁን ስለነገረው ጥላሁን ወደ ከብሩክ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ከአዲስ አበባ መጣ።

በቀጠሮው ቀንም ብሩክና ጥላሁን ተያይዘው ወደ ከተማው አስተዳዳሪ በመሄድ ምላሽ ጠየቁ የከተማው አስተዳደርም በመንደሩ ብዙ ሰፊ ሜዳዎች እንዳሉና በነሱ ምርጫ መሬት እንደሚሰጣቸው ተናግሮ ተለያዩ።

ጥላሁን አንዳች አይነት ጥርጣሬ በውስጡ ስላደረ ለብሩክ ጥርጣሬውን አካፈለው

"አቡሽ ?"

"ወይ"

"ይሄ ሰውዬን ግን አምነኸዋል ?"

"እንዴት?"

"የአሁኑን ባላውቅም የኣቶ መኮንን ወዳጅ ነበር ምናልባት ከአቶ መኮንን ጋር ተመሳጥረው እኛን አደጋ ላይ ሊጥሉ አስበው ቢሆንስ ?"

" በፍፁም ከአቶ መኮንን ጋር መጣላታቸውንና ላይገናኙ መለያየታቸውን ራሱ ለማ ነግሮኛል "

"ውሸቱን ቢሆንስ "

"አይ ኣይመስለኝም ውሸቱን ቢሆን እስካሁን አንድ የሆነ ፍንጭ እናይ ነበር ዝም ብሎ እውነታውን መቀበል ነው "

"እሺ እንዳልክ ግን በሙሉ ልብህ እንዳታምነው "

"እሺ አታስብ ይልቅ ነገ ቦታውን መርጠን ለአስተዳደሩ እናሳውቅና በቅርቡ የግንባታ ስራው መጀመር አለበት ድርጅቱ በቶሎ ስራ መጀመር አለበት ብሏል እና ደሞ መሀንዲሶቹም ስራው በመዘግየቱ እየተሰላቹ ነው ።"

"እሺ አቡሽ እንሄዳለን ችግር የለውም "

ወደ ገጠሪቱ መንደር ለመሄድ የተነሱት በጠዋት ነበር በአህያ እና በበቅሎ ከሚጎተቱ ጋሪዎች ውጪ ባለ አራት ጎማ መኪና የማያስገባው መንገድ በእግራቸው ለመጓዝ የብሩክን መኪና ወይዘሮ የትናየት ግቢ ትተውት ጉዞ ጀመሩ በጉዞአቸውም ስላሳለፉት ቆይታ አንድ ሁለት እያሉ ማውራት ቀጠሉ።

በቅድሚያ ጥላሁን ስላሳለፋቸው ነገሮች ማውራት ጀመረ ስለ ትምህርቱ ክብደት ፣ ትምህርቱ እና ስራው የሚጠይቁትን ስብዕና እና ሞራል ፣ ስለ ትዕግስት ጥሩ አመለካከት እንዳለው ቆንጆ እንደሆነችና እንደተዋደዱ እና እንደተጫጨ አጫወተው።

ብሩክም ስለ ትዕግስት መስማቱ አስገርሞት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመጀመሪያ ጊዜ ለትምህርት ሲሄድ ያሳየችው አኳኋን ድምፁንና ድርጊቱ እየቀየረ እያሳቀ ከነገረው በኋላ የውጭ ሀገር ቆይታው ምን እንደሚመስል እያጫወተው ወደ መንደሩ ደረሱ።

ሁለቱም በየተራ ቤተሰቦቻቸውን አንድ ላይ ከጠየቁ በኋላ መንደሪቱን ቁልጭ አድርጎ በሚያሳየው ተራራ ላይ ለመውጣት ሲያቀኑ የአቶ መኮንን ቤት በሁለት ፓሊሶች እየተጠበቀ ስላስተዋሉ ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ ወደ ፖሊሶቹ በመሄድ ሰላምታ ካቀረቡላቸው በኋላ ምን እንደተፈጠረ ሲጠይቁ አቶ መኮንን ትናንት በቤታቸው ታይተዋል መባላቸውንና ሲመጡም መሰወራቸውን ገልፀው በከተማው ፖሊስ መምሪያ ትዕዛዝ ቤቱ በፖሊስ እንዲጠበቅ እና ምናልባት ተመልሶ የሚመጣ ከሆነ በቁጥጥር ስር ለማዋል በመንደሩ የተመደቡ የፈረቃ ፖሊሶች መሆናቸውን ስለነገሩአቸው ብሩክና ጥላሁን ጉዞአቸውን መንደሪቱን ወደ ሚያሳየው ተራራ አደረጉ።

****

ብሩክና ጥላሁን የመንደሪቷን ለጥ ያሉ ቦታዎችን እያዩ ጥላሁን አንድ ቦታ ላይ አይኑ እንዳረፈ ለብሩክ ይነግረውና በጥላሁን ምርጫ ቦታውን እንደመረጡ ከበስተ ጀርባቸው "እናንት ከይሲዎች እንዳትንቀሳቀሱ !" በማለት ከየት መጡ ሳይባሉ የሀገሬው አዋቂ የነበሩት አቶ መኮንን ከፖሊስ ጣቢያ ሲያመልጡ የነጠቁትን ሽጉጥ አቀባብለው ከኋላቸው ተገተሩ

ብሩክና ጥላሁንም በመደናገጥ ፈዝዘው ቀሩ አቶ መኮንንም " ምን ያፈዛችኋል እጅ ወደ ላይ !" በማለት ጮኸው ተናገሩ

ሁለቱም በመደናገጥ እጃቸውን አነሱ

"እናንት ከይሲ ዲቃላዎች እኔን ለማሳሰር በናንተ ቤት ወጥመድ አጠመዳችሁ ኣይደል ?" በማለት ሽጉጡን አነጣጥረው ጠየቁአቸው

ጥላሁንም "እሱ ምንም አያውቅም እኔ ነኝ ሁሉንም ያደረኩት መግደል

ከፈለጉም እኔን እዚሁ ይጨርሱኝ "በማለት እየተንቀጠቀጠ ተናገረ

አቶ መኮንንም ሽጉጡን በድጋሚ እያቀባበሉ "ዝም በል እኔ አንተን መግደል ብፈልግ እዚሁ ድፍት አደርግህ ነበር የኔ ችግር ከዚህ ከይሲ ጋር ነው " እያሉ ወደ ብሩክ ሽጉጡን ሲያነጣጥሩ ብሩክ እራሱን እያረጋጋ ኮስተር በማለት ከፍ ያደረጋቸውን ሁለት እጆቹን እያወረደ

"ታድያ ግደለኛ ምን ትጠብቃለህ ከዛም ምንም የማያውቁት የመንደሩ ሰዎች ጋር ሄደህ ዞራ ወጣ ዞራ ገባ እያልክ በጓዳህ የቀቀልቀው አስተሳሰብህን አጠጣቸው "እያለ ሲመልስ

አቶ መኮንን ይበልጥ እየተናደደ "እኔማ ያኔ ነው ያጠፋሁት አባትህን ፀጥ እንዳደረኩት አንተንም ፀጥ ማድረግ ነበረብኝ ግን አሁን ጊዜው ደርሷል ፀጥጥጥ ብለህ አባህ ጋር ትሄዳለህ "እያሉ የአባቱ ሞት ምንነት እንቆቅልሽ ሆኖበት ለነበረው ብሩክ የአባቱ ገዳይ እሱ መሆኑን ሲነግረው

ብሩክ ባለበት መቆም አቅቶት እየተንደረደረ ወደ አቶ መኮንን ሲጠጋ አቶ መኮንን የያዙትን ሽጉጥ ቃታ ሳብ አድርገው ተኮሱ።

አቶ መኮንን አንድ ጊዜ ስበውት የተኮሱበት ምላጭ በተደጋጋሚ ቢስቡትም እንቢ ስላላቸው ጀርባቸው ለሁለቱ ተስፈኞች ሰጥተው በሩጫ ከቦታው ሸሹ።

"አይሆንም !!! "ተራራውን ያናወጠና እስከመንደሩ የተሰማ ጩኸት ብሩክ አሰማ

ጥላሁን መሬት ላይ በደረቱ ለጥ ብሎ ተኝቷል

"አይሆንም !!! በፍፁም አይሆንም !!!"እያለ በጉልበቱ ወደ መሬት ወድቆ ጭንቅላቱን ይዞ እየጮኸ ጥላሁንን ከተደፋበት መሬት አንስቶ አቀፈው

"እርዱኝ እርዱኝ !!!! ኧረ የሰው ያለህ " እያለ እያጣጣረ የነበረውን ጥላሁን በእቅፉ ተሸክሞ ተራራውን ሲወርድ ሁለት ጊዜ የተኩስ ድምፅ ተሰማ።

ፓሊሶች ጥላሁን ላይ ተኩሶ እያመለጠ የነበረው አቶ መኮንን ላይ ሁለት ጊዜ ተኩሰው መሬት ላይ ጥለውት ነበር ።

ብሩክ እየጮኸ ወደ መንደሩ ጥላሁንን ተሸክሞ ገባ የጥላሁን ቤተሰቦች እየጮሁና እያለቀሱ አካባቢውን አወኩት ሌሎች ፖሊሶችም በስፍራው ስለነበሩ ጥላሁንን ተያይዘው ወደ ከተማ ለማድረስ ተረባረቡ። ፓሊሶች ወደ ከተማ በመደወል መኪና የሚችለውን ያህን ገብቶ እንዲጠብቃቸው በስልክ ያወራሉ፤ የመንደሩ ሰዎች ጥላሁንን የሚሸከሙበት ቃሬዛ ፍለጋ ወድያ ወዲህ ይላሉ ፤ የጥላሁን ቤተሰቦችና ብሩክ አሰቃቂ ለቅሶአቸው መንደሩን ረብሾታል።

****

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ነበር ወደ ከተማው ሆስፒታል የተተኮሰበትን ጥላሁንን ይዘው የደረሱት ብዙ ደም ስለፈሰሰውም የብሩክ ደረትና ሸሚዝ በደም ተጨማልቋል የሀኪም ቤቱ ሰራተኞችና ብሩክ ጥላሁንን በህመምተኞች አልጋ በማስተኛት ወደ ድንገተኛ ክፍል እያስገቡት እያለ ጥላሁን የብሩክን እጅ በግራ እጁ ጨምቆ በመያዝ በቀኝ እጁ አውራ ጣት የ 'በርታ' ምልክት አሳየው ብሩክም እያለቀሰ "ምንም አትሆንም .... ምንም አትሆንም " እያለው ሲከተለው የተወሰኑ ሀኪሞች ብሩክን አስቆሙት።

ብሩክ በረንዳው ላይ ፈዝዞ ቆሟል የአባቱ ገዳይ አቶ ግርማቸው እንደነበር በራሱ በግርማቸው አንደበት ሰምቷል። በድንገት የተፈጠረውን የሰሙት

አክስቱ እና ሄኖን በኮሪደሩ እየሮጡ ወደ እርሱ ሲመጡ ተመለከተ።

አክስቱና ሄኖንም እንዲረጋጋና ልብሱን እንዲቀይር ቢነዘንዙትም "ለኔ ነበር ሚገባው ... ለምን ገባህባት ለምን ተንቀለቀልክ ..... የትምህ እንትሄድ አንተን ማጣት አልፈልግም "እያለ በኮሪደሩ እየተመላለሰ ከማልቀስ ውጪ ምላሽ ስላልሰጣቸው ሄኖን በማቀፍ ልታፅናናው ሞከረች ብሩክ ግን ቅድም ጥላሁን በወደቀ ሰዓት ጉልበቱ ተመትቶ ስለነበር በሽታው ተነስቶበት ስለነበር በሽታውም ድንጋጤውም አንድ ላይ ማቀነባበር የተሳነው አዕምሮ ስራውን አቆመ ። መሬት ላይ ተኝቶ ጉልበቱን ይዞ በመጮህ ራሱን ሳተ።

****

ብሩክ ራሱን ያገኘው በነጭ ሀኪሞች ፈገግታ ተከቦ ነበር ከአልጋው ሰር ሄኖን አለች ፤ የተፈጠረውን ለማሰብ እየሞከረ ወደ ሄኖን ቀና በማለት

"ምንድነው ?" አላት

ሄኖንም በተጨነቀ እና በተረበሸ መንፈስ ሆና "እዝናለው ወደ ካንሰር ከማደጉ በፊት መሆን ነበረበት " ስትለው ብሩክ ምን እንደሆነ ስለገባው እግሩን ቀና ብሎ ተመለከተው ለአመታት ሲያሰቃየውና ሲታገሰው የነበረው ህመም በዶክተሩ ትዕዛዝ ባለመመራቱ ቀኝ እግሩን አሳጥቶት በነጭ ፋሻ ተጠቅልሏል።

ድንገትም ብሩክ "ጥላሁንስ ?" በማለት መልሷን ጠብቆ ላይን አይኗን እያየ ጠየቃት

ሄኖንም አንገቷን ካቀረቀረች በኋላ አንገቷን ወደ ጎን በማንቀሳቀስ መሞቱን ነገረችው።

ብሩክም በእንባ እየታጠበ "ጥሌ እኔ ነኝ ጥፋተኛው ይቅር በለኝ "እያለ ደጋግሞ ያወራል ሄኖንም ፈረንጆቹ ዶክተሮች እንዲወጡ ነግራቸው ወንበሯን ሳብ አድርጋ ወደ አልጋው ራሰጌ በመምጣት ፀጉሩን እያሻሸች

"ብሩኬ አሁል ሁሉ አልፏል የምንወደው ጓደኛችን ጥላሁን አቶ መኮንን በቃ የሉም መመለስ አንችልም የተፃፈላቸው ስለነበረ ሄዱ አንተም እንዲህ እንድትሆን ህይወት የፃፈችልህ ፈተና ነው ፈተናውን ማሸነፍ ትችላለህ ።

ወደ ውጭ ሳይሆን ወደ ራስህ ተመልከት አሁንም አቅም ና ጉልበት አለህ ራስህን ስተህ ሁለት ሳምንት ቆይተሀል በዚህ መሀል ሁኔታውን የሰሙ ከሀገር ውጭ እስከ ሀገር ውስጥ ያሉ አዝነዋል በዛች መንደርም ያሉ ሰዎች 'አለቃ ሰው አይገድልም ፤ አለቃ አቶ መኮንን አይደለም 'እያሉ ዘወትር ያወራሉ። ብሩኬ አንተ ብቻ ጠንክረህ የጀመርከውን ህልምህን ጨርስ ብዙ ሰው አብሮህ አለ ራስህን አበርታ አይዞህ።"እያለች ውስጡን በተስፋ በመሙላት ከሀዘኑ ልታፅናናው ሞከረች።

****

ጊዜ ሰራው ነውና ነጎደ ሰውም ባህሪው ነውና ብሩክ ከሀዘኑ ተፅናና የሆስፒታሉ ምርቃት ስነስርዓት ላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መስራቾች እና አንዳንድ የከተማው አስተዳዳሪዎች ንግግር ካደረጉ በኋላ መድረኩ ለብሩክ ተሰጠው።

ብሩክም በድጋፍ ወደ መድረኩ እያነከሰ ወጥቶ ምስጋናውን ካቀረበ በኋላ ንግግሩን ጀመረ "ስሜ ብሩክ ፈይሴ ይባላል የተወለድኩት በዚች ትንሽ መንደር ሲሆን በማሳዎቿ ቦርቄ በዝናቧ ታጥቤ ጭቃዋን አቡክቼ እንደማንኛውም ህፃን ነው ያደኩት ነፍሱን ይማረውና አባቴ የብርሀን ጮራ

እንዳይ ከአስራ ሁለት አመት በላይ አስራ ስድስት ኪሎ ሜትሮችን አቆራርጬ እንድማር በማድረግ የህይወቴን ትልቁ ቦታ ይይዛል እናቴ ህይወቷ ያለፈው ታናናሽ እህቶቼን በምትወልድበት ጊዜ በአቅራቢያዋ የህክምና ጣብያ ባለመኖሩ ነበር ውድ ወንድሜ ጓደኛ ዬ እና አብሮ አደጌ ጥላሁንም ያረፈው የጤና ተቋም በቅርብ ባለመኖሩ ብዙ ደም ፈሶት ነበር" እያለ የመጣበትን እንባ ጠርጎ "እናም ዛሬ ይህ ውብ የሆነ ዘመናዊ ሆስፒታል ያረፈበት ቦታ የጥላሁን ምርጫ ቦታ ስለሆነ እንዲሁም ይህ ሆስፒታል እንዲሰራ ሰማዕት ስለሆነ ሆስፒታሉ ከዛሬ ጀምሮ በውዱ ጓደኛዬ ስም 'ጥላሁን አጠቃላይ ሆስፒታል ' በማለት እንደሚጠራ ስናገር ለጥላሁን ባለኝ ክብር እና ፍቅር እንደሆነ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለው።

በመቀጠል ሌሎች ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ ስራዎች ከኢትዮጵያ እና እንግሊዝ መንግስት ጋር በመሆን እንደምንሰራ እየገለፅኩ በመንደሩ ላላችሁ ወጣቶች መልእክቴን ላስተላልፍ እፈልጋለው ። ነገ በሁሉም አዕምሮ የሚኖር ያልተጨበጠ ተስፋ ነው እስካልሞታችሁ እና ትንፋሻችሁ ከስጋችሁ እስካልተለያየና ማሰብ እስከቻላችሁ ድረስ ፈፅሞ ስለ ነገ ተስፋ እንዳትቆርጡ።

በማለት ከመድረኩ እያነከሰ ሲወርድ በሜዳው ላይ ተሰብስበው ንግግሩን ሲያደምጡ የነበሩት ከልጅነቱ እስከዚህች ቀን የሚያውቁት የመንደሩ ሰዎች ለረጅም ሰአት እንባ በተቀላቀለበት ጭብጨባ ሜዳውን ረበሹት።

ተፈፀመ